ክፍል ዐሥት

በመንገዱ መጽናት

ሃያ ሶስት

አንድ ቀን በጊዜው

አንደ ደመና በዙሪያችን የከበቡን አነዚህ ሁሉ ምስክሮች ስለሆን፤ አንግዲያውስ ለኛም ለንደ ሸክም የሆነብንን ነገር ሁሉ በለኛ ባደ የተጣበቀውን ኃጢአት ለስወገዳን በፊታችንም ያለውን ሬጫ በተሰገስተ በመጽናት ለንሩጥ

(ዕብ 12፡1)

እላት በቂ ነዳጅ ከሌለው እንደሚጠፉ ሁሉ፣ አምነታችንም የሚያቀጣጥለው ከሌለ እንዲሁ ነው።

ቀደም ብለን እንዳየነው፣ ጥንቁቆች ካልሆንን ብዙ ነገሮች ጉዞአችንን ሊያስተጓጉሉ ይችላሉ፤ አፍራሽ ስሜቶች፣ የተሳሳቱ መሻቶች፣ መጥፎ ልማዶች፣ ተስፋ መቁረጥ ወይም ሽንፈት፣ አለቸጋሪ ወዳጅነቶች፣ መከራና ሐዘን ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሁላችንንም ያጋጥመናል፣ ከነዚህ በአሸናፊነት እንድንወጣ እግዚአብሔር ሊረዳን ይፈልጋል።

ለአብዛኞቻችን ግን፣ ሕይወት ባለማቋረጥ በከባድ ቀውስ ወይም በችግሮች የተሞላ አይደለም። ይልቁንም፣ አብዛኛውን ጊዜአችንን የምናውለው በወትሮአዊ የዕለት ተዕለት ኑሮአችን ነው። በሥራችን ላይ በቤተሰባችን፣ በገንዘብ፣ በመዝናኛና በመሳለሉት ላይ ነው። ምግብ መዘጋጀት አለበት፤ ቆሻሻ የሆኑ ነገሮች መጣል አለባቸው፤ የተጠቀምንበት ዕዳ (የአገልግሎት ሂሳቦች) መከፈል አለባቸው፤ ልጆች አዲስ ጫማ እንዲገዛላቸው ወይም ከትምህርት ቤት የተሰጣቸውን የቤት ሥራቸውን ሲሠሩ እርዳታ ወይም ለእግር ኳስ ልምምድ እንዲወስዱ ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህንን ጽሑፍ እየፃፍኩ ባለሁበት ሰዓት እንኳን፣ ከቤታችን ውጭ ያለው የፍሳሽ ማስተላለፊያ ቦይ ተደፍኖ፣ የዝናቡ ውሃ ወደ ውስጥ ጠብ ጠብ እያለ በማጥኛ ክፍሉ ያለውን ምንጣፍ አበስብሷል። ሕይወት በየቀኑ በፈተናና በቀላሉ በቁጣና በንዴት ውስጥ በሚከቱ ነገሮች የተሞላች ናት። እነዚህን ሁኔታዎች ስመከላከል እርምጃ የማንወስድ ከሆነ፣ እምነታችንን በቀላሉ ሊያዳክሙ ይችላሉ።

እምነት ሲቀዘቅዝ (ሲጠፋ)

የዴማስ ማንነት ስለጭር ጊዜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብቻ የታየ ቢሆንም፣ ስለገልግሎቱ በግልጽ ብቁና የተሰጠ ሰው ነበር። ምናልባት ወጣትና በቤተሰብ ኃላፊነት ያልተያዘ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ለሁለት ጊዜ በገዛው አብሮት እንዲሆን የመረጠው፣ ጳውሎስ ወንጌልን ሲሰብክ የረዳውና የደረሰባቸውን መከራና ችግር አብሮ የተጋፈጠ (ቆላ 4፥14፣ ፊሊ 1፥24) ነበር። አንድ ጊዜ ሐዋርያ ጳውሎስ በእምነቱ ምክንያት በታሠረ ጊዜ፣ ዴማስ ጳውሎስን ለመርዳት ከአጠገቡ አልተለየም፣ በሚረዳው ጊዜ ራሱንም ለአሰራት በሚያጋልጥ ሁኔታ እያለፈ ነበር።

ነገር ግን ይህ ከፍተኛ ትጋቱ አልዘለቀም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጻፉት ስሜትን ከሚነኩ አረፍተ ነገሮች በአንዱ፣ ጳውሎስ፣ "ዴማስ ይህን ዓለም ወዶ ተለይቶኛል" (2ጢሞ 4፥10) ብሎ ጽፏል። ከዚያ በኋላ ስለ ዴማስ የተሰማው ምንም ነገር የለም።

ዴማስ ምን አግኝቶት እንዲህ ሊሆን ቻለ? ይህን ለማወቅ የምንችልበት መንገድ የለም፣ ነገር ግን በአንድ ሁኔታ ላይ ሲደርስ ራሱን ለማግለል ወስኖአል፣ ይህች ዓለም በምታቀርብለት ግብጥ ለመዝናናት ና ዓለም ያቀረበችለትን ረብ ያልሆነ ነገር ለማሳደድ ጊዜው እንደሆነ አስቦአል። ጳውሎስ ስለ ዴማስ እምነት መካድ ወይም ምግባረ ብልሹነት ያሰው ነገር የለም፤ ሁላችንም እንደምናውቀው ምናልባት ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ተመልሶ በመሔድ ከሐዋርያ ጳውሎስ ጋር የሠራውን የጀግንነት ሥራና ያሳለፈውን መከራ በኩራት ነግሮአቸው ይሆናል። ነገር ግን የዴማስ የሕይወቱ ቅደም ተከተል ተዘበራረቀበት፣ የዚህ ዓለም ብልጭልጭ ነገር ከኢየሱስ ጉዳይ በለጠበት። ይህን ተገንዝቦ ከሆነ አስገራሚ ነው።

ከጳውሎስ ጋር አብሮ በመጓዝ ያገለግል የነበረው የወጣቱ ጢሞቴዎስ ሁኔታ ይለያል። ጢሞቴዎስ እንደ ዴማስ ተመሳሳይ ፈተናዎች ገጥመውታል፣ ነገር ግን የርሱን መጨረሻ ስንመለከት ፍጹም ልዩ ነው። ጢሞቴዎስ እንደ ዴማስ ልዩ ልዩ መከራዎችና ችግሮች ደርሰውበታል፣ ነገር ግን ጳውሎስ በጻፋቸው መልዕክቶች የዓለምን ምንነት አየገለጸለት ወጣቱ ለዚህ ዓለም ትርፍ ለሌለው ነገር እንዳያስብና ይልቁንም በተቻለው መጠን በሱ ምክር አንዲመራ ባሳሰበው እንደፀና እንመለከታለን። የጳውሎስ ትዕዛዝ፣ "አንተም

የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም ወታደር በመሆን መከራን በትዕግስት ተቀበል" (2ጢሞ 2፥3) የሚል ነበር። ሐዋርያው "ጳውሎስ የተከበርህ ልጄ ሆይ" ብሎ መጥራቱ የሚያስገርም አይደለም።

ዴማስ -- ወይስ ጢሞቴዎስ? የትኛውን ለመሆን ትፈልጋለችሁ?

ጫናዎች

በሚያሳዝን ሁኔታ ብዙ ክርስቲያኖች የዴማስን መንገድ በመከተል ጉዞአቸውን ይደመድሙታል፣ ይህን ሁልጊዜ የሚያደርጉት ሳይገነዘቡት ነው። ራሳቸውን ለክርስቶስ አሳልፈው ሰጥተው ነበር፣ ሰጊዜው እርሱ የሕይወታቸው ማዕከል ነበር። ቀስ በቀስም ክርስቶስ እየተገፋ ወደ ጥግ ይደረግና ሌሎች እንግዳ ነገሮች የርሱን ሥፍራ ይወስዳሉ። በየዕለት ተግባሮች በመጠመድና በዓለም እሴቶች ተጽዕኖ ውስጥ በመግባት ኢየሱስ በማርቆስ ወንጌል በዘሪው ምሳሌ እንደጠቀሳቸው ሰዎች ይሆናሉ። ኢየሱስ በሰጠው በዘሪው ምሳሌ የጠቀሳቸው ሰዎች "የእግዚአብሔርን ቃል በደስታ ይቀበላሉ፤ ይሁን እንጂ የዚህ ዓለም አሳብ፣ የሀብት ፍቅርና ሌላውም ከንቱ ምኞት ወደ ልባቸው ገብቶ ቃሉን ስለሚያንቀው ያለ ፍሬ ይቀራሉ" (ማር 4፥19) በማለት ነው።

ይህ ለምን ይሆናል? *ብዙ ምክንያቶች አሉ፣ ከነዚህ ውስጥ ለንደኛውና ዋናኛው የጊዜ ተጽእኖ (ጫና) ነው።* እግዚአብሔርን ብንረሳ ሕይወታችን የግርግር ይሆናል። አንዲት ሴት በጻፈችልኝ ደብዳቤ "በማንኛውም ባሰብኩ ቁጥር አጸልይ ነበር፣ አሁን ልጅ ከወለድኩኝ ጀምሮ ግን የምፀልየው ጥቂት ቀናትን እያሳለፍኩ ነው" ብላኛለች።

እግዚአብሔር የሚገፋበት ሌላው ምክንያት የሕዝብ ተዕዕኖ ነው። አንድ ሰው በፃፈልኝ ደብዳቤ፣ "ክርስቲያን ነኝ፣ ነገር ግን አለቃዬ እንደ ጉዶሎ ኪስ እንዲያስበኝ አልፈልግም፣ ማስብ ይኖርብኛል አንዴ?" ብሏል። ሌላ የኮሌጅ ተማሪ ደግሞ፣ "የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ሆኜ ጠንካራ ክርስቲያን ነበርኩ፣ አሁን ግን ራሴን ችዬ ከቤት በመራቄ በቀላሉ እንደ ሕዝቡ መኖር ችያለሁ" በማለት መስክሮአል።

ሌላው ትልቁ ችግር ደግሞ ያልተናዘዝነው ኃጢአት ነው። ትንሽ ኃጢአት ወደ ትልቅ ያድጋል፣ በምንፈተንበት ጊዜ

የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድነው? ብለን ከመጠየቅ ይልቅ፣ በተቃራኒው "እሰከመቼ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ክርስቲያን ሆኜ አዘልቀዋለሁ" ብለን እናማርራለን።

የመጨረሻው ምክንያት፣ ነገር ግን፣ የችግሮች ሁሉ ቁንጮ የሆነው፣ የመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓታችን (ስነምግባራችን) መላላት ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን ከመደርደሪያው አይወርድም፣ ጸሎታችን የይስሙላና የይድረስ ይድረስ ዓይነት ነው፣ የሞቀ የነበረው ክርስቲያናዊ ህብረትና ግንኙነታችን ይቀዘቅዝና በቤተ ክርስቲያናችን የምናደርገው ተሳትፎ በጣም ይቀንሳል፣ ለሌሎች የምንሰጠው አገልግሎት ይደበዝዛል። *መንፈሳዊ እድገታችን* ባለበት የሚረግጥና የማያድግ ይሆናል፣ "ይልቅስ በጌታችንና በአዳኛችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እርሱንም በማወቅ እደጉ" (2ጴጥ 3፥18) ወደተባለው አንደርስም። ለራሳችን፣ "እግዚአብሔርን የምፈልገው ከሆነ ሁልጊዜ አለ ብለን እናስባለን፣ በተቃራኒው ደግሞ አንደገና መልሰን "ቁልቁለቱን መውረድ አችላለሁ" እንላለን።

አንድ ነገር አትዘንጉ፣ የማቀጣጠያ ነዳጅ ከሌለ እሳት አንደሚቀዘቅዝ ሁሉ እንዲሁ ያለ *መጽሐፍ ቅዱስ ቃል*፣ ጸሎትና ክርስቲያናዊ ህብረት አምነታችን ይዳከማል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ለይጣን በእኛ ላይ ድልን ያገኛል፣ ልክ ግልጽ በሆነ ኃጢአት ወይም የአሰማመን ችግር ውስጥ እንደከተተን ያህል ይቆጥራል። እኛም በየዕለት ተግባሮቻችን በመጠመድ እምነታችን እንዲቀጭጭ መንገድ እንጠርግለታለን።

መሠረታዊ መርህ

መፍትሔው ምንድን ነው? በመጀመሪያ ደረጃ፣ ችግሩን ለይቶ ማወቅ ነው። የራሳችንን *መንፈሳዊ* ሁኔታ ዝቅ በማድረግና እግዚአብሔር እንደማያሰብልን ድምዳሜ በመስጠት፣ "አኔ አንድ ተራ ክርስቲያን ነኝ" እንላለን።

ነገር ግን እንደዚህ ዓይነቱ አመለካከት የመጽሐፍ ቅዱስን ውሳኝ *መርህ* አንዳናስተውል ይከለላል። ኢየሱስ *ሥልጣኑንና* ፍቅሩን በሁለንተናዊ ኑሮአችን ውስጥ ሊያንሠራፋ ይፈልጋል። ከሱ ቁጥጥር ውጭ የሆነ ምንም ነገር ስለሌለ ሕይወታችንን ያሳደፈውን ኃጢአትና የለይጣን አሠራር ከእኛ ላይ ፈጽሞ ሊያስወግደው ይፈልጋል።

በሳምንቱ ካሉን ሰባት ቀናት ውስጥ ሰድስቱን ለራሳችን ጉዳይ ተጠቅመን እግዚአብሔርን በአንዱ ቀን እንወስነዋለን። ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ለሰ ነፍሳችን እንጂ በዓለም ስላለው ጉዳያችን - ስለ ጊዜያችን፣ ገንዘባችን፣ ሥራችን ወይም ቤተሰባችን ግድ እንደማይለው እንደመድማለን። በሌላ አነጋገር፣ ሕይወታችንን ለሁለት ክፍለን እግዚአብሔርን ባንድ ክፍል ገድበን ከሌሎች ጉዳዮቻችን እናስወጠዋለን።

ይህ ትልቅ ስህተት ነው። ይህን እንድናደርግ ለይጣን የሚፈልገው ነው። ለይጣን ለእግዚአብሔር በላምንት አንድ ቀን ብቻ እንድንወስን ካግባባን ወይም ከሕይወታችን የተወሰነ ክፍል ብቻ እንድንተውሰት ካደረገ ድል ተቀዳጅቷል ማለት ነው። ነገር ግን አንድ ቀን ለይጣን ድል ተመቶና የኢየሱስ ጌትነት በፍጥረት ሁሉ ላይ ይፋ ይሆናል። እግዚአብሔርም ይህንን አሁኑኑ እንዲጀመር ይፈልጋል።

ኢየሱስ በእያንዳንዱ የሕይወታችሁ ጉዳይ አንዳይገባ ያገደው ምንድነው? በራሳችሁ ልታደርጉት (ልትቆጣጠሩት) በመፈለግ ነው? ወይስ እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ሥልጣን እንዳለውና ሥልጣኑንም ለመዘርጋት እንደሚፈልግ ክቶ አልተረዳችሁም? ወይስ እርሱ በእናንተ ላይ ጌታ እንዳይሆን ያገደው ኃጢአት አለ? ምክንያታችሁ ምንም ይሁን ምን፣ ሁለተናችሁን መሉ ለመሉ ለክርስቶስ እንድትሰጡና የሕይወታችሁን ክፍል ሁሉ እንዲቆጣጠረው አስረክቡት። *መጽሐፍ ቅዱስ* እንዲህ ይላል "ሁለንተናህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ። በእርሱም ታመን እርሱም ይረዳሃል። ታማኝነትህ እንደ ጠዋት ብርሃን እንዲወጣ በፍርድ የምታገኘው ነፃነት እንደቀትር ጸሐይ ደማቅ እንዲሆን ያደርግልሃል" (መዝ 37፥5-6)።

የጊዜ ወጥመድ

ሁላችንም በቀን ውስጥ ተመሳሳይ የጊዜ መጠን (ደቂቃና ሰዓት) ያለን መሆኑ ግልጽ ነው፣ እውነትም ነው። ዋናውና ትልቁ ጥያቄ፣ እንዴት እንጠቀማቸው? ነው።

በዚህ ዘመን አብዛኛው ህዝብ አንድም በስራ የተወጠረ ወይም ደግሞ በተቃራኒው የቦዘነ ነው። የጊዜ አጠቃቀማችን የግርግር፣ ምንም ነገር በአግባቡ የማይሠራበት ወይም በጣም የተጨናነቀና ያቀድናቸውን ነገሮች ለመፈጸም የምንወጠርባቸው

ናቸው ወይም ደግሞ በቋሚነት ለመደለትና ለመዝናናት ብቻ የሚታሰብ ነው። በታሪክ በጣም ጭንቀታምና ችኩል ትውልድ ነን - ደግሞም መዝናናት የምንወድ ነን። መጽሐፍ ቅዱስ ሁለቱም ጽንፎች ስህተት እንደሆኑ ይነግረናል።

በሥራ የተወጠሩና ምንም ዓይነት ትርፍ የሚባል ለዓት የሌላቸውን ለዎች ሕይወት ልብ ብላችሁ ተመልከቱ። አንድ ጊዜ ነጋዴ የሆነ ለው፣ "ሁልጊዜ በሥራ መወጠር ምን ችግር አለው? መጽሐፍ ቅዱስ ጠንክረን መስራት እንዳለብን ይናገር የለም እንዴ?" ብሎኛል። እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ ትክክል እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስም፣ "እጅህ ለማድረግ የምታገኘውን ሁሉ እንደ ኃይልህ ታድርግ" (መክ 9፥10) እንደሚል አረጋግጬለታለሁ። እንዲሁም "ስንፍና ያደኸያል፣ ተግቶ መሥራት ግን ያበለጽጋል" በማለት ደስታውሰናል (ምሳ 10፥4)።

አሳዛኙ ነገር ይህ ነጋዴ በሥራ የመወጠር እደጋ ምን እንደሆነ የማሳያ ሕያው ምሳሌ ነበር። ልጆቹ ከሉ በተቃራኒው በመቆም የተበሳሹ ዋልጌዎች ሆኑ። በራሱ ፈቃድ በሳምንት ከ60-70 ለዓት ይሠራ ነበር፤ ለዕረፍት ወይም ለቤተሰቦቹ ጊዜ አልነበረውም፤ የትዳሩ ሁኔታ የተመለቃቀለና የተበላሸ ነበር፤ ልጆቹ ጠላቶቹ ሆነውበት ነበር፤ ጤንነቱም የተቃወሰ ነበር። በተጨማሪም ሀብንም ስራ በትክክል አቀናጅቶ መሥራት ባለመቻሉ በእፍረትና በጭንቀት ውስጥ አልፏል። በዚህ ሁሉ ውጥረት መሐል ሕይወቱ ከደስታና ከሰላም የራቀ ነበር።

ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ፣ እንዳንድ ለዎች ከመጠን ያለፈ ትርፍ ለዓት አላቸው። በባህርያቸው ስልቹና በቋሚነት እስደሳች ነገር የሚፈልጉ በመሆናቸው አእምሮአቸውን ምንም ጥቅም በሌለው ነገር (እነሱ መዝናኛ ነው ብለው የሚያስቡት በእብዛኛው ግን ሀከትና ብጥብጥን ወይም የዘቀጠ ባህርይን በሚያገሳ) ያዝናናሉ። ወይም በአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኝነት ወይም ደግሞ በአልኮል መጠጥ ሱሰኝነት ውስጥ ወይም በሌላ አፍራሽ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ይገባሉ።

ሁልጊዜ ያለንን ጊዜ እንዴት መጠቀም እንደሚገባን ለመምረጥ እንችልም፤ በርግጥ አንዳንድ ጊዜ ያለንበት ሁኔታ ራሱ ይቆጣጠረናል። ስለዚህ ጉዳይ ሳሰብ ሁልጊዜ ልቤ በየዕለቱ በሕይወት ለመቆየት እንደሚፍጨረጨሩ ወደሚጽፉልኝ ጥቂት

እናቶች ይሔድብኛል። እቅመቢስነት፣ ሀመም፣ ሥራ ማጣት፣ ተጣሪ መሆን ዱሮ እንደምንሠራ አሁን እንዳንሠራ ሊያደርጉንና ዋጋቢሶች "እንዲሁ ጊዜ የምናባክን" አድርገን ራሳችንን እንድንቆጥር ያደርጉናል። ነገር ግን ምንም እንኳ ሁኔታዎች ጊዜያችንን ቢቆጣጠሩም፣ አሁንም በእግዚአብሔር እርዳታ ራሳችንን ልንገዛ (ልንቆጣጠር) እንችላለን። በጊዜያችን ላይ ቁጥጥራችንን እንድናጠናክርና በአዳዲስ ቀኖች በአግባቡ እንድንጠቀም ሊረዳን ይችላል።

ጊዜን በዘዴ (በጥበብ) መጠቀም

ጊዜያችንን እንዴት አድርገን በጥበብ (በዘዴ) መጠቀም እንችላለን? እስኪ ጠቃሚ ሆነው ያገኘኋቸውን አራት ነጥቦችን ልግለጽላችሁ።

አንደኛ፣ አያንዳንዱን ቀን ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁ ሰጦታ አድርጋችሁ ቁጠሩት። አያንዳንዱን ቀን እንደ አስጨናቂና ከፋ አድርጋችሁ ከማየት ይልቅ እግዚአብሔርን ታገለግሉት ዘንድ በዕድሜያችሁ ላይ የተጨመረላችሁ ሌላ ዕድል እንደሆነ ተመልከቱ። ጊዜ የማያልቅ ነገር አይደለም፣ የበለጠ ተጨማሪ ጊዜ እንደቀረን ለማሰብም እንችልም፤ አንድ ቀን የምድር ቆይታችን በድንገት ያበቃል። መዝሙረኛው "እኔ ሁልጊዜ በአንተ እጅ ነኝ" (መዝ 31፥15) ብሏል። የተሰጠንን አንድ ቀን ጨርሰን ከእንቅልፋችን በነቃን ጊዜ ልናደርገው የሚገባን የመጀመሪያ ነገር እግዚአብሔር ስለሰጠን ተጨማሪ ቀን እርሱን ማመስገን ነው።

ሁለተኛ፣ ጊዜአችሁን ለእግዚአብሔር አውሉት። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ቀን የሰጣችሁ በምክንያት (በዓላማ) ነው፤ በከንቱ እንድታባክኑት ወይም ደለአግባብ እንድትጠቀሙበት እይደለም። እግዚአብሔር የሰጠንን ጊዜ ስለምንጠቀምበት ሁኔታና መንገድ እንጠየቅበታለን። አንዲት ደቂቃ እንኳ ብታመልጠን ልንመልሳት አንችልም።መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ጥበበኞች ለመሆን እንድንችል ዕድሜያችን ምን ያህል እጭር እንደሆነ አስተምረን" (መዝ 90፥12) ይላል።

ይህንን እንዴት እድርገን በተግባር ልናውለው እንችላለን? ይህ ማለት የተሰጠንን ጊዜ በተግባር ላይ ለማዋል በጥበብና ውጤታማ በሚሆን መንገድ ማቀድ እንድንችል እንዲረዳን እግዚአብሔርን መለመን ይሆናል። ይህ ማለት ጊዜአችንን እንዴት

እንደምንጠቀምበት ደግመን ደጋግመን ማሰብና እግዚአብሔር በሚፈልገው ቅድመ ተከተል ማስተካከል ማለት ይሆናል። እንዲሁም በጣም ባተሌ የሆንንበትን (ወይም የተጨናነቅንበትን) ሁኔታ መመርመር ያስፈልገናል። የምናደርገው በርግጥ አስፈላጊ ነው? ወይም የምናደርገው ዝም ብሎ የሌሎችን ቀልብ ለመሳብ ነው? ብለን ልንፈትሽ ይገባናል። ሁሉንም ነገር ልናደርግ አንችልም፣ አንዳንድ ሁኔታዎች እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆኑ "እምቢ አልችልም" ልንል ይገባል።

ሰላተኛ፣ ጊዜአችሁን ለእግዚአብሔርና ለሌሎች መድቡ። ማንም ክርስቲያን፣ "ለእግዚአብሔር ባተሌ ሆንኩ አይልም"፣ ነገር ግን (ካለመፀለይና መጽሐፍ ቅዱስ ካለማንበብ አልፎ) እንዴት ቀኑን ሙሉ ስለእግዚአብሔር ሳታስቡ ታሳልፋላችሁ? የናንተን እርዳታ ወይም ማበረታቻ የሚፈልግን ሰው ችላ ማለት እንዴት ይቻላችኋል?

ይህ ለምን ይሆናል? አንደኛው ምክንያት ለእግዚአብሔር ትርፍ ጊዜያችንን ልንሰጠው ስለምንፈልግ ነው። ነገር ግን ትርፍ ጊዜ ሳናገኝለት ቀኑ ያልቃል። በሌላ አባባል፣ የምናደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ በአዕምሮአችን (በልባችን) ስንመዘግብ እግዚአብሔርን በዝርዝራችን መጨረሻ ላይ እናስቀምጠዋለን። መሆን ያለበት ግን ተቃራኒው ነው። ኢየሱስ፣ "እናንተ ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን ጽድቅና መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ሌላውም የቀረው ነገር ሁሉ ይጨመርላችኋል" (ማቴ 6፥33) ብሏል።

በመጨረሻም፣ ለራሳችሁ ፍላጐት ጊዜ ይኑራችሁ። ሁላችንም ዕረፍትና መዝናናት እንፈልጋለን፣ እግዚአብሔር የስራን በዚህ መልኩ ነው። አንዳንድ ሰዎች የዕረፍት ፈቃድ ሲወስዱ ወይም ለጥቂት ለዓታት ከሥራ ሲለዩ የጥፋተኝነት ስሜት ይሰማቸዋል፣ ነገር ግን እንዲህ ሊሆኑ አይገባም። በጣም በተጨናነቀ አገልግሎት ውስጥ ሳሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን፣ "እናንተ ብቻችሁን ወደ አንድ ገለልተኛ ሥፍራ ሒዱና ጥቂት ዕረፉ" (ማር 6፥31) ብሏቸዋል። ኢየሱስ ለማረፍ ጊዜ ያስፈልጋል ካለ እኛስ አያስፈልገንም? አንድ ሰው በቂ እንቅልፍ ካጣ ወይም በአግባቡ የማይመገብ ከሆነ በብዙ መልኩ ለሰይጣን ጥቃት የተጋለጠ ይሆናል።

በሥራ ከኢየሱስ ጋር

ጊዜአችንን በአግባቡ መጠቀም አስፈላጊ ነው፣ ነገር ግን አብዛኞቻችን በቀን ካለን ጊዜ ውስጥ የበለጠው የተያዘው በሥራ ነው። ይኼ እውነት የሆነው ተቀጥረው ስራ ለርተው ደሞዝ በሚያገኙት ላይ ብቻ አይደለም፣ በቤት ውስጥ ሆነው በስራ ተጠምደው የሚውሉትንም ይጨምራል።

ብዙ ክርስቲያኖች፣ በየዕለት ሥራቸውና በእምነታቸው መካከል ሊኖር የሚገባው ግንኙነት ጥቂት እንደሆነ አድርገው ይመለከታሉ፣ እንዲያውም የሚሠሩትን ሥራ (ሥራ መሥራትን) እንደ ሸክም ይመለከቱታል። በድፍረትም፣ እግዚአብሔር አዳምን ከኤደን ገነት በማባረር "በወዝህ ትበላለህ" አላለውምን? (ዘፍ 3፥19) ይላሉ። ነገር ግን ይህ ጠቅላላ አውነታውን የሚያሳይ አይደለም። ሥራ በራሱ ክፋ አይደለም፣ ከውድቀት በፊት እንኳ እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በኤደን ገነት እኖረው። ይህንንም ያደረገው ሰው የእትክልቱን ቦታ እንዲያለማና እንዲንከባከበው ነው (ዘፍ 2፥15)። በተጨማሪም በመንግሥተ ሰማያት፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን፣ ዕረፍት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር እንድንሠራ ያዘጋጀልን ሥራ አለ (ራዕ 22፥3)።

ክርስቶስ በሕይወታችን እያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ሥልጣኑን ለማስፈን እንደሚፈልግ ልብ በሉ። በሥራችንም ሊመራን ይፈልጋል። በየቀኑ በምትሠሩት ሥራ ላይ ኢየሱስ ጌታ ሆኖአል? ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?

እንደኛ፣ ሥራችሁን እንደሸክም ከመመልከት ይልቅ በእግዚአብሔር የተሰጣችሁ ኃላፊነትና አደራ እንደሆነ አድርጋችሁ ቁጠሩት። ሥራችሁ ምንም ይሁን ችግር የለውም፣ ሥራችን ከክብር ጋር ሕጋዊ ቢሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠን ነው። ምናልባት ሥራችን አድካሚና ትርጉም የለሽ ቢሆንብንም ከእግዚአብሔር እንደተሰጠን አንድ ጊዜ ካወቅን አመለካከታችን ይቀየራል። የመክብብ መጽሐፍ ፀሐፊ ይህንን አውነት፣ "እንግዲህ ለሰው የሚጠቅመው ነገር በኖር ደክሞ በመሥራት ያፈራውን ሁሉ በመብላትና በመጠጣት ራሱን ለማስደሰት መቻሉ ነው፣ ይህም ከእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑን ተረድቻለሁ" (መክ 2፥24) በማለት ጽፏል።

ስለ አንድ ሰው ለአንድ ዓይነት አገልግሎት ወይም ተልዕኮ በእግዚአብሔር "እንደተጠራ" አድርገን እንናገራለን፣ ነገር ግን ኢየሱስና ሌሎች በፈቃዱ ውስጥ መሆናቸውን ካወቃችሁ እናንተም ስለሥራው ተጠርታችኋል። ይህ ማለት ሥራው ከቶ አስልቺ ወይም ክባድ ወይም አድካሚ አይሆንም ማለት ነው? በርግጥ አይደለም። ነገር ግን ሥራችንን እግዚአብሔር እንደሰጠን አንድ ነገር አድርገን ስናይ፣ እንዲያውም የድግግሞሽ ተግባራት እንኳን ቢሆኑ ዋጋ አላቸው።

በተጨማሪም፣ በምትሠሩት ሥራ ታማኞች ሁኑ። ኢየሱስ፣ በምድር የሕይወት ዘመኑ አብዛኛውን ጊዜ የኖረው፣ ማርያምና ዮሴፍ ከግብጽ ከተመለሱ በኋላ በተቀመጠበት በናዝሬት ነበር። ዮሴፍ አናጢ ነበር፣ ኢየሱስ የዮሴፍን ዱካ በመከተል አናጢ ሆኖ ነበር (ማር 6፥3)።

ኢየሱስ እንዴት ጥሩ አናጢ እንደነበር ልትገምቱ ትችላላችሁ? የዕቃ መደርደሪያ እንዲሠራላችሁ ካዘዛችሁት በሮቹን አልገጠመላችሁም? ወይም ደግሞ እንጨቱ የተስጠነቀ ነበር? ወይም ሠርቶ ያለረከባችሁ ሁለት ወራት ዘግይቶ ነው? በርግጥ ኢየሱስ እንደዚህ አላደረገም። እኛስ በምንሰራው ሥራ ታማኝነትን እናሳድላለን?

ታሪክ ፀሐፊዎች እንደሚነግሩን በሮማውያን አገዛዝ ስር ከነበሩ ህዝቦች መካከል ግማሽ ያህሉ ባሮች ነበሩ። (አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች የሮማ ውድቀት ምክንያት የሆነው ለዚህ ምግባረ ብልሹና አስከፊ ተቋም ድጋፍ በማድረግዋ ነው ይላሉ።) በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩ ክርስቲያን ባሮች በነበራቸው አነስተኛ የነፃነት ዕድል ውስጥ ሆነው በታማኝነት እንዲሠሩ ማስገንዘቢያ ተሰጥቷቸዋል፣ "አገልጋዮች ሆይ ለምድራዊ ጌቶቻችሁ በሁሉ ነገር ታዘዙ የምትታዘዙትም ሰውን ደስ ለማሰኘትና ለታይታ ሳይሆን ጌታ ኢየሱስን በመፍራትና በልበ ቅንነት ይሁን" (ቆላ 3፥22)። አስረሥቻቸውም (ጌቶቻቸው) እንደዚሁ በአውነትና በትህትና እንዲሆኑ ታዘዋል፣ "ጌቶች ሆይ! እናንተም በሰማይ ጌታ እንዳላችሁ ታውቃላችሁ፣ ስለዚህ አገልጋዮቻችሁን በቅንነትና በእኩልነት አስተዳድሩአቸው" (ቆላ 4፥1)። ክፍለ ዘመኑ እንዳለቀ የሰው ልጅ ክቡር መሆኑ በወንጌል አማካይነት የተዘራው ዘር ከዘመናት በኋላ በመጨረሻ ፍሬ አፍርቶ የባሪነትን ሥርዓት አንገዳግዷል (በእርግጥ ከፍተኛ ትግልን የጠየቀ ነበር።) እናም ዛሬ

ማንኛውም ዓይነት የባርነት አገዛዝና ጥቃት እግዚአብሔርን እንደማጥቃት የሚቆጠር፣ የተጠላና የተወገዘ ነው። ምንም እንኳ በምድር ላይ በተለያዩ የዓለም ክፍሎችና አገዛዝ ውስጥ የምንኖር ቢሆንም ወሳኙ መርህ ግን አልተሰወጠም። ሠራተኛ ወይም አሠሪ ብትሆኑ፣ በታማኝነትና ኃላፊነታችሁን በብቃት በመወጣት ሥሩ፣ እንደዚሁም የሚጠበቅባችሁን ትህትናና ቅንነት በሥራችሁ ሁሉ ላይ አሳዩ።

በመጨረሻም፣ ሥራችሁን በሐቀኝነት ሥሩ። በሥራቸው ላይ ችግር ካጋጠማቸው ክርስቲያኖች አልፎ አልፎ ደብዳቤ ይደርሰኛል። አሰሪዎቻቸው ሕገ ወጥ ወይም የማጭበርበር ሥራ እንዲሠሩ ወይም ወሲባዊ ጥቃት ሊፈጽሙባቸው የጠየቋቸው፣ ወይም የማጭበርበር ወይም ሌላ ሕገወጥ ድርጊት ያጋጠማቸው ናቸው። እንደዚህ ዓይነት ችግሮች በጣም ውስብስብና ፈታኞች ናቸው፣ አንዳንድ ጊዜ ትክክለኛ የአተገባበር አቅጣጫ ስይቶ ለማወቅ ቀላል አይሆንም። ነገር ግን ምንም ዋጋ ቢያስከፍልም፣ ሥራቸውን በታማኝነትና በሐቀኝነት እንዲሠሩ አነግራቸዋለሁ። ከእግዚአብሔር ፈቃድና መስፈርት ጋር ድርድር ውስጥ እንዳይገቡ አመክራቸዋለሁ። እግዚአብሔር ከነርሱ ጋር እንደሆነና እንደማይተዋቸው አሳስባቸዋለሁ። ከባድ ቢሆንም ከከፋ ይልቅ መልካም መሥራት እንደሚሻል አስታውሳቸዋለሁ።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ "እናንተ ራሳችሁ ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁ። አሁን ግን በጌታ ብርሃን ስለሆናችሁ በብርሃን እንደሚኖሩ ሰዎች ኑሩ (ምክንያቱም የደግነት ሁሉ የጽድቅና የእውነት ፍሬ የሚገኘው ከብርሃን ነው) ስለዚህ ጌታን ደስ የሚያሰኘው ነገር ምን እንደሆነ መርምሩ። ወደ ብርሃን አውጥታችሁ አጋልጡት እንጂ ፍሬ ቢስ ከሆነ ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ (ኤፌ 5፥8-11) ይላል። እነዚህ ቃላት ሁለተናችሁን፣ ሥራችሁንም ጨምሮ የሚመለከቱ ናቸው።

የሕይወታችሁ የዕለት ተዕለት የድግግሞሽ ተግባራት እምነታችሁን እንዳያላሰ አትፍቀዱላቸው፤ ነገር ግን በየቀኑ ሁለተናችሁን (ጊዜአችሁንና ሥራችሁን ጭምር) ለኢየሱስ አገዛዝ አስረክቡ። ከዚያም አምነታችሁና የፍቅር ግለታችሁ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር የለጣችሁን "ነዳጅ" - የክርስቲያኖች ህብረት፣ የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት "ነዳጅ" - በመጠቀም ኃይላችሁን አድሱ።

ሃያ ዐራት

መንታ መንገዶች



ስየመከርኩሀና ስያስተማርኩህ የምተሔደበትን መንገድ ሰመሰከትሃብሁ።

(መዝ 32÷8)

ያለፈ ነገር መለወጥ አንችልም፣ ነገር ግን መጪውን መለወጥ እንችላለን። አንድ በአሥር ቤት ታስሮ የሚገኝ ሰው በቅርቡ፣ "የፈፀምኳቸውን አንዳንድ ውሳኔዎቼን ወደኋላ ተመልሼ አንዳልፈጽማቸው መወሰንና መለወጥ አልችልም። መጥፎ ውሳኔዎችን በማከታተል ፈጽሜአለሁ፣ አሁን የዘራሁትን አያጨድኩ ነው" በማለት ጽፎልኛል። ምናልባት የዚህ ሰው ሁኔታ ከእናንተ የተለየ ይሆናል፣ ነገር ግን ማንኛችን ነን ያለፈውን ስህተት ለመከላከልና መጥፎ ለራን ላለመለራት የምንመኘውና የምንፈልገው?

የሚያሳዝነው ግን፣ የብዙ ሰዎች ሕይወት መጨረሻ በሌለው መጥፎ ምርጫ ሽክርክሪት ውስጥ የተጠመደ መሆኑ ነው። እናም መጥፎ ምርጫዎች ምንጊዜም ውጤታቸው ያው መጥፎ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለን ትክክል ነው፣ ሰው የሚያጭደው የዘራውን ነው (ገላ 6÷7)። አንዲሁም "ፍርድ ብታጓድል መከራ ያገኝሃል" (ምሳሌ 22÷8) ብሎ ያስጠነቅቀናል።

ክርስቲያኖች እንኳ መጥፎና የስህተት ምርጫ ከማድረግ ነፃ አይደለንም። በሕይወታችን ውስጥ ከሚገጥመን ሸካራ ትምህርት አንዱ ውሳኔአችን በሚያስከትለው ውጤት ለመኖር መገደዳችን ነው። ጥንቃቄ የተላበሰ ምርጫ የማድረግ ችሎታ ልናዳብር የሚገባን ለዚህ ነው።

እግዚአብሔር በፊታችን ያስቀምጠው የሕይወት ጉዞ ጎዳና አልጋ በአልጋ አይደለም፣ በጉዞአችን አዘውትረው መንታ

መንገዶች፣ መለቀለኛና አቋራጭ መንገዶች ያጋጥሙናል። አንዲህ ዓይነት መንገዶች ከፊታችን ሲደቀኑ የትኛውን መርጠን ነው የምንጓዘው? ሕይወት በውሳኔ የተሞላች ናት፣ ይህንን ደግሞ ልናመልጠው አንችልም። አንዳንዶቹ ቀላል (ክብደት የሌላቸው) ናቸው፣ ጭራሽ ግምት ውስጥ የሚገቡ አንኳን አይደሉም። ሌሎቹ ግን (በጊዜው በሚገባ ባንረዳቸውም) በሕይወታችን ለውጥ የሚያስከትሉና ከባድ ናቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር ለለምናደርገው ምርጫ እና ለለምንወስነው ውሳኔ በእርግጥ ይጠነቀቅልናል?

የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈለግ

ለዓመታት ያህል ኮሚኒዝም ተጽዕኖ ባደረገባቸው የምስራቅ አገሮች፣ በተለይ በሶቪዬት ኅብረት፣ አንድንሰብክ እግዚአብሔር በርን አንዲከፍትልን ጸልዬአለሁ። በመጨረሻም በሞስኮ ከተማ ወንጌልን አስብክ ዘንድ በተጋበዝኩ ጊዜ ልብን በሚያስጨንቅ ሁኔታ ውሳኔ ለመስጠት ተቸገርኩ። በእርግጥ እግዚአብሔር በሩን ከፍቶልኝ ነው? ወይስ ለያጣን ወጥመዱ ውስጥ ለመክተት ያዘጋጀው ተንኮል? ወይስ ለይጣን ያለንን አገልግሎት ለማጥፋት ያቀደው ነው? በማለት ብቻዬን አስቸጋሪና ትክክለኛውን መንገድ ለማወቅ ፈታኝ በሆነና ለውሳኔ በሚያስቸግር ፈተና ውስጥ ገባሁ።

ችግሩ ግብገፐው መያያገር ያለው መሆኑ ነው፣ ዓለም አቀፋዊ በሆነ የለላም ጉባኤ ላይ እንድሳተፍ የተጠየቅኩበት ጭምር ነበር። ለሞስኮ መንግስት ድጋፍ የሚለጠና የሶቪየት ህብረትን ፓለቲካዊ አቋም የሚያንፀባርቁ፣ በአንፃሩ ደግሞ ሌሎች መንግሥታትን የሚተናኮሉና የአስተዳደር ፖሊሲያቸውን የሚነቅፉ አዝማሚያዎች ነበሩ፣ የኔንም አገር አሜሪካንን የሚኮንኑ ነበር። ይህ ልዩ የሆነው ዓለም አቀፍ የለላም ጉባኤ በቤተ ክርስቲያን ድጋፍ ለጪነት የሚካሔድ ቢሆንም ብዙዎች እንደሚያስቡት ከጉባኤው በስተጀርባ የሶቪየት ህብረት መንግስት ቁጥጥር ያለበት ነበር። ይህንን ጉባኤ ብካፈል፣ የሶቪየት ህብረት ፓለቲካዊ ፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ አልሆንም? እንደ ቅል (ገራገር) ያዩኝ ይሆን? ወይስ ወንጌልንና ከሚኒዝምን እንደሚያስታርቅ ሰው? በሚል ወሳኝ ጉዳዮች ተወጠርኩ። አንዳንድ የአገልግሎታችን የቦርድ አባላት - ጥበበኛ የሆኑና የሚከበሩ ወንዶችና ሌቶች እንኳን ሳይቀሩ - ተጠራጥረው ነበር። የአሜሪካን ምክትል ፕሬዝዳንት፣ አንዱን አምባሳደር አስጠርተው የተላከልኝን የግብገር ደብዳቤ አስንብበው

በጉባኤው ላይ መሳተፍ እንደማይገባኝ አጥብቀው ተቃወሙ። የመጽሔትና የጋዜጣ አሳታሚዎችም በጉባኤው ላይ መሳተፌን በመቃወም አቋም ያዙ።

እኔ ግን አብዝቼ በፀለይኩ ቁጥር (መጽሐፍ ቅዱስን እየመረመርኩ፣ ጠቃሚ የሆነ ምክርንም ከወገኖች እየጠየቅሁ) ግብዣውን እንድቀበል እግዚአብሔር እየመራኝ እንደሆነ አመንኩ። ውሳኔውን በአምንታ ሰቀበል የሰላም ጉባኤውን ሰካፈል ደግሞ በተመልካችነት መካፈል እንዳለብኝ ተገነዘብኩ፣ በዚህ መልኩ ብሳተፍ ጉባኤው የሚያወጣውን አዋጅና መግለጫ የድጋፍም ሆነ የተቃውሞ ድምጽ ከመስጠት ውጪ ያደርገኛል፣ በጉባኤውም ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰላም ምን እንደሚናገርና ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም ምን እንደሆነ ለመናገር እንደምችል አሰብኩ። ሞስኮ በሚገኙ ሁለት ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ወንጌልን ለመስበክ እንደምችል ተረዳሁ።

በመጨረሻም ለመሔድ ወሰንኩ። ምንም እንኳ ጉዞአችን አለመግባባትን የፈጠረ ቢሆንም ጥልቅ የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድና አመራር ነበረው። ወንጌልን በሞስኮ መስበክ ብቻ ሳይሆን በአገሪቱ ግዛት በሙሉ እግዚአብሔር የአገልግሎት በር በሰፊው ከፍቶልኛል። ይህንን ቀደም ብዬ አለስተዋልኩትም ነበር። ይህን ግብዣ ውድቅ ባደርገው ኖሮ አገልግሎታችን ባላደገ ነበር። በተለይ በዚህ የአገልግሎት ጉዞ መንታ መንገድ አጋጥሞኝ ነበር፣ እግዚአብሔር ግን መምረጥ ያለብኝን መንገድ አሳይቶኛል።

እግዚአብሔር ይጠነቀቅልናል?

በእርግጥ እግዚአብሔር ለምንሰጠው ውሳኔአችንና ምርጫችን ይጠነቀቅልናል? እግዚአብሔር ለሕይወታችን እቅድ - እና በትክክል የምናውቀው እቅድ - አለው? ወይስ እኛ እራሳችን በራሳችን ውሳኔ እንድናደርግ ይተወናል?

የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ ግልጽ ነው፣ እግዚአብሔር ስለ እኛ ሁሉን ነገር ያውቃል፣ ደግሞም ለእኛ ምን እንደሚሻለንና እንደሚበጀን ያውቃል። ከፊታችን ሊገጥመን የሚችለውን አደጋ ይመለከታል፣ የሚያጋጥመንንም ደስታ ያውቃል። ነገር ግን እግዚአብሔር የሚያውቀው መልካም የሆነውን ብቻ ሳይሆን መልካም ነገር እንዲሆንልንም ይፈልጋል። ምክንያቱ በጣም ቀላል ነው፣ እግዚአብሔር ይወደናል።

ይህ ሆኖ ሳለ፣ አንዳንድ ሰዎች ለሕይወታቸው መልካም እቅድ እንዳለው ለማመን ይቸገራሉ። "እሱ በሥራ የተወጠረ ስለሆነ የኔ ጉዳይ ግድ ሊለው አይችልም" በማለት ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ። ሌሎች ደግሞ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ፈጽሞ አያስቡም፣ እራሳቸው ለራሳቸው እንዲወስኑ የተወሰኑት አድርገው ያስባሉ። አሁንም ሌሎች ደግሞ ሌላ ችግር ያለባቸው አሉ፣ እግዚአብሔር ጨካኝና አምባገነን እንደሆነና ሰዎችን ማስጨነቅ የሚፈልግ እንደሆነ አድርገው ያስባሉ። ለምንስ እንዲህ እንድንሆን ይፈርድብናል በማለት እንደነሱ አስተሳሰብ ጉስቋሎች እንድንሆን እስከሆነ ድረስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለምን እንፈልጋለን? ብለው ይስባሉ።

ይሁን እንጂ፣ ለብዙዎቻችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ አንዳናውቅ መሰናክል የሚሆንብን አንዱና ትልቁ ችግር የራሳችንን ሕይወት በራሳችን ምርጫ ለመምራት ስለምንሮጥ ነው። የኛ ችግር በልባችን ውስጥ ጦርነት መኖሩ ነው - ጦርነቱ በእግዚአብሔር ፈቃድና በራሳችን ፈቃድ መካከል የሚደረግ ነው።

እግዚአብሔርን የምንፈልገውና እንዲመራን የምንጠይቀው ለጥቅማችን ሊሆን ነው። ከዚያም ያሰብነውን ነገር አግኝተነው ከጨበጥነው በኋላ እግዚአብሔር ለእሱ እንድናደርግለት የሚፈልገው ነገር እንዳለ ካሰብን ለማድረግ ፈቃደኛ አንሆንም። አንዲት ሴት፣ "ላደርገው የምፈልገው ነገር ስህተት እንደሆነ አውቀዋለሁ፣ ነገር ግን ምንም ቢሆን አሁን አደርገዋለሁ። እግዚአብሔር ይቅር ይለኛል፣ ይቅርታ አያደርግልኝም?" በማለት ደብዳቤ ጽፋልኛለች።

እነዚህ ሀሳቦች በሙሉ መለኪያውን የሳቱና በመንፈሳዊ ረገድ እደገኛ ናቸው። እግዚአብሔር ማን እንደሆነና ለኛ ምን ያህል በጥልቀት እንደሚጠነቀቅልን የማያገናዝቡ ናቸው። ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመግለጽ ከምፈልጋቸው እውነቶች መካከል አንዱና ዋናው የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ፍቅር መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ባይወደን ኖሮ፣ በውሳኔአችን ምክንያት ስለሚገጥመን ችግር ግድ አይልም ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ይወደናል - ልዩ የሚያደርገውም ይህ ነው። እርሱ ስለሚወደን፣ ፈቃዱ ለኛ ሁልጊዜ የተሻለ ስለሆነ፣ ሁልጊዜ መልካም ስለሆነ በፍጹም መተማመን ልንፈልገው እንችላለን። ከሁሉም በላይ፣ እኛ የዘላለም ድነት እንድናገኝ ልጁን ወደ ዓለም በመላክ ስለ

ኃጢአታችን እንዲሞት አስከማድረግ ከወደደን እንዴት ስለ እኛ ስለ ነገአችን አይጠነቀቅልንም? እንዴት አይወደንም እንላለን? መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "እግዚአብሔር ለአንድ ልጁ ሳይራራ ስለኛ አሳልፎ ከሰጠው፣ ከልጁ ጋር ሁሉን ነገር እንደሚሰጠን እርግጠኞች ነን" (ሮሜ 8፥32)።

አግዚአብሔር ይወዳችኋል፤ ስለሚወዳችሁም፣ ለሕይወታችሁ ዘላለማዊ ዕቅድ አለው። ምንም ነገር ፈቃዱን እንዳትፈልጉ እንዲያደርጋችሁ አትፍቀዱለት።

የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁለቱ ገጽታዎች (አቅጣጫዎች)

የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት አናውቃለን? የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎች ይህን ጥያቄ ሁልጊዜ በብዙ ክርስቲያኖች እንደሚጠየቁ ይነግሩናል። ጥያቄው የሚቀርብላቸው ከጥሩ ምክንያት ጋር ነበር። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማወቅ የበለጠ ሌላ የተሻለ ነገር ሊኖር ይችል ይሆን?

ከሁሉ አስቀድመን የእግዚአብሔር ፈቃድ ባለሁለት አቅጣጫ እንደሆነ በርግጠኝነት ልንገነዘብ ይገባናል። *አንደኛ፣ እግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ ወይም አጠቃላይ ብለን የምንጠራው ፈቃድ አለው*፤ የእግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ ፈቃድ ለሰው ልጆች ሁሉ የተሰጠ ነው። ይህን የእግዚአብሔርን ዓለም አቀፋዊ ፈቃድ ሞራላዊ (ከብረ ሀሊናዊ) ፈቃድ ብለን ልንጠራው እንችላለን፣ ምክንያቱም ይህ ፈቃድ ጉዳይ ያለው ከኛ ሥነ - ምግባራዊ ጠባይና ሞራል ጋር በመሆኑ ነው።

የእግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ ፈቃዱ ከሰው ሰው የሚለዋወጥና የተለያየ አይደለም፤ በእኔ ላይ እንደሆነ አንዲሁ በናንተ ላይ ተመሳሳይ ነው። ለምሳሌ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁላችንም ሕይወታችንን ለኢየሱስ ክርስቶስ አንድንሰጥና አምነን እንድንከተለው ነው። እንደዚሁም የእግዚአብሔር ፈቃድ ኃጢአት ማድረግን እንድንተው ነው፤ እንድንዋሽ፣ ወይም እንድንሠርቅ ወይም ዝሙት እንድንፈጽም ወይም እንድንገድል ወይም እንድንመኝ ወይም ንፋጉች እንድንሆን ከቶ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። እነዚህ ነገሮች ሁላችንንም አይመለከቱምን? በእርግጥ ይመለከቱናል፣ ምክንያቱም አነዚህ ሁሉ የመጡት ከዐስርቱ ወርቃማ ትዕዛዛት ውስጥ ናቸው (በዘፀአት 20 እና በዘዳግም 5 ላይ ታገኙአቸዋላችሁ)።

የእግዚአብሔርን ዓለም አቀፋዊ ፈቃድ - ለሁሉ ሰው (እናንተንና እኔን ጨምሮ) የሆነ ፈቃዱን እንዴት እናውቃለን? ትክክለኛ መልስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አናገኛለን። በእርግጥ፣ እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስን ለእኛ የሰጠበት አንዱ ምክንያት የእርሱን ፈቃድ አናውቅ ዘንድ ነው፤ "ቅዱስ መጽሐፍ በሙሉ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፈ ነው፣ እርሱ እውነትን ለማስተማር፣ የተሳሳቱትን ለመገሰጽ፣ ስህተትን ለማረምና ለትክክለኛ ኑሮ የሚበጀውን መመሪያ ለመስጠት ይጠቅማል" (2ጢሞ 3፥16)። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ወጣቶች ሕይወታቸውን በንጽሕና መጠበቅ የሚችሉት ትዕዛዛትህን በመፈጸም ነው" ይላል (መዝ 119፥9)።

እንዳንድ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ልንከተለው የሚገባ ግልጽና ልዩ የሆነ መመሪያ ይሰጠናል። መክፈል የሚገባንን ቀረጥ በማታለል አለመክፈል ስህተት ስለ መሆኑ እግዚአብሔርን መጠየቅ የለብንም፤ ምክንያቱም አርሱ አስቀድሞ፣ "ያለባችሁን ግዴጅ ፈጽሙ፤ ግብር ለሚገባው ግብርን፤ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን ክፈሉ" በማለት እዞናል። ወይም ደግሞ ለትዳር አጋሮቻችን ታማኝ አለመሆን ስህተት ነው ወይስ አይደለም ብለን እግዚአብሔርን መጠየቅ ተገቢአችን አይደለም፤ ስለዚህ ጉዳይ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ በጣም ግልጽ ነው፤ ስለዚህ ከዝሙት ራቁ (1ቆሮ 6፥18) ብሎናል። አግዚአብሔር በፍጹም - ደግሞም በፍጹም - ቃሉን፣ መጽሐፍ ቅዱስን፣ የሚቃረን ነገር እንድታደርጉ አይመራችሁም።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ልዩ መመሪያ ብቻ አይደለም የሚሰጠን። እንድንመራበት ሞራላዊና መንፈሳዊ የሆኑ በጣም ጠቅለል ያሉ (አጠቃላይ) መመሪያዎችንም ጨምሮ ይሰጠናል። ኢየሱስ ክርስቶስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካሉት ህጎች ሁሉ የሚበልጠው የትኛው እንደሆነ በተጠየቀ ጊዜ ሁለት መመሪያዎችን መሠረት በማድረግ፣ "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኃይልህ፣ በፍጹም አሳብህም ውደድ፤ ባልንጀራህንም እንደራስህ ውደድ" አለው (ሉቃስ 10፥27)። እነዚያን መመሪያዎች በትክክል የምንከተላቸው ቢሆን ኖሮ ምድራችን አሁን ካለችበት ሁኔታ የበለጠ እንዴት የተሻለች በሆነች ነበር!

"ለእግዚአብሔር ቃል ጭፍን ከሆንክ፣ ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ጭፍን (ደንቆሮ) ትሆናለህ" የሚል አባባል

ለመጀመሪያ ጊዜ መቼ እንደለማሁት ባላስታውስም በጭራሽ እልረሳውም። እግዚአብሔር ስለ ሕይወታችን ያለውን ፈቃድ በተመለከተ ላሉን ብዙ ጥያቄዎቻችን መልስ የሰጠን ቢሆንም እልሰማነውም፣ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስን ስለማናውቅ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በምናውቅበት ጊዜ መመሪያዎቹና ምክሮቹ ለውሳኔዎቻችን እንደ ማጣሪያ ያገለግላሉ፣ እግዚአብሔርም ስህተት የሆነውን ነገር ለማስወገድ ውስጣዊውን ማጣሪያ ይጠቀምበታል። መጽሐፍ ቅዱስን የዕለት ተዕለት ሕይወታችሁ አካል እድርጉት፣ በተጨማሪም እግዚአብሔር በነፍሳችሁ ውስጥ የቃሉን እውነት እንዲተገብር ለምኑት።

ለየግል የእግዚአብሔር ፈቃድ

እግዚአብሔር በሁሉም ላይ ተፈፃሚ የሚሆን ዓለም አቀፋዊ ፈቃድ ብቻ እይደለም ያለው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ባለሁሉት እቅጣጫ ነው እንዳልነው፣ *ሁለተኛው ፈቃዱ ለግለሰብ (ለየግላችን) ያለው ፈቃድ ነው*። ከዓለም አቀፋዊው ፈቃድ በተቃራኒ ግለሰባዊ የሆነው ፈቃድ ከሰው ሰው የሚለያይ ነው። በሌላ አነጋገር፣ እግዚአብሔር ለኔ ለግሉ ያለው ፈቃድ ለእንተ ወይም ለእንቺ ካለው ፈቃድ ይለያል። እግዚአብሔር ከጀርባችን ተቀምጦ ሕይወታችንን በዘፈቀደ ለንመራው ዝም ብሎ የሚያየን አይደለም፣ ለእያንዳንዳችን ምን እንደሚበጀንና እንደሚሻለን ያውቃል፣ ስለዚህ በሕይወታችን ታላቅ የሆነ ደስታ የሚመጣው እርሱ ለኛ ያለውን አቅድ ስናውቅና ስናደርግ ነው።

በሕይወቴ ካጋጠመኝ የደስታ ቀኖች ውስጥ አንዱ ሩት የጋብቻ ጥያቄዬን መቀበሏን የገለጸችልኝ ቀን ነው። ደስታዬን ልቆጣጠረው አልቻልኩም ነበር። ነገር ግን ይህ ከመሆኑ ከጥቂት ዓመታት በፊት ክገጠመኝ አሳዛኝ ቀኖች ሁሉ የበለጠ አንድ ደዘንክበት ቀን ገጥሞኛል። ካንዳት ላገባት እስባት የነበረችው በጣም ቆንጆ ወጣት ጋር የነበረን ግንኙነት በድንገት ተቋርጧል፣ በዚህም ልቤ በጣም ተሰብሮእል ልቤ የተሰበረው ስህተት እንደሠራች በማመን ነበር - ነገር ግን እግዚአብሔር ለእኔ ከእኔ እጅግ በጣም የተሻለውን ያውቅ ነበር። ሩት ለኔ የእግዚአብሔር ምርጫ ነበረች (ልክ እኔን ለርሷ እንደመረጠላት)፣ ስለዚህ እኔ ሁል ጊዜ እግዚአብሔር ለያንዳንዳችን የሚበጀውን በመምረጥ ስላደረገልን ማዳኑና መልካም እሠራሩ አመሰግነዋለሁ።

እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን ግላዊ (ግለሰባዊ) እቅድ አለው። ይህ የእግዚአብሔር ታላቅ ዕቅድ በሕይወታችን ውስጥ ታላላቅ ጉዳዮችን የሚያቅፍ ነው። ማንን እንደምናገባ፣ ምን እንደምንሠራ፣ የት እንደምንኖር፣ ሌላው ቀርቶ መቼ እንደምንሞት ሁሉ ማለት ነው። ዕቅዱ በተጨማሪ የዕለት ተዕለት ኑሮ ዝርዝርን ያቅፋል፣ ስለ ቤተሰባችን፣ ስለ ገንዘባችን አወጣጥ፣ ስለ መዝናኛ ሰዓታችን፣ ክጓደኞቻችን ጋር ስለምናደርገው ግንኙነትና የመሳለሉትን ሊቆጠሩ በማይችሉ ጉዳዮች ላይ የምናደርገውን ምርጫና ውሳኔ ይጨምራል። ለሁሉም ነገሮቻችሁ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየፈለጋችሁ ነው? መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ስለ እናንተ ያለኝን ዕቅድ የማውቅ እኔ ብቻ ነኝ፣ ይህም ዕቅድ ክፋትን ሳይሆን ሰላምን በማስገኘት እናንተ በተስፋ የምትጠብቁት መልካም ነገር የሚፈጸምበት ነው" (ኤር 29፥11)።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ

በተጨባጭ (በትክክለኛ) ሁኔታ ላይ ተንተርሶ የሚቀርብ ጥያቄ ይህ ነው፣ ከባድ ውሳኔ የሚጠይቅ ጉዳይ ሲገጥመንና ለንፋጠጥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት ልናውቅ እንችላለን? እስኪ ጠቃሚ ሆነው ያገኘኋቸውን ስድስት መመሪያዎችን ልሰጣችሁ።

አንደኛ፣ ውሳኔአችሁን ለእግዚአብሔር ስጡ። መደበኛ የሆነ የጸሎት ጊዜ መድቡና እግዚአብሔር እንዲመራችሁና ፈቃዱንም እንዲያስታውቃችሁ ጠይቁት። የምትፈልጉትን ጥበብና ዘዴ እንዲሰጣችሁ ለምኑት፣ ፈቃዱን እየተቃወማችሁ እንደሆነም እንዲያሳያችሁ ጠይቁት። እድርጋችሁ ከሆነም፣ ንስሃ ግቡ፣ በፈቃዳችሁ ላይ ክርስቶስ ጌታ እንዲሆን አስረክቡት። የመዝሙረኛው ፀሎት የናንተ ይሁን፣ "እግዚአብሔር ሆይ እንተ የምትፈልገውን ነገር ማድረግን አስተምረኝ፣ እኔም በታማኝነት እታዘዛለሁ፣ በፍፅም ቅንነት እንዳገለግልህ አስተምረኝ" (መዝ 86፥11)።

እንዳለመታደል ሆኖ ይህን የመጀመሪያውን ደረጃ ለመግደፍ (ለመሳት) በጣም ቀላል ነው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንፈልጋለን እንላለን - ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲመራን መጠየቁንም ሳናቋርጥ፣ በችኮላ ለመወሰን በመፍጨርጨር በየእቅጣጫው እንሯሯጣለን። ወይም አንዳንድ ጊዜ የተሻለው መንገድ የትኛው

እንደሆነ አውቀናል ብለን እናስባለን፣ እግዚአብሔር ሰኛ ያለው እቅድ ግን ሌላ ነው። ይህ በናንተ ላይ እንዲሆን አትፍቀዱ፣ ማንኛ ውንም ውሳኔ ለእግዚአብሔር ስጡ። ሲጀመር ብቻ ሳይሆን እስክመጨረሻው ሂደት ስርሱ ፍቀዱለት።

ሁለተኛ፣ መጽሐፍ ቅዱስን መርምሩ። ውሳኔና ምርጫ ስሚያስፈልገው ስማናቸውም ጉዳያችሁ መጽሐፍ ቅዱስ ቀጥተኛ የሆነ መመሪያ አለው? እናንተ ላሳችሁበት ሁኔታ የሚስማማ መመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ? እንደኔ ዓይነት ችግር ያጋጠመው ሰው ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ? ካለስ እንዴት ተወጣው? (አንዳንዶች ከፈፀሙት የስህተት ውሳኔ እንኳን ሰመማር እንችሳለን)። አስቀድመን ምን አንደተነጋገርን አስተውሉ፣ እግዚአብሔር ቃሉን (መጽሐፍ ቅዱስን) የሚቃረን ማናቸውንም ነገር እንድንፈጽም ከቶ አይመራንም።

ሶስተኛው፣ በአካባቢያችሁ ያሉትን ሁኔታዎች አወቁ። እግዚአብሔር የሚሠራው በእኛ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአካባቢያችንም ይሠራል። እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሚመራን በአካባቢያችን ባለው ሁኔታ እማካይነት ነው። ለምሳሌ፣ እግዚአብሔር አንተን/ አንቺን ልዩ አድርጐ ፈጥሮአል፣ እርሱ ያላችሁን ችሎታና የችሎታችሁን ውስንነት አንድታውቁ ይፈልጋል። እግዚአብሔር አንድ ነገር አንድንሠራ ወይም አንድፈጽመው ሰመፈፀም የምንችልበትን ችሎታና ብቃት ሳይሰጠን አያዘንም ወይም ደግሞ እግዚአብሔር የርሱን ፈቃድ ስንፈልግ እግዚአብሔር የዕድሎችን በር በመክፈት ወይም በመዝጋት ይመራናል። በተጨማሪ እግዚአብሔር ውሳኔ በምናደርግበት ጊዜ በጥበብና በዘዴ እንድናደርገው ይፈልጋል። ውሳኔ ስናደርግ ውሳኔዎቹ ሊያመጡ የሚችሉትን ውጤት አስበናል (መዝነናል)? ያሉንን አማራጮችና ችሎታዎች ፈትሸን የትኛው አማራጭ የተሻለ ውጤት ሊያስገኝልን እንደሚችል አይተናል?

ዐራተኛ፣ አምላካዊ (በጐ) ምክር ፈልጉ። እግዚአብሔር ለአንዳንድ ሰዎች ልዩ የጥበብ ስጦታ ሰጥቷል፣ ስለዚህ ለመወሰን ስንቸገር፣ የነዚህን ሰዎች ምክር መፈለግ ይረዳል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤ "መልካምን ምክር ብትቀበል ሁሉ ነገር ይሳካልሃል፡- ምክርን ባትቀበል ግን ምንም ነገር አይሳካልህም" (ምሳሌ 15÷22)። እነዚህ ሰዎች ሁኔታችሁን ተረድተው እንዲረዱአችሁ እግዚአብሔር

የሚጠቀምባቸው ቢሆንም፣ የሚሰጡንን ምክር በጥንቃቄ ልንመዝነው ይገባናል።

በዓመታት አገልግሎቴ በፈቃደኛነት ጥበባቸውንና ልምዳቸውን በማካፈል ላልተሰዩኝና ለረዱኝ ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን ሁልጊዜ አመሰግነዋለሁ። የነዚህ ሰዎች ምክር እጅግ አስፈላጊ ሲሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመለየት ረገድ በብዙ ረድቶኛል።

አምስተኛ፣ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ታመኑ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ በእውነትና በታማኝነት ስንፈልግ፣ እግዚአብሔር የፀና ውስጣዊ እምነት ወይም በየትኛው አቅጣጫ መሄድ እንዳለብን ፍንጭ ይሰጠናል፣ ይገፋፋናልም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "ከመንገድ ወጥታችሁ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ ብትባዝኑ ከበስተኋላችሁ፣ 'ትክክለኛው መንገድ ይህ ነው፣ በዚህ ሂድ' የሚለውን ድምጽ ትሰማላችሁ" (ኢሳ 30÷21)።

የሚያበረታታው (የሚያደፋፍረው) ድምጽ የሚመጣው፣ ክርስቶስን ብናውቅ በውስጣችን ከሚኖረው ከቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። ኢየሱስ፣ "የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል" (ዮሐ 16÷13) ብሏል። ይህ የፀና ውስጣዊ እምነት ስሜት እይደለም፣ እግዚአብሔር እኛን የሚመራበት የተረጋጋ ሰላም የተሞላ እርግጠኛ መንገድ ነው።

መንፈስ ቅዱስ ተለይቶ (ብቻውን) አይሠራም። ስለሆነም፣ የራሳችንን መሻት ከመንፈስ ቅዱስ ማበረታቻ ጋር አንዳናደበላልቅ (አንዳናወነባብድ) ልንጠበቅ ያስፈልጋል። መጸለይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት፣ አካባቢያችንን መፈተሽ፣ እና አምሳካዊ ምክር መፈለግ ያስፈልገናል። እግዚአብሔር ወደ መጨረሻው ውሳኔ ወይም ግብ እንድንደርስ ሁልጊዜ በውስጣችን ያደፋፍረናል።

በመጨረሻም፣ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን በእግዚአብሔር ታመኑ። እግዚአብሔር እንድትወስኑ ከመራችሁ በኋላ ወደኋላ አትበሉ። ይልቁንም፣ በምሪቱ ታመኑ፣ ክፉታችሁ ቀድሞ እንደሚወጣ እመኑ - እርሱ ያደርጋል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እንደመራን እርግጠኛ የምንሆነው ውሳኔ ካደረግን በኋላ ነው፤ ነገር ግን በእውነት የርሱን ፈቃድ የምንፈልግ ከሆነ፣ መንገዱ ግልጽ ባይሆን እንኳን እርሱ ሲመራን ተስፋ ስጥቶናል።

ስለግል ሕይወቱ እግዚአብሔር ስላለው ፈቃድ በሺዎች የሚቆጠሩ ጥያቄዎች ያሉት የሚመስል የማውቀው ወጣት ነበረ። ስለገዳዩ ከማንም ጋር ብዙ ሰዓታትን ይነጋገራል፤ ከሚገናኘው ሰው ሁሉ ምክር ይቀበላል፤ ብዙ ሰዓታትን በመናገር ያባክናል፤ ነገር ግን ከቶ ወደ ውሳኔ መድረስ አልቻለም።

ጊዜያችሁ እያለቀ እያያችሁ ከኋላ በመቀመጥ ዝም ብላችሁ ታላቅ መገለጥ (ራዕይ) ወደ እኛ ይመጣል ብላችሁ አትጠብቁ። ጊዜአችሁንም አታባክኑ። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሔ ሊሆን ይችላል ብላችሁ ባሰባችሁበት እቅጣጫ ጉዞአችሁን መጀመር የበለጠ ጥሩ ሊሆን ይችላል፤ እየተጓዛችሁበት ያለው መንገድ እርሱ የማይፈልገው ሆኖ ቢዘጋና ሌላ መንገድ በሚከፍትበት ጊዜ በአመራሩ ታመነበት። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን እንጂ በራስህ እውቀት አትደገፍ፤ በምታደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን አስቀድመው፤ እርሱም በትክክለኛው መንገድ ይመራሃል" ይላል (ምሳሌ 3፡5-6)።

አስተውሉ፤ እግዚአብሔር ይወዳችኋል፤ ፈቃዱንም ታውቁ ዘንድ ይፈልጋል። ፈልጉ ... እወቁ ... እናም ፈጽሙ። የርሱ መንገድ ሁልጊዜም ተወዳዳሪ የለውም።

ሃያ አምስት

ስተሻለው ወይም ስከፋው

ሰው ስለቱንና ስናቱን ተቶ ከሚስቱ ጋር የሚተባበረው ለስዚህ ነው፤ ሁለቱም ስንድ ይሆናሉ

(ዘፍ፡ 2፡24)

ከመልካም ጋብቻ የበለጠ ደስታን የሚሰጥ እንደሌለ ሁሉ፤ መጥፎ ጋብቻ ከማያመጣው ስቃይ የበለጠ የለም።

ወደ ኋላ መለስ ብዬ ስመለከተው በወጣትነት ጊዜዬ ስለጋብቻ ትልቅ ስፍራ ስጥቼ እስብ እንደነበረ አስታውሳለሁ፤ ነገር ግን ማግባት ማለት በእርግጥ ምን ማለት እንደሆነ ብዙም አላስብም ነበር።

አንድ ቀን አንድ ሰው በኮሌጅ የመጨረሻውን ዓመት ትምህርቴን ስማር እኖርበት ወደነበረው ቤት እየነዳ መጣ። በአቅራቢያችን የምትገኝ የአንዲት እነስተኛ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን ነበር። "በማኅበረ - ምዕመናኑ የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ እንድትሆንላቸው በማሰብ ሊያነጋግሩህ ይፈልጋሉ" ብሎ ነገረኝ። በዚያ ዓመት ውስጥ በብዙ ቤተክርስቲያኖች እየተጋበዝኩ በመደበኛ ነት እየተገኘሁ እስብክ ነበር፤ ከነርሱ እንዳንዶቹ ስብከት እዳምጠው እንደ ነበር አስባለሁ። ከቤተክርስቲያኒቱ ወገኖች ጋር ስለተፈለግኩበት ጉዳይ ከተነጋገርንበትና ከጸለይንበት በኋላ ግብዣቸውን ተቀበልኩ።

ይህን ውሳኔ ባሰላሰኩበት ጊዜ ብቸኛው ችግሬ ልክ ትምህርቴን እንዳጠናቀቅኩኝ (እንደተመረቅኩ) ከሩት ጋር ወዲያውኑ ለመጋባት ቃል መግባታችንን መርሳቴ ነበር - መጋቢ ስመሆን ጥሪውን ስቀበል ሩትን ማማከር ይገባኝ እንደነበር በጭራሽ አረስቼው ነበር። ውሳኔዬ እኔን እንደረበሸኝ እርሷንም ረበሻት።

ውሳኔው የጋራ እንጂ የግሌ ብቻ መሆን አልነበረበትም። ወዲያውኑ አሷ አኔን ግዴለሽ እንደሆንኩ አድርጋ እንደቆጠረችኝ አንዳውቅ እደረገችኝ፣ በዚህ ምክንያት በመበሳጨቷም ልወቅሳት እልቻልኩም። መማርና ማሰላሰል ጀመርኩ - ቀስ በቀስም መፍራት ጀመርኩ - ጋብቻ አንዲያው በቀላሉ የእርስ በርስ ግንኙነትን ወይም ወዳጅነትን በመመስረት ከመደሰት ያለፈ ነው። ብዙ ብዙ ነገር በውስጡ አለ። ከስድሳ ዓመታት ትዳር በኋላም አሁንም እየተማርኩ ነው።

ጋብቻ፡- የእግዚአብሔር ስጦታ ነው

ጋብቻ ምንድን ነው? ከሁሉም በበለጠ ስለ ጋብቻ ልንረዳው የሚገባን እስፈላጊ እውነት፣ *እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን ስጦታ መሆኑን ነው*። ጋብቻ በእግዚአብሔር የተሠራ ነው፣ በእኛ አይደለም። ማኅበረሰብ የመሰረተው አይደለም፤ እግዚአብሔር የመሰረተው ነው። ኃጢአት ወደ ዓለም ከመግባቱ ከብዙ ዘመን በፊት እግዚአብሔር ወደ አዳም ተመለከተና እንዲህ አለ፣ "ለው ብቻውን መኖሩ መልካም አይደለም፤ ስለዚህ ተስማሚና ረዳት ጓደኛ አፈጥርለታለሁ" (ዘፍ 2፥18)።

እግዚአብሔር ይህን አለካለበት ነጥብ ድረስ የፈጠራቸውን ነገሮች ሁሉ "መልካም" ብሏል። አሁን ግን አንድ ነገር - የአዳም የብቸኝነት ሁኔታ - መልካም እንዳልሆነ አሳወቀ። ምንም እንኳ አዳም ከእግዚአብሔር ጋር ያልተገደበ ህብረትና ግንኙነት የነበረው ቢሆንም ያ በቂ አልነበረም። አዳም ሕይወትን የሚገራው ሌላ ለው ያስፈልገው ነበር - ስለዚህ እግዚአብሔር ሔዋንን ፈጠረለት። የመጀመሪያው ሰርግ የተዘጋጀው በእግዚአብሔር በኤደን ገነት ውስጥ ነበር። ጋብቻ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ ጋብቻ የምንባረክበትና ፍጹም የምንሆንበት መንገድ ነው።

ጋብቻ፡- ስሕብሮነት ነው

እግዚአብሔር ጋብቻን የሰጠን ለምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ምክንያቶችን ይሰጠናል። ከነዚህ ዋንኛው፣ እግዚአብሔር *ጋብቻን የሰጠን አብሮ ለመሆን (ለአብሮነት) ነው*። እግዚአብሔር አዳምን የእንስሳት ሠራዊት ሁሉ ስም እንዲያወጣላቸውና እንዲቆጣጠራቸው ሲነግረው፡- "ለአዳም ግን ተስማሚና ረዳት ጓደኛ ገና አልተገኘለትም ነበር" (ዘፍ 2፥20)። አዳም የተሠራው በእግዚአብሔር አምሳል ነው፣ ልክ ፍቅር

የእግዚአብሔር ባሕርይ አካል እንደሆነ፣ ፍቅር የአዳምም ባሕርይ አካል ነበር። አርሱ ሊወደው የሚገባው እንድ ለው ደስፈልገው ነበር፣ በምላሹም አርሱን የሚወድ ለው ይፈልግ ነበር። ብቸኝነቱን የሚያርቅለትና ሙሉ የሚደደርገው እንድ ለው ብቻ ነበር።

እንዳንድ ለዎች "ሚስቴ/ባሌ ከሁሉ ይበልጥ ጓደኛዬ ናት/ነው" በማለት ሲናገሩ ስለማ ሁልጊዜ እበረታታለሁ። ለብዙ ዓመታት እኔ በማደርገው ረጅም ጉዞ ምክንያት ከሩት ጋር ረጅም ቀናት ተለያይተን እንቆያለን፣ አንዳንድ ጊዜም በጣም ረኽርም ለሆነ ጊዜ ለመቆየት ጉዞዬን ስጀምርና ልክ ቤቴን ለቅቄ የምሳፈርበትን ባቡር ወይም አውሮፕላን እንደያዝኩ አይኖቼ እንባ ያመነጫሉ። አሁን በእርጅና እድሜያችን እንድ ላይ ሆነን፣ ትልቁ ደስታችን የሆነው አብረን መሆናችን ነው። ቃላት ሳንለዋወጥ በጸጥታ ሆነን በተቀመጥንበት እጅ ለእጅ በመያያዝ፣ አብረን ቴሌቪዥን በማየት፣ በህብረት ሆነን በመጸለይና የእግዚአብሔርን ቃል በመከፋፈል በእብሮነታችን እንደለታለን። አብሮ በመሆን የሚገኘውን የደስታ ጥልቀት ተገንዝበናል።

እግዚአብሔር ጋብቻን የመሰረተበት ሌላው ምክንያት ደግሞ በጋራ በመሆን እንድንረዳዳና እንድንበረታታ ነው። ሔዋን ለአዳም "ተስማሚ" ወይም "በቂ" እንድትሆን ነበር። ሔዋን ለአዳም ባሪያው ወይም አገልጋይ አልነበረችም። ነገር ግን የእግዚአብሔርን እደራ (የማስተዳደር ኃላፊነት)፣ "ብዙ ተባዙ ዘራችሁ ምድርን ይሙላ፣ ምድርም በቁጥጥራችሁ ሥር ትሁን" (ዘፍ 12፥8) ብሎ የለጠውን በተሳካ ሁኔታ እንዲያሚላ የምታግዘው ረዳቱ ነበረች።

አዳም ከእግዚአብሔር የተሰጠውን እደራ ብቻውን መወጣት አይችልም ነበር። ለአዳም ሔዋን ታስፈልገው ነበር - ሰሔዋንም አዳም ደስፈልጋት ነበር። በመካከላቸው አንዳቸው በአንዳቸው ላይ የመበላለጥና የበታች ወይም የበላይ አልነበረም። እርስ በርስ የሚፈላለጉና አንዱ በሌላው ላይ ጥገኛ ነበሩ። ባለትዳሮች ተለያይተው ላይ በጣም አዝናለሁ። የማይከባበሩና የሚናናቁ ጥንዶች ያሳዝኑኛል። ባል ወይም ሚስት የትዳር አጋራቸውን ሲተቹ ወይም ሲሰድቡ ወይም ሲያንቋሸሹ መስማት አሳዛኝ ነው። ለእርስ በርሳችን የማደቋርጥ መረዳዳትና ማበረታታት ያስፈልገናል።

ጋብቻ፦ ሰደሰታ የተሠሪ ነው

በተጨማሪ፣ እግዚአብሔር ጋብቻን የሰጠን ሊጋራ ደስታና መዝናናት ነው። እግዚአብሔር ለአዳም ሔዋንን ሲያመጣለት ምን ይህል እንደተደሰተ ማሰብ ትችላላችሁ፣ ደስታውን የገለጸው በታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን የፍቅር ቅኔት በመቀኘት ነበር፣ "እርስዋ ክአጥንቴ የተገኘች አጥንት ናት፣ ከሥጋዬ የተገኘች ሥጋ ናት" (ዘፍ 2፥23)። እግዚአብሔርም፣ በአካል ቢሆን፣ በመንፈስ ቢሆን፣ በስሜት ቢሆን፣ በአእምሮ ቢሆን አንዱ ሰሌላው የደስታ ምክንያት እንዲሆኑ ይፈልጋል።

ሌላው እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ የሰጠን ተጨማሪ ስጦታ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ነው። እግዚአብሔር በጋብቻ ውስጥ ከሰጠን ሰጦታ ሁሉ እንደ ግብረ ሥጋ ግንኙነት የማስደሰት አቅም ያሰው ምንም ነገር የለም፣ በተቃራኒው ደግሞ በዘመናት ሁሉ በኃጢአት የታወክና የተጠመዘዘ እንደ ግብረ ሥጋ ግንኙነት የመሰሰ ነገር የለም። እግዚአብሔር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሰጦታ የሰጠን የሰው ልጅ ዘር ቀጣይነት እንዲኖረው (ምንም እንኳ በጣም አሰፈላጊ ቢሆንም) ብቻ አይደለም። የግብረ ሥጋ ግንኙነት በእግዚአብሔር የተሰጠው የባልና የሚስት የጠሰቀ የፍቅር መግለጫ እንዲሆን ነው። በዚህ ምክንያት፣ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም ያለበት በጋብቻ ቃል ኪዳን ክልል ውስጥ ብቻ ነው፣ "ወንድ እናቱንና አባቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር የሚተባበረው ሰዘህ ነው፣ ሁለቱም አንድ ይሆናሉ" (ዘፍ 2፥24)። የግብረ ሥጋ ግንኙነት በባለትዳሮቹ መካከል የአንድነታቸው ምልክትና እስከ ሞት የሚዘልቅ የቃል ኪዳን ማህተም እንዲሆን የታሰበ ነው።

እግዚአብሔር በግብረ ሥጋ ግንኙነት ንጽህናና ታማኝነት እንዲኖር የሚጠይቀን እንድንሰቃይ ሳይሆን የበለጠ ደስተኛ እንድንሆን ስለሚፈልግ ነው። እግዚአብሔር ከእኛ የበለጠ ከጋብቻ ውጪ የምንፈጽመው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ምንጊዜም የርሱን ፍጹማዊ ዕቅድ የጣለና የልብ ሰብረትንና አለመተማመንን እንደሚያስከትልብን ያውቃል። አንድ ሰው ከጋብቻ በፊት ሌሰኛ (ልክሰክሰ) ቢሆን፣ በጋብቻ ጊዜ ከትዳር ጓደኛ ጋር እርግጠኛ የሆነ መተማመን ሊኖር ይችላል? አንድ ወንድና ሴት እንዲያው ዝም ብለው በእንድነት ቢኖሩ፣ ሁልጊዜ አንድ ነገር ጎደሰ" ነው፣ *አሰም መሰጣጣት ነው።* እስከ ሞት የሚዘልቅ በእርስ በርሳቸው መካከል የመሰጣጣት ቃል ኪዳን ሰሰሰ፣ ግንኙነታቸው ሁልጊዜ

ያልተረጋጋና የሚያስተማምን ዋስትና የሌለው ይሆናል። የሚያምነው ዓለም "የወሲብ ነፃነት" ብሎ የሚጠራው ይህ የወረደና አሳፋሪ ተግባር በትክክል የወሲብ ነጻነት ሳይሆን የወሲብ ባርነት ነው - በራሳችን መሻት ላይ የጫንነው ባርነት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ በማለት ያስጠነቅቃል፣ "ልብስህ ሳይቃጠል እሳት በጉያህ ይዘህ መሔድ ትችላለህን? እግርህስ ሳይቃጠል የእሳት ፍም ረግጠህ መቆም ትችላለህን? ከሌላ ሰው ሚስት ጋርም መተኛት የዚያኑ ያህል እደገኛ ነው፤ ይህን የሚያደርግ ሁሉ ክመቀጣት አያመልጥም" (ምሳ 6፥27-29)።

ጋብቻ ፦ ቤተሰብ መሆን ነው

እግዚአብሔር ሰኛ ጋብቻን የሰጠበት ትልቁ ምክንያት ቀጣይነት ያለው ቤተሰብ እንዲኖርና ለቤተሰቦቻችን ደህንነት በማለብ ነው። ክተሰጠን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ተያይዞ ሌላ መለክታዊ ስጦታ ተጨምሮልናል፤ እሱም የልጆች ስጦታ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ልጆች ክእግዚአብሔር የሚገኙ ስጦታዎች ናቸው፣ እውነተኛም በረከት ናቸው" (መዝ 127፥3) ይላል።

ነገር ግን ልጆች ኃላፊነት የሚለማቸውና የበለሰ ሆነው ማደግ እንዲችሉ መመሪያና ፍቅር ይፈልጋሰ። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ለሰው ዘር ባለው እቅድ መሠረት ደህንነቱ በሚያስተማምን ቤተሰብ ውስጥ መፈፀም ያለበት ነው። ልጆች በተሻለ ሁኔታ በሳል ሆነው የሚያድጉት በተረጋጋና ፍቅር በተላበሰ ቤተሰብ ውስጥ እንደሆነ እግዚአብሔር ያውቃል፤ እግዚአብሔር ጋብቻን ለእኛ ከሰጠበት ምክንያት አንዱ ይህ ነው። ባሎችና ሚስቶች ሰራሳቸው ብቻ እንዲኖሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም፤ ለልጆቻቸው ደህንነት ጭምር ሊኖሩ ይገባቸዋል።

በተበላሸና ፈሩን በሳተ በዚህ ዓለም ውስጥ ቤተሰቦቻችን ከዚህ ተስማሚ ስጦታ ሊርቁ እናያለን። በፍቺ፣ በስደብ፣ በቸልተኝነት፣ በድህነት፣ በአልኮል ሱሰኝነት፣ በቤተሰብ ብጥብጥ፣ በትዳር ጓደኛ ሞት ምክንያትና በነዚህና በሌሎች ችግሮች የቤተሰቦች መፍረስ የውድቀታችን አሳዛኝ ጠቋሚዎች ናቸው።

ምናልባትም እናንተ ራሳችሁ ከነዚህ በአንዱ ችግር ውስጥ አያሰፋችሁ ልትሆኑ ትችላላችሁ፤ ለለዚህ በዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ ካላችሁ፣ ሊረዷችሁ የሚችሉ ሰዎችን ለመፈለግ (ለማግኘት) ክመጣር አታመንቱ። (እንደ መጋቢያችሁ ወይም በዚህ ጉዳይ ላይ

የማማከር ሥልጠና ያለውን ሰው ማለት ነው።) እንደዚሁ ዓይነት ችግሮች ውስብስብ ናቸው፣ በራሳችሁ አቅም ለመቋቋም እጅግ ከባድ ሊሆኑባችሁ ይችላሉ፣ ወይም ካደረሱባችሁ ጉዳት ለማገገም ከብዶአችሁ ይሆናል። ነገር ግን እግዚአብሔር በምን ዓይነት ችግር ውስጥ እያለፋችሁ እንደሆነ እንደሚያውቅና በፍቅሩና በጥበቡ ዙሪያችሁን እንደሚከብብ ከቶ አትዘንጉ። ከዚህ በተጨማሪ የእግዚአብሔር ጥበብና ፍቅር ያላቸው ሌሎች ሰዎች በዙሪያችሁ እንዳሉ ልብ በሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ክፉዎች በብዙ መከራ ላይ ይወድቃሉ፣ በእግዚአብሔር የሚታመኑ ግን ዘላለማዊ በሆነው ፍቅሩ ይጠበቃሉ" (መዝ 32፥10) ይላል። በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ተስፋ ይሰጠናል፣ "ከእናንተ መካከል ጥበብ የጎደለው ሰው ቢኖር እግዚአብሔርን ይለምን፣ እግዚአብሔር ይሰጠዋል፤ ምክንያቱም እርሱ ምንም ሳይከለክል ለሁሉም በልግስና የሚሰጥ ቸር አምላክ ነውና" (ያዕ 1፥5)።

በአካባቢያችን ያሉ ሁኔታዎች ለቤተሰባችን ከባድና አስቸጋሪ ቢሆኑ እንኳን፣ የተሻለ ነገር ለማድረግ ከመጣር ሊያግዱን አይገባም። አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ ዐምፀው ከኤደን ገነት ከተባረሩ በኋላ፣ ልጆቻቸውን በሚያሳድጉበት ጊዜ ከፍፁምነት ጉድለዋል። አንደኛው ልጃቸው (ቃየን) ሌላውን ልጃቸውን (አቤልን) ገድሏል። አዳምና ሔዋን በግልጽ ከቃየን ጋር አብረው የወደቁ ቢሆንም፣ ከአቤል ጋር ወደ ግቡ ደርሰዋል። እንዲህ ተብሎ እንደተነገረን፣ "እግዚአብሔርም በአቤልና በመስዋዕቱ ደስ አለው" (ዘፍ 4፥4) ማለት ነው። ፍቺ ወይም ሞት ወይንም ደግሞ ሌላ ዓይነት ችግር ቤተሰባችንን ቢለያይ እንኳን፣ ተስፋ መቁረጥ የለብንም። እግዚአብሔር ለለ ቤተሰባችን ከእኛ በላይ ይጠነቀቅልናል፣ በእሱ አርዳታ ለልጆቻችን መልካም ነገርን ማድረግ እንችላለን።

ጋብቻ፦ ሲየሱስን ለማንፀባረቅ ነው

ሌላው እግዚአብሔር ጋብቻን ለእኛ የሰጠበት ትልቁ ምክንያት ሲየሱስን እንድናንፀባርቅ ነው። ክርስቲያኖች ከሆንን ሌሎች ሰዎች በግል ሕይወታችን ኢየሱስን እንደሚያዩ በትዳራችንም ውስጥ ኢየሱስ ተንፀባርቆ ሊያዩ ይገባቸዋል።

ፍቅር፣ ሰላም፣ ደስታ፣ ትዕግስት፣ ደግነት፣ ጨዋነትና ሌሎችም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ በየግል ባሕርያችን እንደሚንፀባረቁ

ሁሉ በክርስቲያን ባልና ሚስት ግንኙነት መካከል ገሃድ ሆኖ መውጣት ይገባቸዋል (ገላ 5፥22-23)። ከዚህም በበለጠ የባልና ሚስት ህብረት፣ በክርስቶስና በሕዝቡ መካከል ያለ አንድነት ምልክት (ምሳሌ) ሊሆን ይገባል (ኤፌ 5፥22-23)። ሌሎች ሰዎች በጋብቻችሁ ውስጥ ክርስቶስን ያያሉ?

ምን አጋጠመው?

ጋብቻችን ትክክለኛውን አቅጣጫ በሚለቅበት ጊዜ ከሰይጣን የበለጠ የሚደሰት ማንም የለም፣ የሰይጣን ግቡ ሁልጊዜ አግዚአብሔር ለእኛ ያለውን በጎ ዓላማ ማገድ ነው። የጠነከረ የክርስቲያን ጋብቻ በእግዚአብሔር እጅ የሚመሰገን መሣሪያ እንደሆነ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ፣ አብዛኛውን ጊዜ ሰይጣን ጠንካራ ጥቃቱን በቀጥታ ወደ ጋብቻችን የሚያነጣጥረው ለዚህ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን በጋብቻ ላይ የመጀመሪያ ጥቃት ሲፈጽም የታየው በእዳምና በሔዋን ጋብቻ ነው። ባልና ሚስትን ለመለያየት ያደረገው መከራ ነበር። ይህ ለልቱ ዛሬም አልተቀየረም። ሰይጣን ጋብቻችን የተሸመደመደ እንዲሆን ይፈልጋል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከፊታችን ያዘጋጀልንን ጉዞ እንዳንንዝ ጥቂት ነገር ተስፋ እንደሚያስቆርጠን ስለሚያውቅ ነው።

አንድ ጊዜ አንድ ሰው፣ ሰዎች በደብዳቤዎቻቸው ከሁሉ ይበልጥ የሚጽፉልኝ ችግር ምን እንደሆነ ጠይቆኝ ነበር። እኔም "በብዛት ለጋብቻ ችግር ነው" ብዬ መልሼለታለሁ። በፍቺ ችግር ምክንያት የልብ ስብራት ያልደረሰባቸው (እኛን ጨምሮ) ጥቂቶች እንደሆኑ አውቃለሁ። ብዙ ጋብቻዎች ችግር የሚያጋጥማቸው ለምንድነው? ሊደረግ የሚችል ነገር አለ?

ከብዙ ጋብቻዎች በስተጀርባ ያለው መሠረታዊ ችግር በአንድ ቃል ሊጠቀለል ይችላል፣ ግጭት (አለመግባባት) ነው። አለመግባባት በብዙ መልክ ልገለጽ ይችላል። በባለትዳሮች መካከል አለመነጋገር ሊሆን ይችላል፣ መለዳደብና ሁከት የሚገለጽበት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ለአለመግባባቱ የመነሻ ምክንያት ምንድን ነው? የግጭቶች ምንጫቸው ማለቂያ የሌለውና አብዛኛውን ጊዜም ለይቶ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። የአንዳንድ አለመግባባቶች ምንጫቸው ስዎች ወደ ጋብቻዎቻቸው የሚያመጡአቸው ችግሮች ናቸው። ወደ ትዳር ዓለም የገቡት ደህንነት ስለማይሰማቸው፣ ወይም የበታችነት ስሜት እንዳይሰማቸው ወይም ከብቸኝነት የተነሣ፣ ወይም በወሲብ ፍቅር

ወይም ደግሞ ካለባቸው የኑሮ ችግር ለመላቀቅ ይሆናል። አነዚህ ሁኔታዎች ውለው አድረው የአለመግባባት ምንጭ ይሆናሉ።

ቁጣ፣ ተሳዳቢነት፣ የአልኮል ሱሰኝነት አመንዝራነትና ሌሎች የመሳሰሉት ችግሮች ካለበት ቤተሰብ የሚመጣ ስው ወባሳ ይዞ ስለሚመጣ በትዳር ጓደኛው ላይ ችግር ሊፈጥርና ወደ ብጥብጥ ሊመራ ይችላል። ወይም ደግሞ ከሁለት አንዳቸው (ባል ወይም ሚስት) ምናልባት ያልበሰሰና ኃላፊነት የማይሰማቸው ከሆኑ ሁልጊዜ ስለሚገጥማቸው ችግር ሌላውን የሚወቅሱና የሚቃወሙ ይሆናሉ፤ ይህ ደግሞ አለመግባባትን ይፈጥራል። አንዳንድ ጊዜ ባለትዳሮች ባለመከባበር (በመናናቅ) ምክንያት አብረው ለመቀጠል ይቸገራሉ። ሁለቱም በጣም ግትር የሆኑ ቢጋቡና እርስ በርስ ለመቻቻል ካልተማሩ ችግር ይገጥማቸዋል። በትዳር ውስጥ የዘመዶች ጣልቃ ገብነት ካለም የአስመግባባት ምንጭ ይሆናል።

ሌሎች አለመግባባቶች የሚፈጠሩት ባለትዳሮቹ ራሳቸው በሚፈጥሩት ችግር ነው። የጋብቻ አማካሪዎች እንደነገሩኝ ባለትዳሮች ከሚጋፈጣቸው ትላልቅ ችግሮች መካከል በገንዘብ ምክንያት የሚፈጠረው አለመግባባት ዋንኛው ነው። በቀላሉ የሚገኙ ብድሮችና ቀልብ የሚሠርቁ (የሚያባብሉ) ማስታወቂያዎች ብዙዎችን በዕዳ ባሕር ውስጥ እንዲዘቅጡ በማድረግ ወደ ብጥብጥ መርተዋል። ብዙ ልብ ሰባሪ የሆኑ ደብዳቤዎች ብዙ ጊዜ ይደርሱኛ ል። እነዚህም ባለመተማመን፣ በአልኮል ሱሰኝነት፣ በቁማር፣ በመናናቅ ምክንያት ወይም በሌላ አፍራሽ ምክንያት ጋብቻቸው ከፈረሰ ሰዎች የሚደርሱኝ ናቸው።

ሳይገለጽ መቅረት የሌለበት ሌላ የአለመግባባት ምክንያት ምንጭ የመንፈሳዊ ሕይወት አለመጣጣም ነው። አልፎ አልፎ አማኝ ካልሆኑ ጋር ፍቅር እንደያዛቸው የሚገለፀ ደብዳቤዎች ከክርስቲያን ወጣቶች ይደርሱኛል። በደብዳቤዎቻቸው ግንኙ ነታቸውን ወላጆቻቸው እንዳልተቀበሉ ይነግሩኛል። የማጽናልኝም ወላጆቻቸው ጋብቻውን እንዲፈቅዱላቸው እንዳሳምንላቸው ነው - ነገር ግን በጨናማ ሕሊና ላደርግ አልችልም፣ አልሞክረውም። ይህ ነገር በመጽሐፍ ቅዱስ ተቀምጧል፣ "በማይመች ሁኔታ ከማያምኑ ሰዎች ጋር አትጣመሩ" (2ቆሮ 6፡14)። ይህንን መሰል ለሆነ ጥያቄ ሁሉ፣ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚያመለክት ደብዳቤም ደርሶኛል። ደብዳቤውን የጻፈልኝ የአግዚአብሔርን መመሪያ አቃሎ አማኝ ያልሆነችውን ካገባ ክርስቲያን ሲሆን በአድራጎቱ አሠቃቂ

ሕይወት እንዳላለፈ፣ በሥቃይ የተሞላ ዋጋ እንደከፈለ፣ አለመጠጣም፣ አለመተማማን፣ የታማኝነት መጥፋትና ብሎም ፍቺ እንደተጋፈጠ ያረጋግጣል። እንዲህ ዐይነት የጋብቻ ውሳኔ ካደረጉት መካከል አልፎ አልፎ ብቻ አማኝ ያልሆነው የትዳር አጋራቸው ከዓመታት ፀሎትና መስዋዕትነት ከመክፈል በኋላ ወደ ክርስቶስ እንደመጣላቸው ይገልጹልኛል።

መሠረታዊ ችግር

በጋብቻ ውስጥ አለመግባባቶች በብዙ ነገሮች ይቀሰቀሰሉ፣ ነገር ግን ከሁሉ ነገር በስተጀርባ እጅግ መሠረታዊ መንስኤ አለ፣ አርሱም ራስ ወዳድነት ነው።

እጅግ ብዙ ባሎችና ሚስቶች ወደ ሕይወት የሚገቡት አግቢአቸው አንድ ዓላማ እንዲያሟላላቸው ነው፣ ዓላማውም እንዲያስደስታቸው ነው። ነገር ግን ጋብቻን ራስን በመጥቀምና በማስደሰት ግብ አቅጣጫ ብቻ መገንባቱ ቤቱን በአሸዋ ላይ እንደገነባው ዓይነት ሰው የሚቆጠር ነው። እያንዳንዱ በራሱ ፍላጎት ላይ ካነጣጠረ፣ አንዱ ሌላውን የትዳር ጓደኛውን ለማስደሰት ምን ማድረግ እንደሚገባው አይጨነቅም። ይህ ዓይነት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ፣ ጋብቻው በስባድ ኪሳራ ውስጥ እንደሆነ ይቆጠራል።

እውነተኛ ፍቅር ግን በራስ ወዳድነት ላይ የተመሠረተ አይደለም። ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ ራሳችሁን ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ? ይህንን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ፣ በመጀመሪያ የፍቅር ተቃራኒ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ራሳችሁን ጠይቁ። ቀደም ብሰን እንደተመለከትነው፣ የፍቅር ተቃራኒ ጥላቻ ብቻ አይደለም ወይም እንዲያው ግድ የለሽነትም አይደለም፣ ግን ራስ ወዳድነት ነው። ስለዚህም ነው ፍቅር - እውነተኛ ፍቅር፣ አጋፔ ፍቅር - በወሲባዊ ስሜት ላይ የተመሠረተ ወይም ደግሞ ሌላውን ለው በአካላዊ ውበት የመማረክ ተግባር ያልሆነው። በዚህ ዘመን ብዙዎች ለዎች ፍቅርን ከወሲባዊ ስሜት መማረክ ወይም ደግሞ ስሜትን ከመቀስቀስ ጋር ያመሰቃቅሉታል። የመገናኛ ብዙሃንም ይህን የተሳሳተ ሀሳብ በየቀኑ ያራግቡታል። ብዙ ሰዎች፣ እነዚህ የመገናኛ ብዙሃን ስለ ፍቅርና ጋብቻ የሚያስተላልፉትን የእንጋገር ብዒሎችን የተመሠረቱ የተንጋደዱ አስተሳሰቦችን ተቀብለዋል ብዬ እስጋለሁ። ነገር ግን ውበት ይረግፋል፣ ስሜትም ይጠፋል። በአካላዊ ውበት በመማረክ ወይም በወሲብ ስሜት በመገፋፋት

የተመሠረተ ጋብቻ ከለርጉ ማግስት ጀምሮ ስመፍረስ የተዘጋጀ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ እንድናፈቅር የማፍቀር ችሎታ የሰጠን እግዚአብሔር ብቻ ነው። የእውነተኛ ፍቅር ትርጉሙንም የሚያስተምረን እግዚአብሔር ብቻ ነው።

እውነተኛ ፍቅር

እውነተኛ ፍቅር ምንድነው? ቀደም ብለን ስለ እርስ በርስ ግንኙነት በሚያወራው ምዕራፍ እንደተመለከትነው፣ እውነተኛ ፍቅር በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ተግባር ነው። ይልቁንም ምርጥ ነው ብለን የምናስበውን ነገር ለራሳችን በማድረግ ፈንታ ለሌሎች ለማድረግ አስበንበት የምናደርገው ውሳኔ ነው። ለዚህም ነው በጋብቻ ውስጥ መሰጠት የሚያስፈልገው። ወንዱና ሴቷ ሁለቱም አብረው እስከኖሩ ድረስ አንዱ ለሌላው መሰጠት ማለት ነው።

እኔና ሩት በተጋባን ጊዜ፣ በቤተሰቦቻችንና በወዳጆቻችን ፊት ቆመን ለተጠየቅነው ሁሉ "አስማማለሁ" ብለናል። በነዚህ ቃላት በቀሪው ዘመናችን አንዳችን ለሌላው መሰጠት እንዳለብን ቃል ኪዳን አድርገናል። ነገር ግን ኪዳን ስንገባ ቆመን የነበረው በጉባኤው ፊት ብቻ ሳይሆን የቆምነው በእግዚአብሔር ፊት ጭምር ነበረ፣ በሱ ፊት መሃላ ፈጽመናል። እርሱ አንድ አድርጉናል፣ ስለዚህ እርስ በርሳችን መዋደድ እንዳለብንና በሕይወት ዘመናችን ሁሉ አብረን በሕይወት ስንኖር ሰርስ በርሳችን ታማኝ እንደምንሆን ለእግዚአብሔር ቃል ገብተናል። የፍቅራችን ኪዳን ከበድ ያለ የመሰጠት ውሳኔ ሲሆን በእግዚአብሔር መገኘት ማህተም የታተመ ነበር። ከባለቤቴ ጋር ለዓመታት አብረን ስንኖር ድካምና ውጥረት በመንገዳችን ላይ ሲያጋጥሙን፣ ኢየሱስ፣ "እንግዲህ እግዚአብሔር ያጣመረውን ሰው አይለየው" (ማቴ 19፥6) ያለው ቃል ሰርስ በርሳችን እውነተኛ እንድንሆን አድርጉናል።

የፍቅር ስዕል

የኮሌጅ ተማሪ የሆነች አንዲት ወጣት በቅርቡ በጻፈችልኝ ደብዳቤዋ፣ "ለማግባት ያሰኝ ፍላጎት በጣም ከፍተኛ ነው። ነገር ግን ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ በትክክል ስለማወቁ እርግጠኛ አይደለሁም። ያደግኩት በፈረሰ ቤተሰብ ውስጥ ነው፣ እውነተኛ ፍቅር የሚባለውን ከቶ አይቼው አላውቅም። ለመሆኑ እውነተኛ ፍቅር የሚባል አለ? " በማለት ጠይቃኛለች።

አዎን አለ፣ እውነተኛ ፍቅር የሚባለው እውን አለ - ልናውቅም ልናገኝም የምንችለው በእግዚአብሔር ርዳታ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአታችንንና ራስ ወዳድነታችንን አስወግዶ በኛ ውስጥ የርሱን ፍቅር ሊተካ ይፈልጋል። የርሱ ፍቅር ለራሳችን ሳይሆን ለሌሎች ትኩረት እንድናደርግ የሚያደርግ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል፣ "እንዲሁም እያንዳንዱ ሰው የራሱን ጥቅም ብቻ ሳይሆን የሌላውንም ሰው ጥቅም ያስብ" (ፊልጵ 2፥4)።

እውነተኛ ፍቅር ማለት ይህ ነው፣ ኢየሱስ ሰኛ ራሱን እሳልፎ እንደሰጠ፣ መስዋዕት እንደሆነ ማለት ነው፣ "ራሱን በትህትና ዝቅ አደረገ እስከ ሞት ድረስ የታዘዘ ሆነ" (ፊልጵ 2፥8) ፍቅር ማለት የራስን ፍላጐት ለሌላ መሠዋት ነው። ፍቅር ምን እንደሆነ ለማወቅ ትሻላችሁ? ኢየሱስን ተመልከቱ፣ በገዛ ፈቃዱ የመንግስተ ሰማያት ክብሩን ትቶ ኃጢአትና በደል በሰለጠነባት በዚህች ምድር ሰመመላለስና ለሰው ሁሉ የሚሆን እጅግ ታላቅ የሆነ መስዋትነትን ሰመክፈል የመጣውን - በመስቀል ላይ ተሰቅሎ የሞተልንን - ተመልከቱ፣ ስለዚህ እኛ ዳንን። በኛ ምትክ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፣ ከራሱ ይልቅ እኛን አስበለጠን፣ እውነተኛ ፍቅር የሚሠራው እንዲህ ነው።

የሐዋርያው ጳውሎስ ራበን አሳልፎ የመስጠትን ፍቅር ምንነት ማብራሪያ - መጽሐፍ ቅዱስ አጋፔ ፍቅር ይለዋል - አብዛኛውን ጊዜ ጋብቻ በማፈፀምበት ሠርግ ላይ ይጠቀሳል፣ ግን ወዲያውኑ ይረሳል። ነገር ግን በልባችንና በአዕምሮአችን ውስጥ መቀበር ያለበት ነው፣ "ፍቅር ታጋሽ ነው፣ ፍቅር ደግ ነው። ፍቅር አይመቀኝም፣ ፍቅር አይተበይም፣ ፍቅር አይኮራም። ፍቅር ስርዓተ ቢስ አይደለም፣ ፍቅር የራሱን ጥቅም ብቻ ፈላጊ አይደለም፣ ፍቅር አይበሳጭም፣ ፍቅር ቢበደልም በደልን አይቆጥርም። ፍቅር ሁሉን ችሎ ይታገሳል። ፍቅር በሁሉም ላይ ተስፋ ያደርጋል፣ ፍቅር በሁሉ ነገር ይፀናል፣ ፍቅር ሁልጊዜ ይኖራል እንጂ አይጠፋም (1ቆሮ 13፥4-5፣ 7-8)።

ይህ ለሚፀና ፍቅር ከእግዚአብሔር የተሰጠ የገዛ ካርታ ነው። ይህንን የገዛ ካርታ ብንጠቀምበት ጋብቻችን (እናም ሕይወታችን) ምንኛ ልዩ በሆነ ነበር!

ሃያ ስድስት

እሳቱ እንዳይጠፋ መጠበቅ

ስኔና ቤቱ ግን ስገዚለብሔርን ስናመልካለን።

(ኢያሱ 24÷15)

ዕፀዋት በራሳቸው ማደግ አይችሉም፤ በሚገባ ማደግ ይችሉ ዘንድ የመኮትኮት፣ የማረምና ውኃ የማጠጣት እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል። የእውነተኛ ጋብቻ ሁኔታም እንዲሁ ነው።

በቅርቡ የጋብቻ መታሰቢያ በዓላቸውን ሊያከብሩ ወደ አንድ ምርጥ ወደ ሆነው ምግብ ቤት ሔደው ስለነበሩ ባለትዳሮች የሰማሁት አለ። በሠላሳዎቹ ዓመታት የዕድሜ ክልል የሆነች ታስተናግዳቸው የነበረች ሴት፣ የባለትዳሮቹ ሁኔታ የተለየ ሲሆንባት ተጠራጥራ በጠየቀቻቸው ጊዜ፣ ከተጋቡ ልክ 16 ዓመት እንደሆናቸው ነገሯት።

"16 ዓመት!" ብላ በመደነቅ ጮኻ በመናገር፣ ራሷንም በመነቅነቅ "በጋብቻ ይህን ያህል ዓመት ከማንም ሰው ጋር አብሮ ስመቆየት አላስብም" ካለች በኋላ በጋብቻ ውስጥ ሰሠላት ጊዜ አግብታ የፈታችና አሁን አብሯት ያለው ሦስተኛዋ ሰው በባልነት ሊቀጥል ምንም ፍላጎት ያላላያት መሆኑን ተናገረች። ለዚህች ሴት ጋብቻ ማለት የጥቂት ዓመታት የጊዜያዊ ደስታ ውል መሆኑ ያለዝናል።

ይህች ሴት ስለጋብቻ ያላት አሉታዊ አስተሳሰብ በዚህ ዘመን በብዙ ሰዎች ዘንድ እየተስተጋባ ነው ብዬ እፈራለሁ። ባለፉት ዐሰርቱ ዓመታት ውስጥ የፍቺ ቁጥር በአስደንጋጭ ሁኔታ መጨመሩን የስታትስቲክስ መረጃዎች ያመለክታሉ። አንዳንድ ወጣቶች ትዳር መያዝን እየሸሹ ነው፣ ምክንያቱም ካገቡ ትዳሩ ላይዘልቅ ይችላል በሚል ፍርሃት ነው። ይህ አንዳለ ሆኖ ግን

ማንም ቢሆን ጋብቻው ይፈርሳል እያሰ ወደ ጋብቻ አይገባም። የሆሊውድ ተዋናይ ወይም ተዋቂ የፖፕ ሙዚቃ አቀንቃኝ ለዐራተኛ ወይም ለአምስተኛ ጊዜ ወደመተሳሰፊያው በመሄድ "በመጨረሻ እውነተኛ ፍቅር አገኘሁ" ይላል። የሚያሳዝነው ግን ደስታን ይለጠናል ብለው የነበረው ተስፋ ሁሉ ቅዠት ይሆናል። ግን ይህ ሁኔታ በዚሁ መቀጠል አለበት? ደስተኛና ዘላቂ ጋብቻ መመስረትስ ይቻላል?

ያልተጣሩ ህልሞች

ይህ ምዕራፍ እየተጻፈ ሳለ፣ አንዱ የልጅ ልጃችን እኔና ሩት ከስድሣ ዓመት በፊት በተጋባንበት ጊዜ ቃለ መሐላ በፈፀምንባት ጻሎት ቤት የጋብቻ ሥርዓት ተፈፀመለት። የልጅ ልጃችን ከሙሽራይቱ ጋር ሊጎበኙን አዜታችን በመጡ ጊዜ ሁለቱ ለእርስ በርስ ያላቸው ፍቅራቸውና መተሳሰባቸው እንደዚሁም የሚታይባቸው ደስታ ገሃድና አስደናቂ ነበር። ልክ ሴሎች ባለትዳሮቿን እንደማውቃቸው፣ አነርሱም ፈቃዳቸው ፍጹም ዘላቂና እንከን የሌለበት ፍቅር ሆኖ አንዲቀጥልላቸው ተስፋ ያደርጋሉ።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ አዲሶቹን ባለትዳሮች ልረዳቸው አልቻልኩም፣ ግን ሊያጋጥሟቸው የሚችሉ ፈተናዎችን በጋራ እንዲጋፈጡት መንገዱን አሳያቸዋለሁ። እንደ ሁሉም አዲስ ሙሽሮች የሕይወት ተሞክሮአቸው ይለያያል፣ የተለያየ የትምህርት ደረጃ፣ የተለያየ ልምምድ፣ የተለያዩ ወላጆች፣ የተለያዩ ወንድሞችና እህቶች ሌላው ቀርቶ ከተለያየ ተስፋና ህልም የመጡ ናቸው። አብዛኛውን ጊዜ አስቸጋሪ የሆነውን፣ እያንዳንዳቸው ማቻቻል ወይም ማስተካከል እንደሚገባቸው አውቃለሁ።

ለለ ብለለታቸውና አንዱ ለሌላው ለላለው መለጠት ጽኑ መተማመን አለኝ፣ ነገር ግን የጀመሩት የሕይወት ጉዞ መንገድ ከወደፊቱ አለቸጋሪ ወይም ከባድ ሥፍራዎች እንደሚኖሩት አውቃለሁ። ይህ ዓይነቱ ችግር በሁሉም ጋብቻ ያጋጥማል፣ ሰይጣንም አጋጣሚውን ሁሉ በመጠቀም አፍራሽ ድርጊቱን ለመፈፀም ይጥራል።

የሚያሳዝነው ግን፣ ብዙ ባሎችና ሚስቶች ጋብቻ የሚመሠርቱት በከፍተኛ የፍቅር ለሜት ውስጥ ሆነው ባላቸው ፍቅርና ለሜት ላይጠራጠሩ - የሚያጋጥመውንም መሰናክልና ችግር እንደሚሻገሩ በመተማመን ነው። ከጊዜ በኋላ የፖፕ ሙዚቃ

አቀንቃኝ የለጠው ተስፋ ይህ አይደለምን? ይላሉ። ነገር ግን ችግሮች ሲጀምሩ፣ በጋራ በመሥራትና ችግሮቹን ከመፍታት ይልቅ "ያገባሁት ትክክለኛ ያልሆነውን ሰው ነው?" አም ለእኔ እሱ "ትክክለኛ" ሰው አይደለም! ምናልባት ስህተት ሰርቻለሁ . . . ሌላ ሰው መፈለግ ይኖርብኝ ይሆናል በማለት ለራሳቸው ማውራት ይጀምራሉ።

በዚህ ዘመን ፍቺ ቀላልና የተለመደ ስለሆነ የሚያሳምም ውጤቱን ለማየት ተስኖናል። እንዳንዶቻችሁ ምን እያልኩ እንደሆነ ታውቁታላችሁ፣ ምክንያቱም በራሳችሁ ሕይወት የፍቺ ጠባሳ ስላለ ነው፤ የወላጆቻችሁ ወይም የራሳችሁ ጋብቻ ፈርሶባችሁ ስለሚሆን ነው። እስካሁንም እንኳን የተቃውሞ የቁጣ፣ የምሬት፣ የተስፋ መቁረጥ ስሜት እየተናነቃችሁ ይሆናል - እነዚህ ሁሉ ፍቺን ተከትለው የሚከሰቱ ናቸው። እግዚአብሔር በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እያለፋችሁ እንደሆነ እንደሚረዳ፣ አሁንም እንደሚወዳችሁና እርስ ሊያፅናናችሁና ሊመራችሁ እንደሚፈልግ እረጋግጥላችኋለሁ። በክርስቶስ በኩል ወደርስ እንደ ተመለሳችሁ አዲስን ተስፋ ታገኛላችሁ፣ እግዚአብሔር፣ በተጨማሪ፣ በመንገዳችሁ ሊረዷችሁና ሊያበረታቱአችሁ የሚችሉ ሰዎችን ይሰጣችኋል።

እያንዳንዱ ፍቺ ያልተጣራውን ሕልም፣ የተሰባበረን ተስፋ፣ የፈረሰውን ግምት ይወክላል። እንዲሁም እያንዳንዱ ፍቺ እግዚአብሔር ስለጋብቻ የሰጠውን መሠረታዊ ንድፍ መጣስን ይወክላል። እግዚአብሔር የሰጠው ንድፍ ባል ለሚስቱ፣ ሚስት ደግሞ ለባሏ፣ ሁለቱ አብረው እስከኖሩ ድረስ፣ የተሰጡ መሆኖቸውን ያመለክታል።

የመከላከያ መድኃኒት

ትዳራቸው ከፈረሰባቸው ብዙ ሰዎች ደብዳቤዎች ይደርሰኛ ል፣ ብዙዎቹ ምን እንዳጋጠማቸው ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ተደጋጋሚ ገላጭ ሐረግ "በቃ፣ ሊሆን አልቻለም" የሚሉ ነው..

ነገር ግን ፍቺን እንደተላል በዚህ ሀገር የምንለው ብቻ ሳይሆን "የመሬት መንቀጥቀጥ ሆነ" ከሚባለው በላይ ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት ሩትና እኔ ጓደማላን ኃይለኛ የመሬት መንቀጥቀጥ በመታት ጊዜ ወዲያውኑ በአደጋው የተጐዱ ወገኖችን እንዴት መርዳት እንደምንችል ለማየት ሄደን ነበር፣ እንዲህ ዓይነት ውድመት አጋጥሞ አይቼ አላውቅም። አስተናጋጃችን ይህ የመሬት

መንቀጥቀጥ እደጋ የደረሰው ለብዙ ዓመታት ከምድር በታች የነበረው ግፊትና ውጥረት እያደገና እየጨመረ መጥቶ፣ ልክ የታፈነ ቁስል እንደሚመነጭ፣ የተከሰተ እንደሆነ አስገነዘበኝ። በመጨረሻም እነዚያ ከመሬት በታች የነበሩ ውጥረቶች ኃይለኛ ሆነው በምድር ላይ በመፈንዳት ብዙ ጥፋት ያስከትላሉ። የመሬት መንቀጥቀጥ እንዲያው ዝም ብሎ በድንገት አልሆነም፣ ነገር ግን ለብዙ ዓመታት እያደገ የመጣው ውጥረት ውጤት ነው። ጋብቻ ሊፈርስም በዚሁ መልክ ነው። ከብዙ ፍቺዎች በስተጀርባ ለማደግ ዓመታት የፈጁ ውጥረቶች ነበሩ።

ነገር ግን በመሬት መንቀጠቀጥ እደጋና በፈረሰ ጋብቻ መካከል አንድ ዋና ልዩነት አለ። የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋን ማንም ወይም ምንም ሊከላከል አይችልም - ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ የሚፈርሰውን ጋብቻ ለመከላከልና ለማዳን ብዙ ሊደረግ ይችላል። በርግጥ እያንዳንዱ ጋብቻ ይለያያል፣ በመሆኑም ሁሉንም ጋብቻ፣ ጥረት ቢደረግም፣ ለማዳን አይቻልም። እንዳንድ ጊዜ ችግሮቹ ጥልቅና የተወሳሰበ ናቸው። ነገር ግን ብዙ ጋብቻዎች እስቀድሞ አፍራሽ የሆኑ ውጥረቶቻቸው እንዳያድጉ የመከላከል ርምጃዎች ቢወሰዱ ኖሮ ለመዳን ይችሉ እንደነበረ እምናለሁ - መዳን ብቻ ሳይሆን፣ ጤናማ፣ ጠንካራና ስኬታማ ይሆኑ ነበር።

እነዚህ ርምጃዎች ምንድን ናቸው? ከራሴና ከሌሎች ወገኖች ልምድ በመነሳት (ከመጽሐፍ ቅዱስ ያጠናሁትንም ይጨምራል)፣ ጋብቻን የተሟላና የተረጋጋ ሊያደርጉ የሚችሉ ሶስት መሰረታዊ የሆኑ ርምጃዎች አስቲ ልዘርዝርላችሁ እነዚህን እሳቱ እንዳይጠፋ የሚያደርጉ ሦስት ርምጃዎች ብለን ልንጠራቸው እንችላለን። በርግጥ እነዚህ ሁሉንም ነገር የሚያጠቃልሉ አይደሉም፣ የመነሻ ነጥብ ብቻ ናቸው፤ ለዓመታት የቆዩ ችግሮች በአንድ ቀን ጀምበር መፍትሔ ሊያገኙ አይችሉም። ይሁን እንጂ፣ ልክ የሕክምና ባለሙያ ችግሮች ከማደጋቸውና ከመባባሳቸው በፊት ለመለየት እንደሚሞክረው፣ እነዚህ ሶስት ርምጃዎች ለጋብቻችሁ የመከላከያ መድኃኒት ሊሆኑ ይችላሉ። ችግሮች ሥር ከመስደዳቸው በፊት በመነጠል ለመከላከል ይረዳሉ።

ጋብቻን ስእግዚአብሔር አስረክቡ (ስጡ)

ጤናማና እጅግ ጠቃሚ በሆነ ጋብቻ ውስጥ ሆኖ ለመቀጠል የመጀመሪያው የማዕዘን ድንጋይ (ርምጃ)፤ ጋብቻን ለእግዚአብሔር ማስረከብ ነው።

ክዓመታት በፊት አንድ ሰው በስዊዘርላንድ የተሠራ የእጅ ሰዓት ለጠኝ። ለዓመታት በትክክል ይቆጥር የነበረው ይህ ሰዓት አንድ ቀን መሥራቱን አቆመ። ወደ ሰዓት ጠጋኝ ወሰድኩት፣ ከመረመረው በኋላ ጠጋኙ ራሱን በመነቅነቅ፣ "አዝናለሁ ይዬን ሰዓት ወደ ፈብራኪው መልሰህ ላከው ሊያስተካክለው የሚችለው እርሱ (የሰራው ሰው) ብቻ ነው" በማለት መለሰልኝ። የጋብቻ ነገርም እንዳሁ ነው። እግዚአብሔር ጋብቻን መሠረተ፣ ለኛም ለጠን፤ በዚህ ምክንያት ለጋብቻችን ዋስትና መመሪያውን መከተል ተገቢ አይደለምን? ደግሞስ በጋብቻችን ችግር ሲፈጠር ወደርሱ መምጣት የለብንም? እግዚአብሔር ለጋብቻ ያለውን እቅድ ችላ ብንል፣ ቤታችን (ትዳራችን) ሁልጊዜ በአደጋ ውስጥ ነው። መልካም ሥርዓት ያለው ቤተሰብ የሚመሠረተው የእግዚአብሔርን ፈቃድ መሰረት ባደረገ መልካም ጋብቻ ላይ ነው። በመልካም ጋብቻ ውስጥ ሶስት ሰዎች እንዳሉ ብዙ ጊዜ ተናግሬአለሁ። እነሱም ባል፣ ሚስት እና እግዚአብሔር ናቸው። ጋብቻችሁን ከአሁን ለዓት ጀምሮ ለክርስቶስ (ሕይወታችሁንም ጨምሮ) በማሰረከብ ጀምሩ።

ጋብቻችሁን ለእግዚአብሔር ማሰረከብ ማለት ምን ማለት ነው? አንድ ነገር፣ በጋብቻ ተጣምሮ ለመኖር የፈጸሙትን ቃለ መሐላ የምር ማድረግ ነው፤ ቃለ መሃላ የገባችሁት ለአርስ በርስ ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔርም ጭምር ነው። ይህ መሃላ ለአርስ በርስ ፍጹም ታማኝ መሆንን ይጨምራል። በጣም የሚያሳዝነው ግን በምንዝርናት ምክንያት ጋብቻ እንደፈረሰ የሚገልጽ ዳብዳቤ ሳይደርሰኝ ያሳለፍኩት አንድም ቀን አለመኖሩ ነው።

ማህበረሰባችን ታማኝ አለመሆንን እንደ ቀላል ነገር ይቆጥራል - እግዚአብሔር ግን አንዲህ አይመለከትም፣ ምክንያቱም እርሱ የሚያስከትለውን ሥቃይና ጥፋት ስለሚያውቅ ነው። ከዐስርቱ ትዕዛዛት አንዱ በግልጽ የሚያውጀው "አታመንዝር" ብሎ ነው (ዘፀ 20፣14)። በብሉይ ኪዳን ዘመን በሞት ያስቀጡ ከነበሩት ከባድ ወንጀሎች አንዱ ዝሙት ነበር። ቀላል ነገር አልነበረም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ከሴት ጋር የሚያመነዝር ግን አእምሮ የጎደለው ነው። እንዲህም የሚያደርግ ነፍሱን ያጠፋል" (ምሳሌ. 6፣32) ብሎ ያስጠነቅቃል። ለትዳራችሁ የገባችሁትን ቃል ኪዳን ለመጠበቅ እስክያቅታችሁ ድረስ የሚያደርግ ፈተና ወደ እናንተ እስኪመጣና እስክሚጥላችሁ ድረስ አትጠብቁት፤ ይህንን ጉዳይ አስቀድማችሁ ወስኑ፣ በፍጹም መስጠት ራሳችሁን ለታማኝነት አሁኑኑ አስረክቡ።

ከዚያ በኋላ ለይጣን በናንተ ላይ ምንም ዓይነት ድል የሚያገኝበትን ከፍተት ያጣል።

ጋብቻን ለእግዚአብሔር ማስረከብ ማለት በተጨማሪ ከክርስቶስ ጋር ባላችሁ ግንኙነት በአንድነት ማደግ ማለት ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ባልና ሚስት ለየብቻቸው በመሆን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አንዲያድጉ አይደለም፣ ነገር ግን የተጋባን ከሆንን እንደ ባለትዳሮች በመንፈሳዊ ሕይወታችን በአንድነት እንድናድግ ነው። በየዕለቱ ከክርስቶስ ጋር ለመገዝ ከመማር የበለጠ በፀና አንድነት የሚያስተሳስር ነገር የለም - ባንድ ላይ መጸለይ፣ ባንድ ላይ ቃሉን ማንበብ፣ ባንድ ላይ ወደ ቤተክርስቲያን መሔድ፣ አብሮ ሕብረት ማድረግ። በየዕለቱ ባንድነት ወደ እግዚአብሔር ፊት የመቅረብ መንፈሳዊ ልምምድ (ሥነ ሥርዓት) ለደስተኛ ቤተሰብ የሚያስፈልግ ወሳኝ ርምጃ ነው።

በወከበ በተሞላ የጊዜ ሰሌዳ እየኖርን ይህ ነገር ሁልጊዜ ቀላል አይደለም። ሰይጣን ሁልጊዜ "ይህ መቅደም አለበት" ብለን የምንሠራውን አንድ ነገር ያቀርብልናል። ከዚህ በፊት አብራችሁ የመጸለይ ልምድ ከሌላችሁ፣ ምግብ ከመመገባችሁ በፊት ሁልጊዜ ጥቂት ጊዜ ስጡና አግዚአብሔር ትመገቡት ዘንድ ስለሰጣችሁ ምግብ አመስግኑት። ይህ የጀመራችሁት ጸሎት እየተመቻችሁ ሲመጣ፣ ሌሎች ጉዳዮቻችሁን ጨምሩና መጸለያችሁን ቀጥሉ። በጋብቻችን የመጀመሪያዎቹ ዓመታት፣ ልጆቻችን በኛ ጥገኝነት ሥር አያለ፣ ምግብ ከተመገብን በኋላ በምግብ ጠረጴዛችን ዙሪያ የቤተሰብ ጸሎት ጊዜ ነበረን። አሁን ግን እኔና ሩት ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል እናነብና ከመተኛታችን በፊት አብረን እንጸልያለን። ዋናው ቁልፍ ነገር፣ በጊዜ ሠሌዳችሁ የሚስማማችሁን (አመቺ) ጊዜ ማድረግና በዚያ ጊዜ በፀሎት መቆየት መቻል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "ስለዚህ አሁን በምታደርጉት ዐይነት አንዱ ሌላውን በማነጽ እርስ በርሳችሁ ተረዳዱ" (1ተሰ 5፣11) ይላል።

ሁለተኛ ርምጃ፣ ለጋብቻ ቅድሚያ ስጡ

ከመጀመሪያው ቀጥሎ ሁለተኛው ደረጃ ራስን ለጋብቻ መስጠት (መስጠት) ነው።

በዚህ ዘመን ሁሉ ነገር ትኩረታችንን ለመሳብ ይጮኻል፤ ሥራ፣ መዝናኛ፣ ቤተክርስቲያን፣ ልጆች፣ ቴሌቪዥን፣ ገንዘብ፣

ማህበራዊ ግዴታዎችና የመሰሳሰት ይጮኻሉ። የጫፃዎች ዝርዝር ማሰቂያ የሌለው ነው። ካልተጠነቀቅንለት (ካልጠበቅነው)፣ ጋብቻችን በነዚህ ነገሮች ይታፈናል። በቀላሉ የትዳር ጓደኛችንን በመውሰድ ይጀምራል፣ ክዚያ ቀጣዩ ማለያየት ነው። ነገር ግን ይህ በፍጹም የእግዚአብሔር አቅድ አይደለም።

እግዚአብሔርን መውደዳችንን ከምናሳይበት መንገድ አንዱ ፍቅራችንን ለትዳር ጓደኛችን በማሳየት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ባሎች ሆይ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደና ራሱን ስለ እርስዋ አሳልፎ እንደሰጠ እናንተም ሚስቶቻችሁን ውደዱ" (ኤፌ 5፥25) ይላል። ክርስቶስ ራሱን መስዋዕት አድርጎ የሰጠው ለህዝቡ ካለው ፍቅር የተነሳ ነው፤ ባልም ሰሚስቱ ካለው ፍቅር የተነሳ ራሱን መስዋዕት አድርጎ ሊሰጣት ይገባዋል። ክርስቶስ ጋብቻን ሲመራና በፍቅሩ ሲሞላው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ሚስቶች ለባሎቻቸው እንዲገዙ (እንዲስማሙ) እና ባሎች ራሳቸውን እንደሚወዱ ሚስቶቻቸውን እንዲወዱ የሚለው መመሪያ ቀላል ይሆናል፤ ክርስቶስን በሕይወቱ የሚያስቀድም ባል፣ ሚስቱን ይወዳል፣ ያክብራልም፤ አምባገነን አይሆንም።

ራስን ለጋብቻ መስጠት ማለት ምን ማለት ነው? ክሁሉም ነገር በፊት ለጋብቻ ቅድሚያ መስጠት ማለት ነው፤ ለደህንነቱ ቅድሚያ መስጠት ማለት ነው። ይህም ማለት ማንኛውንም ማድረግ የምትፈልጉትን ነገር ማደያዝ ያስባችሁ በጋብቻችሁ ላይ የሚያስከትሰውን ፈይዳ በማሰብ ነው። ይህም ማለት ጋብቻችሁ እንደ ማንኛውም ክዕሰት እንቅስቃሴአችሁ አንደ አንዱ የሚታይ ሳይሆን ለሁሉም ነገር ዋንኛና ማዕከላዊ ሆኖ ሊታይ ይገባዋል ማለት ነው። ጋብቻችሁ እንደ ኃላፊነት እንጂ ልክ እንደ ልዩ መብት የሚታይ አይደለም ማለት ነው።

ጋብቻችሁ ለእናንተ ምን ደህል አስፈላጊ ነው? ለማጠናከር ምን እያደረጋችሁለት ነው? ጋብቻችሁ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ እንደሆነ ለእናንተም እንዲሁ ነው? እነዚህ እናንተው ብቻ የምትመልሷቸው ናቸው - ነገር ግን ችላ አትበሏቸው። ለጋብቻችሁ፣ ልክ እግዚአብሔር እንዳደረገው፣ ቅድሚያ ስጡ።

ሦስተኛው ርምጃ ፍቅር እና አክብሮት

ጠንካራ ጋብቻን ለመገንባት ሶስተኛው ደረጃ አርስ በርስ በፍቅርና አክብሮት በመሰጠት መመላለስ ነው።

እነዚህ የተለያዩ ሐሳቦች ይመስላሉ፤ ነገር ግን እውን የተቆራኙ ናቸው። ፍቅር ያለ አክብሮት ማሰት አንድን ስው ልክ ለማዳ እንስሳን እንደምንደባብሰው መደባበስ እንደማለት ነው። በአብሮነታቸው ብንደሰትም፣ ራሳችንን ከፍ አርገን በበታችነት ስሜት በመመልከት ምንም አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሱበት ጠቃማ ነገር እንደሌላቸው መናቅ ማለት ነው። አክብሮት ያለ ፍቅር ወደ ቀዘቀዘና ስኬታማ ወዳልሆነ ግንኙነት ይመራል።

የጋራ (የሁለቱ ወገን) ፍቅርና በአክብሮት መሆን ሁለቱም ለጠንካራ ጋብቻ አስፈላጊ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ስለዚህ ባል ሚስቱን እንደ ራስ አድርጎ ይውደድ፤ ሚስትም ባልዋን ታክብር" (ኤፌ 5፥33) ይላል። ሐዋርያው ጴጥሮስም፣ "እናንተም ባሎች ክሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ክእናንተ ይልቅ ደካማ ፍጥረት ስለሆኑና ክእናንተም ጋር የሕይወትን ጸጋ ስለሚወርስ አክብሩአቸው፤ በዚህ ዓይነት ለፀሎታችሁ መሰናክል የሚሆን ነገር አይኖርም" (1ጴጥ 3፥7) በማለት ጽፏል። ወንዶችና ሴቶች የተለያዩ ናቸው - እግዚአብሔርም የሠራን በዚህ መንገድ ነው - ባሎችና ሚስቶች እነዚህን ልዩነቶች ማወቅና መቀበል አለባቸው (በውስጣቸው ያለው ደስታ እንኳን ይለያል)። ነገር ግን አንዱ ክሌላው የተሻለ ነው ማለት አይደለም። ሁለቱም ባልና ሚስት በእግዚአብሔር ዐይን እኩል ናቸው፤ ሁለቱም በእስ አምሳል ስለተፈጠሩ፣ በእስተሳሰብ፣ በሕሲና በልዩ መብትና በኃላፊነት እኩል ናቸው። በጋብቻ ውስጥ ሰምንም ዓይነት አድሎ ሥፍራ የሰውም።

በጋብቻ ውስጥ ለትዳር ጓደኛችን አክብሮት ክምናሳይበት አንዱና አስፈላጊው መንገድ የግንኙነትን ጥበብ በመማር ነው። ይህ ዝም ብሎ ክማውራት በላይ የሆነ ነገር ነው፤ ሀሳብን እንዴት ማድመጥ እንዳሰብን መማርን ይጨምራል ሀሳብን እርስ በርስ ሰመከፋፈል ፈቃደኝነትን ማሳየት ማለት ነው፤ ይህም የትዳር ጓደኛ ዬ ይቃወመኛል ወይም ይስቅብኛል የሚል ፍርሃት ገፎ በመጣል የሚሆን ነው። እርስ በርስ በስሜታዊነትም ሆነ አስተውሎት ባሰው ደረጃ በምናደርገው ነገር መቀባበል ማለት ነው። በአጠቃላይ ይህ ጉዳያ ሰእኛ ሰወንዶች ከሴቶች ይልቅ ክባድ ፈተና ይሆንብናል፤ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ ጠንክረን መሥራት ይጠበቅብናል። ባሰቤቱ ሩት ሁልጊዜ ችግር እያጋጠማት ወደ እኔ በመጣች ጊዜ፣ እሷ በትክክል የፈለገችውና ያጋጠማት ችግር፣ የእኔም ድርሻና ትብብር

ምን እንደሆነ ሳልገነዘብ በችኮላ ዝም ብዬ መፍትሔ ይሆናል ያልኩትን እንደተናገርኳት እርግጠኛ ነኝ።

የትዳር ጓደኛችሁን እንደምትወዱ ሳትገልጹለት (ሳትገልጹላት) ቀኑ እንዲሄድባችሁ እትፍቀዱለት። ፍቅራችሁን ባገኛችሁት አጋጣሚ ሁሉ ግለጹ። ማቀፍ፣ መሳም፣ በጨዋነት መዳለስ፣ ጨመቅ አድርጎ መያዝ፣ ለረቅ እያረጉ ማየትና በተጨማሪ "አሁንም እወድሻለሁ! እወድሃለሁ" በማለት እርስ በርስ ፍቅራችሁን ልትገልጹ ትችላላችሁ። አንድ በግልጽ የማስታውሰው እኔ በምኖርበት ሰፈር ይኖሩ የነበሩ በዕድሜ ጠና ያሉ ባለትዳሮች ነበሩ። እኔና ሩት እንደተጋባን ለመኖር በሄድንበት ሠፈር ያገኘናቸው ነበሩ። እነዚህ ባልና ሚስት የታወቁ መቂቀኞችና አስተማሪዎች ነበሩ፣ ሁልጊዜ ለሽርሽር ሲወጡ እናያቸው ነበር፣ እጃቸውን እንደ እዲስ ወጣት ፍቅረኞች ያቆላልፋሉ። ለእነሱ ባይታወቃቸውም ለእኔ ግን እንደ ጀማሪ ባልነቴ ምሳሌነታቸው ያስተማረኝ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር ነበር።

በተጨማሪም፣ ለእርስ በርሳችሁ ትሁት፣ ልዝብና አሳቢ ሁኑ። ባል ሚስቱን በአሽሙር ሊያሳፍራት ወይም ሊያቃልላት ወይም ሚስት ባሏን ስታርመው ወይም እንደ ትንሽ ልጅ ስትገሥፀው በተለይ ይህ በሌሎች ፊት ሊደረግ ላይ ሁልጊዜ ልቤ በጣም ያዝናል። ለትዳር ጓደኞቻችሁ ልትጠንቀቁላቸው እንደምትችሉ የሚታሰቡበት ልዩ የሆነ ነገር ሌላው እንዳለ አስቡ። ለመሆኑ የትዳር ጓደኞቻችሁን ተወዳጅ ምላ በመጋበዝ ወይም ደግሞ ያልተጠበቀ ውድ ስጦታ በድንገት በማበርከት ያስገርማችሁት መቼ ነው? አብዛኛውን ጊዜ ትንሽ ነው የሚባል ነገር ትልቅ ዋጋ አለው። ለራሳችሁና ለገጽታችሁ (ለመልካችሁ) ደግሞ ጥንቃቄ አድርጉ። ይህን በምታደርጉበት ጊዜ ለትዳር ጓደኛችሁ አክብሮት እያሳያችሁ ነው።

በጋብቻ ውስጥ ለዛ ያለው ጨዋታ አስፈላጊ ነገር ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ይህ ማለት በትዳር ላይ መሳቅ እይደለም፣ ነገር ግን ከትዳር ጓደኛችን ጋር በሕይወት ስሳጋጠሙ አንዳንድ እንግዳ አመሎች አብሮ መሳቅ ነው። ደግሞ የምታበረታቱ ሁኑ። መጽሐፍ ቅዱስ፣ በየቀኑ በመከባበር ተረዳዱ (ዕብ 3፥13) ይላል። በየጊዜው እርስ በርሳችሁ ይቅር መባባልን ተለማመዱ። ባለቤቱ ሩት ስለዚህ ነገር ስትናገር "መልካም ጋብቻ ሁለት ጥሩ ይቅርታ እድራጊዎችን የያዘ ነው" ትላለች። አንድ ሰው ደግሞ "በጋብቻ ውስጥ ሁለት

አስፈላጊ ሐረጎች "እወድሻለሁ/ እወድሃለሁ" እና "ይቅር በለኝ የሚሉ ናቸው" ብሏል። እርስ በርስ የምትተሳሰቡና የእንዳችሁ ጉዳት ለሌላው የሚለማችሁ ሁኑ። ችግር ባጋጠማችሁ ጊዜ እርስ በርስ ተረዳዱ። በገላትያ 6፥2 ያለው የጳውሎስ መልዕክት ለባሎችና ሚስቶች ልዩ ትርጉም አለው፣ ድካማችሁን እርስ በርስ የምትሸካከሙ ሁኑ በዚህም የጌታን ፈቃድ የምታሟሉ ትሆናላችሁ።

መልዕክት ሳላገቡ

ምናልባት ሳጤ (ለብቻችሁ) ናችሁ፣ ምክንያቱ ከቶ ስሳላገባችሁ ይሆናል ወይም ደግሞ እግብታችሁ ግን በፍቺ ወይም በሞት ምክንያት የተፋለሳባችሁ ትሆናላችሁ። ይህ ማለት እግዚአብሔር እናንተን የሚመለከተው እንደ ሁለተኛ መደብ ለው ነው ማለት ነው? ወይም ደግሞ በሕይወታችሁ የርሱን ዕቅድ ዘንግታችሁ ነው ማለት ነው? በፍጹም አይደለም! እግዚአብሔር አንዳንድ ለዎችን ያለ ጋብቻ እንዲኖሩ እንደጠራቸው እኔ አምናለሁ፣ እግዚአብሔር መሉ ጊዜአቸው እሱን ብቻ በማገልገል እንዲያዝ ስለሚፈልግ ለማገልገል፣ መታጠቅ እንዳለባቸው አምናለሁ። ኢየሱስ አሳገባም ነበር፣ ጳውሎስም እንደዚሁ። በዘመናት ሁሉ አንዳንድ የእግዚአብሔር ምርጥ አጋልጋዮች የነበሩት በፍጹም ያላገቡ ነበሩ። ባላችሁበት ሁኔታ ምክንያት ተስፋ አትቁረጡ፣ ነገር ግን ራሳችሁን ለክርስቶስ ስጡ፣ ሕይወታችሁን እንዲሞላውና ለክብሩ እንዲጠቀምባችሁ ጠይቁት።

እንደዚሁም፣ ራሳችሁን እግዚአብሔርን በማያስከብር ግንኙነት አታጠላልፉ። የወሲብ ስሜት ከሚቀስቅሱና ንጽህናን ከሚያጐድፉ ነገሮች ራቁ። በዙሪያችሁ የሚኖሩ ለዎች እንዲህ ዐይነት ጸያፍ ተግባሮችን የተቀበሏቸው ብቻ ሳይሆኑ በማስፋፋትና በመቀስቀስ ላይ ሲሆን ይችላል፣ ተጠርታችኋልና በጥንቃቄ ኑሩ። በእግዚአብሔር ደረጃ እናንተ የክርስቶስ ክሆናችሁ፣ በልዩ መለኪያ - በእግዚአብሔር መለኪያ - ልትኖሩ ተወርታችኋል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ክሌሎች ለዎች ጋር በኃጢአት አትተባበር፣ ራስህን በንጽህና ጠብቅ" ይላል (1ኛ ጢሞ 5፥22)።

ወይም ምናልባት ወጣት ልትሆኑ ትችላለችሁ፣ እናም ለራሳችሁ "ይህ እኔን አይመለከተኝም እኔ እንኳን እስካሁን አላገባሁም" ትላላችሁ። ነገር ግን ምናልባት እንድ ቀን ልትሆኑ ትችላላችሁና የወደፊቱን የጋብቻ ጉዳያችሁን ለእግዚአብሔር

የምታስረክቡበት ጊዜው አሁን ነው። እግዚአብሔር ከአናንተ የበለጠ ስለ አናንተ ጋብቻ ያገባዋል፤ ክርስቲያን ከሆናችሁ፤ እንድታገቡ ፈቃዱ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለአናንተ ሕይወትን በጋራ አብራችሁ የምትኖሩአቸውን የትዳር ጓደኞች እንደመረጠላችሁ እርግጠኛ ሁኑ። ስወደፊቱ ጋብቻችሁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ትጠይቃላችሁ? ስዚህ እጅግ አስፈላጊ ስሆነ ነገር ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስረክባችኋል? ካላስረከባችሁ አሁኑኑ አድርጉ።

ትክክለኛ ካልሆነ ስው ወይም ትክክለኛ ባልሆነ ምክንያት በፍቅር አትውደቁ። ስለ አካላዊ አቋምና ቁንጅና ትኩረታችንን ስንሰጥና ሰንላብ፣ ውስጣዊ የሆነ ማንነትን ችላ አንላለን፣ የትዳር ጓደኛን እውን ማራኪ የሚያደርጉትን ዘላቂ ብቃቶችን አናያቸውም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ቁንጅና ከንቱ ነው፣ ውበትም ይጠፋል እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን ልትመሰገን ይገባታል" ይላል (ምሳ 31፥30)። መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ፣ እንዲህ ይላል "ለአናንተም ጠጉርን በመሸረብና የወርቅ ጉትቻን በማንጠልጠል ወይም የከበረ ልብስ በመልበስ በውጭ የሆነ ጌጥ አይሁንላችሁ" (1ኛ ጴጥ 3፥3-4)።

ያላችሁበት ሁኔታ ምንም ይሁን፣ ግባችሁ በሁለም ነገር - ጋብቻችሁን ጨምሮ - እግዚአብሔርን ስማክበር ይሁን።

ሃያ ሰባት

የኃላፊነት ቅብብሎሽ

ልጆች ከእግዚአብሔር የሚገኙ ስጦታዎች ናቸው ስሙነተኛ በረከተ ናቸው።

. (መዝ. 127፥3)

የቤተሰብ ኃላፊነት ወላጆች የሆንን ሁለ የምንጋፈጠው፣ ከፍተኛና አስፈላጊ ግዴታችን ሲሆን ማናችንም ብንሆን በትክክል የማንወጣው ነው።

አንደገና በሕይወት አንድ ብዬ ስመኖር ብችል፣ ካለኝ ጊዜ ውስጥ አነስተኛውን ስገዘ፣ አብዛኛውን ደግሞ በቤቴ ውስጥ ከሩትና ከልጆቻችን ጋር ሰማሳለፍ አደርግ ነበር። ገዘ በወንጌላዊ ሕይወት ውስጥ አስፈላጊው ክፍል ነው (ምንም እንኳ ዘመናዊ የመገናኛ ዜዴዎች ማንኑነትን ቀላል ያደረጉት ቢሆንም)፣ ነገር ግን ወደ ኃላ መለስ ብዬ ሳስበው ቁጥራቸው የበዛ ገዘዎቼ በእርግጥ አስፈላጊዎቼ ነበሩ ወይ ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ።

ከቤተስቦቼ ለረጅም ጊዜያት መለየት ለነርሰም ለኔም በጣም አስቸጋሪ ነገር ነበር። በየጊዜው ስልክ አየደወልኩላቸው ላገኛቸው የምሞክር ቢሆንም (ከአንዳንድ የዓለማችን ክፍሎች የሚቻል ባይሆንም) ይህ ሙከራዬ አብሮ መሆንን የሚተካ አልነበረም። ልጆቻችን አያደገ ሳለ አብዛኛውን ጊዜ ከገናቸው ለመሆን አልቻልኩም። ለነርሰም ዋናው ደጡት ነገር ቢኖር አባታቸው በአጠገባቸው አለመሆኑ ነበር።

የቅርብ ጊዜ ጥናቶች የሚመክሩት የልጅን ጠባይ በደንብ ለመቅረጽ የመጀመሪያዎቹ የስድስት ወይም የስምንት ዓመታት ወቅት የበለጠ አመቺ እንደሆነ ነው። ጥናቱ ብዙም አያስደንቀኝም፤ ምክንያቱም ከዛሬ 3000 ዓመታት በፊት መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ልጅን

እንዴት መኖር እንደሚገባው ብታላየው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ከዚያ ፈቀቅ አይልም" (ምሳሌ 22፥6) በማለት አስቀምጦልናል።

በአንድ የበጋ ወራት በአውሮፓ ውስጥ ወንጌልን እየሰበክሁ ሳለሁ አንድ ጓደኛዬ በደግነት ስዊዘርላንድ የሚገኘውን ቤቱን እንድጠቀምበት አዋሰኝ። ቤተሰቤም መጣና ተገናኘን። መኪና እየነዳሁ ወደ ግቢው ስገባ የደስ ደስ ያለው ድክድክ የሚል ልጅ አየሁ። ትንሹ ልጃችን ኔድ ነበር። ብዙ ጊዜ ተለይቼአቸው ነበረና ተለወጠብኝና ዘንግቼው ነበር፤ እርሱም አልለየኝም ነበር። እኔም ሆንኩ እሱ መዘንጋታችን ልቤን በሰላት እንደተወጋሁ ያህል ተሰማኝ።

እምሰቱን ልጆቻችንን የማሳደግ አብዛኛው ኃላፊነት በባለቤቴ በሩት ትከሻ ላይ ወድቆ ነበር - እኔ በወንጌላዊነት እንደተጠራሁ እርሷም ይህንን ልጆችን የማሳደግ ጥሪ ተቀብላለች። አብሬአቸው በምሆንበት ጊዜ በተሰየኋቸው ጊዜ ያልሠራሁትን ለማካካስ ማንኛውንም ነገር ለመሥራት እጥራለሁ፤ ነገር ግን ለማካካስ የማልችለው ልጆቻችንን ሲያድጉና ሊለወጡ ማየት ስለማልችል በዚያ የሚገኘውን ደስታ ነው።

በነዚያ ዓመታት የጠበቃቸውንና መልካም ወንዶችና ሴቶች ሆነው እንዲያድጉ ያደረጋቸውን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። በዚህ ዙሪያ ዋጋ የከፈለችው ሩት ስለሆነች ባለውለታ ነች - ከሁሉም በላይ ደግሞ ለጌታ ምስጋና ይገባዋል።

ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው

ልጆቻችንን የእኛ ልጆች ብለን እንጠራቸዋለን፤ ነገር ግን በርግጥ የእኛ ልጆች እንዳልሆኑ ሁልጊዜ እናውቃለን። የእግዚአብሔር ሥጦታ ናቸው፤ ከእኛ ወጥተው የራሳቸውን ቤተሰብ እስኪመሠርቱ ድረስ በአደራ የተሰጡን ናቸው።

ልጆች ካሏችሁ፤ እነሱ ከእግዚአብሔር የተሰጧችሁ ሰላሆነ ከቶ ችላ አትበሏቸው። ኤላው ወንድሙን ያዕቆብን ከብዙ ዓመታት መለያየት በኋላ ሲያገኘው "እነዚህ አብረውህ ያሉት እነማን ናቸው? ብሎ ጠየቀው። ያዕቆብም ሊመልስ፤ ጌታዬ ሆይ! እነዚህ እግዚአብሔር በቸርነቱ የሰጠኝ ልጆች ናቸው" (ዘፍ 33፥5) አለ። ነቢዩ ኢሳያስ ከቤተሰቡ ጋር የኖረው እግዚአብሔርን እጅግ በረሰ

ሕዝብ መካከል ነበር፤ እሱም በድፍረት፤ "እነሆ እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች" በማለት አሳወቀ (ኢሳ 8፥18)።

ልጆቻችን የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው፤ እግዚአብሔር እንዴት እንዳለደግናቸው አንድ ቀን ይጠይቀናል። ለክርስቲያን፤ የቤተሰብ ሕይወት አይመለከተኝም የሚባል አይደለም፤ የደቀመዝሙርነት አስፈላጊ አካል ነው።

እግዚአብሔር ጋብቻን እንደሰጠን፤ ቤተሰብን ደግሞ ሰጥቶናል። ቤተሰቦችን እኛ አንፈጥርም፤ ቤተሰቦች እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀው ዕቅድ አካል ናቸው። የቤተሰብ ሕይወት በአዳምና በሔዋን ተጀመረ፤ የመጀመሪያ ልጃቸው ሲወለድ፤ ሔዋን በመደነቅ፤ "በእግዚአብሔር እርዳታ ወንድ ልጅ አገኘሁ" አለች (ዘፍ 4፥1)። ኢየሱስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ፤ በቤተሰብ ውስጥ ሆኖ በብስለት እንዲያድግና የምድራዊ ወላጆችን ፍቅርና ሥርዓትን እንዲለማመድ የእባቱ (የእግዚአብሔር) ፈቃድ ነበር። እንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት በማስጠንቀቅ የሚናገሩት ቤተሰቦች ስለሚፈርሱበት ጊዜ ነው፤ "ምክንያቱም ሰዎች ራሳቸውን የሚወድዱ ይሆናሉ . . . ተሳዳቢዎች፤ ለገንዘብ የሚሰገበጉ፤ ትምክህተኞች፤ ትዕቢተኞች፤ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፤ ወለታ ቢሶች፤ ሃይማኖተ ቢሶች፤ ፍቅር የሌላቸው ይሆናሉ" (2ጢሞ 3፥2-3)። ቤተሰብ ሲፈርስ፤ ማኅበረሰብ ይፈረካከሳል። አሁን እየኖርንበት ያለው በእነዚያ ቀኖች ውስጥ ነውን?

ቤተሰብ ለምን?

እግዚአብሔር ልጆችን ሰጥቶናል፤ ግን ለምን? ዋናው ምክንያት ቀላል ነው፤ ነገር ግን አንዳንዴ ከአይናችን ይሰወራል፤ *እግዚአብሔር ልጆችን የሰጠን አዋቂ ሰው ሊድገን እንድናዘጋጃቸው ነው*። ከጨቅላነት እንሰቶ አድገው በመጨረሻው ቤታችንን ለቀው እስኪሔዱ ድረስ፤ ልጆቻችን ነፃ ወደ መሆን ያድጋሉ - ይህ ደግሞ መሆን ያለበት ነው። ምንም ነገር ጣልቃ ካልገባ፤ ሕይወት ሙሉ ክብ ይሆናል፤ ያላደግናቸው ልጆች እነሱ ደግሞ በተራቸው ወላጆች ይሆናሉ፤ እናም የኃላፊነት ዱላ ቅብብሎሽ ወደሚቀጥለው ትውልድ ያልፋል። "ባዶ ጎጆ" ለወላጆች የሚያም ቢሆንም፤ አስፈላጊ ነገር ነው።

በእርግጥ፣ ይህ ታሪክ በመሉ እይደለም። ልጆቻችንን ለእካለ መጠን ማዘጋጀት ያለብን እኛ ነን ነገር ግን ይህ ዝግጅት የሚያቅፋቸውን ማሰብ ይገባል።

የምንችለውን ሁሉ የምናደርገው ለአንድ ነገር ነው፣ *በእካል እንዲኖሩ ለማስቻል* ነው። እዲስ ከተወለደው ሕፃን የበለጠ እርዳታ የሚያስፈልገው ወይም የሚፈልግ ደካማ የለም።

አንዳንድ ጊዜ በእድሜ ወጣት የሆኑ እናቶች እናትነት ከአድካሚነቱ ባሻገር፣ ደስታን የሚሰጥ እንደሆነ ይጽፉልኛል። እኔም እናቶቹ አያደረጉ ያሉት እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ሁልጊዜ ላሳያቸው እሞክራለሁ፣ ልጆቹ በሕይወት እንዲቆዩ ክተፈለገ የነርሱ እንክብካቤ በቋሚነት ሊኖር እንደሚገባ እነግራቸዋለሁ። በቅርቡ ፍራንክሊን የተባለው ልጃችን በአፍሪካ በኤድስ ወረረሽኝ ምክንያት ወላጆቻቸውን ያጡና በተሰፋ መቁረጥና በመከራ ውስጥ ያሉ ህጻናትን ለመርዳት ተሰጥቶ እየሠራ ነው። የሚንከባከባቸውን ከማጣታቸው የተነሳ በየዓመቱ በሺህዎች የሚቆጠሩ ህጻናት በሞት አንደሚነጠቁ የሚነግረን ታሪክ ልብ ሰባሪ ነው። እንደ ወላጆች ተግባራችን የሚሆነው፣ ልጆቻችንን *መመገብ*፣ ሊታመሙ ማሳከም፣ መንከባከብ፣ ሊገጥማቸው ስለሚችል አደጋ ማስጠንቀቅ፣ የመሳሳት ናቸው። ይህን የምናደርገው የወጣትነትን እደጋዎች እንዲያመልጡ ለመርዳት ነው። ይህ እግዚአብሔር ከሰጠን ኃላፊነቶች አንዱ ነው።

የስሜትና የአዕምሮ እድገት

እንደ ወላጅነታችን ኃላፊነታችን፣ ለልጆቻችን አካላዊ (ቁሳዊ) ፍላጐት በማሟላት ብቻ አያበቃም። ጤናማ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ሆነው ሊያድጉ ይችላሉ፣ ነገር ግን ይህ ብቻ ከሆነ፣ ለሕይወት አላዘጋጀናቸውም ማለት ነው። ክዚያም በላይ አግዚአብሔር ራሳቸውን የቻሉ እንዲሆኑ እንደፈለገው ልናደርጋቸው አልቻልንም ማለት ነው።

ይህ ሁኔታ አግዚአብሔር ለምን ልጆችን እንደሰጠን ወደሚያሳየን ወደ ሁለተኛው ምክንያት ይመራናል፣ በለሚታቸውና በአዕምሮአቸው እንዲያድጉ እንድንረዳቸው ነው። ካለዚህ፣ ወደ እካለ መጠን ፅድሜ ክልል የሚገቡት፣ የተበላሹና አጥፊዎች በመሆን ለወድቀት በመጋለጥ ነው።

ልጆቻችን በአዕምሮና በስሜት የዳበሩ እንዲሆኑ እኛ የተማርነውን እናስተላልፍላቸዋለን። እንዲሁም ሕይወትን ከሚጐዱ ነገሮች ጋር እንዲጋፈጡ እንረዳቸዋለን፣ ኃላፊነታቸውንም እናስተምራቸዋለን። በተጨማሪም፣ ጤናማ የሆነ ግንኙነት እንዲመሠርቱ እንረዳቸዋለን። ኢየሱስ ክቤተሰቦቹ ጋር አብሮ ሲኖር በነበረ ጊዜ፣ "በእግዚአብሔርና በሰው ፊት የተወደደ ሆኖ በጥበብና በቁመት እያደገ ይሔድ ነበር" (ሉቃ 2፥52)።

ሌላው ልጆቻችን ጤናማና ሚዛናዊ እመስካክት እንዲያዳብሩ ልንረዳቸው ይገባል። እንደምንወዳቸውና በሕይወት ዘመናቸው ልዩ እስተዋፅኦ ሊያደርጉ እንደሚችሉ እንደምናምናቸው ማወቅ አለባቸው። በቅርቡ ከታላላቅ ዮኒቬርስቲ፡ዎቻችን ባንዱ ስለምታስተምር አንዲት ሴት የሰማሁት አለ። በጣም ጐበዝና ታዋቂ ምሁር ስለነበረች የዲፓርትመንት (ክፍል) ኃላፊ እንድትሆን ተጠይቃ ፈቃደኛ አልሆነችም፣ ምክንያቱም በራሷ መተማመን አልነበራትም። ስለ ችግሯዋ ወደ አማካሪ ሄዳ እርዳታ በፈለገች ጊዜ የችግርዋ መንስኤ ወላጅ አባቷ ሁልጊዜ ምንም መሥራት የማትችል ደካማ እድርጎ አሳንሶ ይመለከታት እንደነበር ታወቀ። በጥሩ ሁኔታ የሠራችውን ሥራ ከማሞገስና ከማበረታታት ይልቅ ይወቅሳትና የተሻለ ነገር መሥራት የማትችል ደደብ አንደሆነች በመሰደብ ተሰፋ ያስቆርጣት ነበር። ምናልባት አባትየው ይህን በማድረጉ እየረዳት እንደነበረ ያስብ ይሆናል - ነገር ግን በራስዋ ሳትተማመን ማደግዋ የሚያስገርም ይሆን?

የስሜትና የአዕምሮ እድገት በአንድ ጊዜ ሊፈጠር የሚችል ነገር አይደለም፤ የኛን ጥረት ይጠይቃል። የመጽሐፈ ምሳሌ ፀሐፊ፣ "ልጄ ሆይ ወደ ጥበቤ አድምጥ፣ ጆሮህን ወደ ትምህርቴ መልስ" (ምሳሌ 5፥1) ብሏል። ጥንታዊው የቻይናውያን ብሪት "ህጻን ልጅ እንደ ቁራጭ ነጭ ወረቀት ነው፣ ማንም ሰው ቢጽፍበት ይቀበላል" ይላል። ይህ በተለይ ወላጆች በልጆቻቸው ላይ ሊያደርጉት ስለሚገባ ጉዳይ የሚያመለክት እውነት ነው።

ባህርይን መቅረጽ

አግዚአብሔር ልጆችን የሰጠን ለሌላም ምክንያት ነው፣ አስፈላጊና ከሁሉም በላጭ ምክንያት፣ ግብረገባቸውና መንፈሳዊ ባሕርያቸው ያማረ እንዲሆን በቀረጻ መርዳት ነው።

ልጆች በአካላቸው፣ በአስተሳሰባቸውና በስሜታቸው ጉልማሳ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ግብረገባዊና መንፈሳዊ መለረት ከሌላቸው፣ ዘላቂ መረጋጋት ምን እንደሆነ ከቶ ሊረዱ አይችሉም። ኢየሱስ እንዲህ ዓይነቱን ለው ቤቱን በአሸዋ ላይ በሰራ ሰው አመሳስሏል፣ "ዝናብ ዘነበ፣ ጕርፍም ጎረፈ፣ ነፋስም ነፈሰና ያንን ቤት ገፋው ቤቱም ወዲያውኑ ወደቀ አወዳደቁም እጅግ የከፋ ሆነ" (ማቴ 7፥27)። ልጆቻችን ክፉውን ከደኅ ሳይለዩ ካደኅ . . . በሐቀኝነት ለመኖር ፍላጐት አይኖራቸውም . . . በእግዚአብሔር አምነት አይኖራቸውም . . . ነፍሳቸው ትደኸያለች፣ እንዲሁም በሕይወታቸው የሚበልጠውን ነገር ይዘነጋሉ። "ከዚህ በኋላ ሁሉን ነገር እንደ እውሎ ነፋስ ጠራርገው ይሄዳሉ፣ ለነዚህ አመፀኞች አምላካቸው ጉልበታቸው ነው" (ዕን 1፥11) እንደተባለላቸው ይሆናሉ።

ግብረገባዊና መንፈሳዊ ባህርይ ባንድ ጊዜ የሚገኝ አይደለም፣ እንዲያውም፣ ለሚታዊና አዕምሯዊ እድገት ሊወስደ ከሚገባው ጊዜ በላይ ሊቆይ የሚችል ነው። ልጆቻቸው ለራሳቸው ስለወደፊት ሕይወት ራሳቸው እንዲያቅዱ የሚተውአቸውና ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለግብረገብነት እንደማያስተምሩዋቸው አንዳንድ ወላጆች አልፎ አልፎ ይነግሩኛል። ይህ በጣም ያሳዝነኛል፣ የማዝነው ወላጆቹ ኃላፊነታቸውን በመተዋቸው ብቻ ላይሆን፣ በዚህ ምክንያት ወደፊት በልጆቻቸው ላይ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ስለማወቅ ነው። አነዚህ ልጆች ልክ እንደ ወላጆቻቸው ካለ ምንም ግብረገብና መንፈሳዊ መለረት ያድጋሉ።

ይህ ማለት ግን በልጆቻችን ላይ ዝም ብለን የግብረገብነትና የመንፈሳዊነት መርሃ ግብር እንጭንባቸዋለን ማለት አይደለም፤ ኮምፒዩተር አይደለም፣ የራሳቸው ፈቃድ አላቸው፣ ባደገም ጊዜ፣ ያስተማርናቸውን ላይቀበሉት ይችላሉ። ከሕይወት ምስጢራት አንዱ ነገር በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያደገ ሁለት ልጆች አንዳንዱ የሚመርጠት የሕይወት አቅጣጫ እጅግ የተለያየ መሆኑ ነው፤ አንዱ ክርስቶስን ሲክተል ሌላው ዐመፀኛና የተናቀ ይሆናል። ይህ የሚሆን ነገር ነው።

ልጆቻችንን ልክ እኛ እንደምናደርገው ልናደርጋቸው አንችልም - ነገር ግን ለግብረገባዊና መንፈሳዊ ሕይወት አድገት የሚሆን ትክክለኛና ምቹ ሁኔታን ልናመቻችላቸው እንችላለን። ጥሩውና መጥፎው ምን እንደሆነ እናስተምራቸዋለን - ወይስ ሀሳቡን ከሚያዩት ፊልም እንዲቀስሙ እንተዋቸዋለን? በእኛ

ሕይወት ውስጥ ክርስቶስን ያዩታል? መጽሐፍ ቅዱስ፣ "አንተ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ልታስተምራቸው፣ እንዲሁም እንዴት መኖርና ማድረግ እንደሚገባቸውም ልትገልጥላቸው ይገባል" ይላል (ዘፀ 18፥20)። በተጨማሪም፣ "ለልጆቻችሁም (የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት) አስተምሩአቸው፣ በቤት በምትቀመጡበት ጊዜ፣ ወይም ስትሄዱ፣ ዕረፍት በምታደርጉበትም ሆነ በምትሠሩበት ጊዜ ሁሉ ስለነርሱ ተነጋገሩ" (ዘዳ 11፥19) ይላል።

ፕበበኛ ወላጅ መሆን

ልጆቻችንን ከማሳደግ በላይ አስፈላጊ የሚሆን ነገር እንደሌለ ሁሉ እንደማሳደግ ፈታኝ ነገርም የለም። እያንዳንዱ ልጅ ይለያል . . . አያንዳንዱ ቤተሰብ ይለያል . . . እንደዚሁም እያንዳንዱ ቀን ይለያል። እንዴት አድርገን ነው መልካም ወላጆች የምንሆነው? አኔንና ሩትን የረዱንን አራት መመሪያዎች ልግለጽላችሁ።

አንደኛ፣ ቤተሰባችሁን ለእግዚአብሔር አሰረክቡ (አደራ መስጠት)። ቤተሰብን ማሳደግ እጅግ ከባድ ነው - እናም በጣም አስፈላጊም ነው - ለብቻችን ልንፈጽመው የምንደፍረውም አይደለም። የእግዚአብሔር ጥበብና አርዳታ በየቀኑ ያስፈልገናል። አንድ ጊዜ አንድ ለው ባለቤቴን ሩትን ልጆቻችንን እንዴት እንዳሳደገቻቸው ጠየቃት፣ እርሷም ያለምንም ማወላወል "በጉልበቴ በመንበርከክ!" ብላ መለሰችለት።

ቤተሰባችሁን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት (ማስረከብ) ማለት ምን ማለት ነው? *ቤተሰባችሁ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመሰርቶ እንዲኖር ማድረግ ማለት ነው።* መጽሐፍ ቅዱስ ልጅን የማቅኛ ዝርዝር የእጅ መጽሐፍ አይደለም፤ በሚያስፈልገን በማናቸውም ሁኔታ ውስጥ ምን ማድረግ እንደሚገባን በትክክል አይነግረንም። ነገር ግን ልጆቻችንን የምናሳድግበትን መመሪያ ይሰጠናል፤ ሆኖም ችላ እንላቸዋለን። ለምሳሌ በቆላ 3፥20 "ወላጆች ሆይ፣ ተስፋ አንዳይቆርጡ ልጆቻችሁን በቁጣ አታስመርሩአቸው" ይላል። ይህን መመሪያ እየተከተልን ነው?

ሌላው ቤተሰብን ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠት (ማስረክብ) ማለት ልጆችን ስለ እግዚአብሔር ማንነት ማስተማር ማለት ነው። ልጆቻችን ልጆች በነበሩ ጊዜ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን በቋሚነት (በአብዛኛው በመኝታ ጊዜ) እናነብላቸው ነበር።

በተጨማሪም ከመመገባቸው በፊት በፀሎት እንመራቸው ነበር። አድገው ትልልቅ በሆኑ ጊዜ እያንዳንዳቸው እግዚአብሔር ስለሰጠን ማዕድ የማመሰገን ተራ ተረክበዋል። ከልጆቻችን ጋር አብረን መጸለያችንና ወደ ቤተ ክርስቲያን ይዘናቸው መሔዳችን እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ሥፍራ እንዲያውቁት ረድቶአቸዋል። ከሁሉም በላይ፣ ሳናስልስ እየጸለይንላቸው ሕይወታቸውን ለጌታ ኢየሱስ እንዲሰጡ አናበረታታቸው ነበር። ልጆች የሚማሩት ከምንነግራቸው ብቻ ሳይሆን ከተግባራችንም ጭምር መሆኑን አስተውሰ።

ባለቤቴ ሩትና እኔ ሁልጊዜ ከቁርስ በኋላ በመመገቢያችን ጠረጴዛ ዙሪያ የቤተሰብ የጸሎት ጊዜ ነበረን። ሁልጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ አጠር ያለ ክፍል አንብበን (አንዳንዴም እያንዳንዱ ልጅ አንድ ጥቅስ እንዲያነብ አድርገን) ከተማርን በኋላ የጸሎት ጊዜ ይኖረናል። የቤተሰብ የጸሎት ጊዜን አስደሳች አድርገት፣ ለአጭር ጊዜም ይሁን። አንድ ጊዜ ቤተሰባችንን ሊነበኝ የመጣ ካህን የጸሎት ጊዜአችንን እንዲመራልን እድሉን ሰጠሁትና የካህኑ ጸሎት በጣም ረዘመ። ወዲያውኑ ልጆቻችን መቁነጥነጥና መተራመስ ጀመሩ። በመጨረሻም ታናሹ ልጃችን በጩኸት፣ "አባባ ይሔ በጣም ረዥም ነው!" ብሎ አምቧረቀ።

ጊዜ መስጠት

ሁለተኛው መመሪያ ለቤተሰባችሁ ቅድሚያ መሰጠት ነው። አንዳንድ ወላጆች ይህን ማድረግ ያቅታቸዋል፣ ምክንያቱም ከቤተሰባቸው ይልቅ ለሥራቸውና ለማህበራዊ ኑሮአቸው ቅድሚያ ስለሚሰጡ ነው። አንድ ጊዜ አንድ ባተሌ አባት "የሚፈልጉትን ሁሉ አደርግላቸዋለሁ፣ አላደርግም አንዴ?" ብሎኛል። አባትነቱ የበለጠ የሚሰማቸው በሚገዛላቸው ምርጥ አሻንጉሊት ሳይሆን አብሯቸው በመሆን የሚያሳልፈው ጊዜ ነው። ልጆቻችን ልዩ እንደሆኑ እየተሰማቸው ማደግ ይኖርባቸዋል፣ ባተሌ ሆነን ለእነሱ ጊዜ የሌለን ከሆነ ግን ይህ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም። አንዳንድ ጊዜ ቆም ብለን ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባናል፣ "ልጆቼ የልጅነት ዘመናቸውን ማስታወስ ያለባቸው በምን ዓይነት መልኩ ነው? የልጅነት ጊዜ ትዝታቸው የሳቅና የደስታ ይሆንላቸው ይሆን? ወይስ በቂ ጊዜ ስላልሰጠኋቸው በቅሬታ ያዩኝ ይሆን? "

ልጆቻችን ከሌሎችም ማለትም በዝሪያ ከተያያዘው የቤተሰብ አካላት ብዙ ሊማሩ ይችላሉ። ልጆቻችን ከተጠቀሙአቸው ትላልቅ ጥቅሞች አንዱ ከአያቶቻቸው በተለይ በአቅራቢያችን ይኖሩ ከነበሩት ከሩት ቤተሰቦች ጋር አብረው ያሳለፉት ጊዜ ነው። አብዛኛው የደስታና የፈንጠዝያ ዘመን ትውስታቸው ከእነዚህ አያቶቻቸው ጋር ባሳለፉት ጊዜ ላይ የተመሰረተ ነው።

ብዙ ቤተሰቦች በችግር ውስጥ የሆኑበት አንዱ ምክንያት ቀደም ሲል የወላጆቹ ወላጆች (አያቶች) የፊፀሙትን ስህተት የአሁኖቹ ወላጆች በተራቸው በመድገማቸው ነው። ነገር ግን እንዲህ መሆን አይገባውም። ባንድ በሚነቀፍ ቤተሰብ ውስጥ ያደገና በየዘመዱ ቤት አየተንከራተተ የኖረ አንድ የማውቀው ሰው ነበር። ይህ ሰው በጣም በሚጠነቀቅለት ባንድ የሰንበት ትምህርት ቤት አስተማሪ በኩል ጌታን አገኘ። በመጨረሻም ቤተሰብ መሰርቶ ወላጅ ሲሆን፣ ከወላጆቹ በተሻለ ሁኔታ ቤተሰቡን ለማስተዳደር ቆርጦ ተነሳ፣ አደረገም። እንዲህም አለኝ፣ "የቤተሰብህን ዓይነት መርጠህ መውለድ አትችልም፣ ነገር ግን ለልጆችህ ምን ዓይነት ቤተሰብ መመሥረት እንዳለብህ ልትመርጥላቸው ትችላለህ።" ብዙ ወላጆች የዚህ ሰው ዓይነት ጥበብ ቢሰጣቸው ምኞቴ ነው።

በፍቅር መተሳሰር

ሶስተኛው መመሪያ ይህ ነው፣ የቤተሰባችሁ ማዕከል ፍቅር ይሁን። ልጆቻችሁን ውደዱ፣ እንደምትወዷቸውም እንዲያውቁ አድርጉ። እግዚአብሔር ይወዳቸዋል፣ እናንተም እንዲሁ አድርጉ መፈቀርን የሚለማመዱ ልጆች እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው ለማመን ይቀላቸዋል።

ደግሞም አበረታቷቸው። ባለቤቴ ሩት በግሷ በምታሳትመው የልጆች መጽሔት (ሀሳቦቿንና ጸሎቶቿን በምትጽፍበት ማለት ነው) ላይ አንድ ጊዜ፣ "የተከበርክ መጽሔት፣ እያንዳንዱን ልጅ የሚያበረታታ አንዳች ቃል ሳትናገር አንዲት ነጠላ ቀን እንኳን አትሰፍ . . . ብዙ ሰዎች ከማንኛውም ምክንያት የበለጠ በማበረታታት ጉድለት የተነሣ ይወድቃሉና" በማለት አንዱ ጽፎልናል" በማለት ትዕፍ እንደነበር ትዝ ይለኛል።

ፍቅር ማለት ልጆች የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ መስጠት ማለት አይደለም። ፍቅር ማለት አንዳንድ ጊዜ "አይደለም" ወይም

"አታድርግ" ማለትን ይጨምራል፤ ምክንያቱ ልጆቻችንን ስለጠላናቸው አይደለም፤ ስለምንወዳቸውና ከእነሱ በተሻለ ለእነሱ ጠቃሚ የሆነውን ነገር ለይተን ስለምናውቅ ነው። ልጆቻችን፣ ወደዱም ጠሉም፣ የማስተካከያ እርምትና ሥነ - ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል፣ ሕይወት በሀግና በስርዓት የተሞላች ናት። ወላጆች ከምንፈጽማቸው በጣም የከፉ ነገሮች አንዱ ለልጆቻችን ሕግን ለማክበር ግዴታ ላይኖራቸው አንዲያድጉ መፍቀዳችን ነው። ሞልቃቃ ልጅ ሞልቃቃ አዋቂ ይሆናል።

ብዙ ልጆች (ወጣቶችንም ይጨምራል) መመሪያና ሥነ - ሥርዓት የሚያስፈልጋቸው ሆኖ አግኝቻለሁ። በስንፍና ሲገደቡ እንኳን፣ "ተው! ይህን ብታደርግ በጣም አወድሃለሁ" ለማለት የሚፈልገውን ወላጅ ያደንቃሉ። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ልጆችህን በልጅነት ቅጣቸው፣ ባትቀጣቸው ግን ለጥፋት አሳልፈሀ አንደለጠሃቸው ይቆጠራል ይላል" (ምሳ 19፥18)።

ልጆችን ሥርዓት ለማስተማር ቋሚ የሆነ ቁጣ ወይም ንግግር ወይም አካላዊ ቅጣት ማለቴ አይደለም። አንድ ልጅ ሥርዓት እንዲኖረው ሲደረግ፣ ስርዓቱ ለምን እንዳስፈለገ ማወቅ ይገባቸዋል። ልጆች አንዱ ከሌላው ይለያሉ፤ ከልጆቻችን አንዱ የተቃውሞ ምልክት ካየ ይበቃዋል፣ ሌሎቹ ግን ጠንካራ ርምጃ ይሻሉ። ሥነ ሥርዓት ማለያዝ የፀና፣ ትክክለኛና ሚዛናዊ፣ ጤነኛ እና ቀጣይነት ያለው መሆን ይገባዋል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ልጅ ለድ አደግ የሆነ እንደሆነ ግን እናቱን ያሳፍራል ... ልጅህን ብትቀጣ ዕረፍትና ለሳም በማግኘት ደስ ትለኛለህ" ይላል (ምሳሌ 29፥15፣ 17)።

የተከፈተ በር

በመጨረሻም፣ በሩን አትዝጉ። አንድ ቀን ልጆቻችሁ ጥለዋችሁ ይሔዳሉ፤ አስከ መጨረሻው በናንተ ሥር ሊሆኑ ወይም ልትቆጣጠሩአቸው አትችሉም፣ ልታደርጉትም አይገባም። ነገር ግን ይህ የግንኙነታችሁ መጨረሻ እንዲሆን አትፍቀዱ!

ግንኙነታችሁ መልካም እንደነበረ ይታሰባል፣ በመሆኑም ልጆቻችሁን ባርካችኋቸው ይሄዳሉ። ይሁን እንጂ፣ ምናልባት አንዳንዶች አባካኞች ሊሆኑ ይችላሉ።

ሁለቱ ወንዶች ልጆቻችን ወደ አመፀኝነትና አደገኛ ባህርይ ውስጥ በገቡ ጊዜ ከአንድ ሌሊት በላይ ያለ እንቅልፍ የሆንንበትና አብዝተን ለመፀለይ የተገደድንበት ጊዜ ነበር። በዚያን ጊዜ ሁሉም ልጆቻችን ተስፋ በመቁረጥ ወይም በጉዳት ውስጥ ያለፉበት ጊዜ ነበር። ነገር ግን ምንጊዜም እንደምንወዳቸው ያውቁ ነበርና ወደ ቤታቸው ተመልሰው መጥተዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ አምላካዊ (በጐ) መሪ ለዕል አምላካዊ ቤተሰብን ይገልጻል፤ "ለውን ከነፋስ እንደ መሸሸጊያ ከዐውሎ ነፋስም እንደመጠጊያ፤ በጥም ቦታም እንደ ወንዝ፣ በበረሃም አገር እንደ ትልቅ ድንጋይ ጥላ ይሆናል" (ኢሳ 32፥2)። ይህ በቤታችሁ አውን ይሁንላችሁ።

ይህን ምዕራፍ እንዳነበባችሁ፣ ራሳችሁን በጸጸት ውስጥ ወይም ደግሞ በሐዘን ውስጥ አለበለዚያም በቁጣ ተሞልታችሁ ታገኙት ይሆናል። ምናልባትም ስታስተዳድሩት የነበረው ቤተሰብ ከሚዛኑ ጐድሎባችሁ ወይም እንደ ድካማችሁ አልሆነም ይሆናል፣ ወይም ምናልባት ቤተሰባችሁ በአሁኑ ለዓት በውዝግብ ወይም ልብ በሚሰብር ምክንያት ፈርሶባቹሁ ልትሆኑ ትችላላችሁ። በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብትሆኑ፣ በታማኝነት ተጋፈጡት፣ ከዚያም ለጌታ ኢየሱስ አስረክቡት። ላለፈ ነገር ባሪያ አትሁኑ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ቤተሰባችሁን እንዲረዳና እርሱ እንደፈለገው እንዲሆን ለምኑት።

ሃያ ስምንት

ተፅዕኖ ማምጣት



እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ... መልካሙን ሥራችሁን ሰዎች በሰማይ ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ ::

(ማቴ. 5፥14፤16)

እግዚአብሔር ልክ ሕይወታችንን ለክርስቶስ በሰጠንበት ቅጽበት ለምን ወደ መንግስተ ሰማያት አይወስደንም?

ከሁሉም በላይ፣ መንግስተ ሰማይ የመጨረሻው መኖሪያችን እስከሆነ ድረስ፣ እግዚአብሔር ወደዛው ቢወስደንና ከችግርና ከመከራ ወዲያውኑ ቢገላግለን የተሻለ አልነበረምን? ከዚያም ጭንቀት ወይም ኀዘን ወይም ሥቃይ እያገኘንም ነበር፣ ከመከራ ሽክሞቻችንና ፈተናዎቻችን በተወገዱልን ነበር:: *ሕይወታችንን ለክርስቶስ ባስረከብንበት ቅጽበት እግዚአብሔር ወደ መንግሥተ ሰማይ ያልወሰደን ግን ለምንድነው?*

ምክንያቱ ቀላል ነው፤ *እግዚአብሔር እዚህ ሰኛ ሥራ አለው*:: መንግሥተ ሰማይ ግባችን ነው፣ እስከዚያ እስክ መጨረሻው ጊዜ እርስ ወዳስበት እስኪወስደን፣ እግዚአብሔር እዚህ የሚያቆየን በዓላማ ነው:: ምድር፣ ወደ መንግሥተ ሰማይ ከመግባት በፊት፣ ልክ እንደ መጠባበቂያ (መቆያ) ክፍል አይደለችም፣ ያለምንም ሥራ ተቀምጠን የመጨረሻው የመሔጃችን ሰዓት እስኪመጣ እጃችንን እጣጥፈን የምንቆይባት አይደለችም:: ምድር፣ የዘመናት ቲያትር (ታሪክ) የሚተውንባት መድረክ ናት:: ትዕይንቱ ክርስቶስ በኃጢአትና በሞት፣ በሰይጣንና በሲያል ላይ ድልን የተቀዳጀበት ታሪክ ነው:: ማን የመሆናችን ጉዳይ ሳይሆን መለከታዊ ድራማውን ለመጫወት ከእግዚአብሔር የተሰጠን ልዩ ተግባር ደስን ነን::

መለኮታዊ ዓላማ

እግዚአብሔር ለኛ የሰጠን ልዩ ተግባር ምንድን ነው? አዚህ ምድር የሚያቆየን ለምንድን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ መልስ አለው፤ *በምድር ላይ እስካሰን ድረስ፣ እግዚአብሔር ለኛ ያሰው ዓላማ፣ ምንም ዓይነት ይሁን ምን በኑሮአችን ሰርስ ክብርና ምስጋና እንድንሰጠው (እንድናመጣስት) ነው*:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ እግዚአብሔር፣ "ቅዱሳንና ነቀፋ የሌለብን ሆነን በፊቱ እንድንገኝ ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ መረጠን . . . ይህም የሆነው በመጀመሪያ በክርስቶስ ተስፋ ባደረግነው በእኛ ምክንያት ለእግዚአብሔር ክብርና ምስጋና እንዲሆን ነው" (ኤፌ 1፥4፤12):: ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ፣ "ብዙ ፍሬ ስታፈሩ አባቴ ይከበራል፣ በዚህ ዓይነት የኔ ደቀመዛሙርት መሆናችሁን ታስረዳላችሁ" (ዮሐ 15፥8) አላቸው:: ግባችሁ፣ በምታደርጉት ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር ለመስጠት ነው?

ነገር ግን ይህ ብቻ ለመሠረታዊ ጥያቄአችን ሙሉ መልስ ሊሆን አይችልም:: እግዚአብሔር እዚህ አንድንቆይ ያደረገበት ምክንያት ምንድነው?

ይህን ጥያቄ ለመመለስ፣ እግዚአብሔር ራሳችንን ለክርስቶስ እንደሰጠን ወዲያውኑ ወደ መንግሥተ ሰማይ ቢወስደን ይህች ምድር ምን ልትመስል እንደምትችል ገምቱ:: የክርስቶስን የማዳን ኃይል ርኅራኄውንና ጽድቁን የሚናገር ባይኖር ኖሮ፣ (ያመኑት ደስ ቀሪ የሚሏዱ ቢሆን ኖሮ)፣ ይህች ዓለም ምን ዓይነት ትሆን ነበር? የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚገልጽ ማንም በሌለበት፣ ስለክርስቶስ እንዲሉት አድርገው ሲሰሙ ወይም እምነታቸውን በርሱ ላይ ሊያደርጉ ይችሉ ነበር? መልሱ ግልጽ ነው፤ ዓለማችን ዘላቂ በሆነ መንፈሳዊ ጨለማ፣ ለዘላለም በፍርሃት፣ በተስፋ ቢስነትና በክፋት ውስጥ እንድትኖር የተረገመች በሆነች ነበር::

ታዲያ እግዚአብሔር እዚህ የሚያቆየን ለምንድነው? የሚያቆይበት ምክንያት አለው፤ ሰዓለም ምሥራቹን ቃል እንድንናገር ያቆየናል:: የምሥራቹ ቃል የክርስቶስ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን አስደናቂ ሥራ እንድታውጁ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ እግዚአብሔር ለራሱ ያደረጋችሁ ቅዱስ ህዝብ ናችሁ" (1ኛ ጴጥ 2፥9):: ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ

የሰጠው ትዕዛዝ ከቶ አልተሻረም፤ "ወደ ዓለም ሁሉ ሒዱና ለለው ሁሉ ወንጌልን አስተምሩ" (ማር 16÷15)።

ይህ ማለት ሁላችንም ለባሕያዎች ወይም የወንጌል መልዕክተኞች ወይም ሚስዮናውያን እንሆናለን ማለት ነው? አይደለም - ለጥቂቶች ግን ነው። ነገር ግን ሁላችንም የክርስቶስ ምስክሮች ለመሆን ተጠርተናል፣ የርሱን ፍቅርና የሚለውጥ ኃይሉን ወደ ፈራረሰውና ወደ ተመሠቃቀለው ዓለም ልናመጣ ነው የተቀመጥነው።

የሸንድ ሰው ተፅዕኖ

"ዐመፅ በቸርነት ላይ" የሚል ታሪክ ለዘመናት አንባቢዎችንና ፊልም አፍቃሪዎችን ያስደነቀ ታሪክ ነበር። ክዚያ በኋላ የሆነው ግን ክአስገራሚነቱ አልፎ በታዋቂነት ተርታ አልተፈረጀም።

ባንዳንድ ምክንያቶች አሁንም አከራካሪ የሆነ ሁኔታ በ1789 ተፈጽሞ ነበር፣ መርከብ ሠራተኞች የመርከቡ ካፒቴን ባሳየው የጭካኔ ተግባሩ ምክንያት ዐመፀቡት። ዊሊያም ብሊፍ የተባለው ይህ ካፒቴን ክዐመፀ ለማምለጥ ክጥቂት ለዎች ጋር ሆኖ መርከቡን ጥሎ በጀልባ ሸሸ። አማጺያኑ ግን በመርከቢቷ ላይ ቀሩ፣ በመጨረሻም ማንም የማይናርባትና የተነጠለች፣ በሰላማዊ (ፖስፊክ) ውቅያኖስ በደበባዊ ክፍል የምትገኝ፣ "ፒትካይርን ደሴት" አግኝተው ደረቅ መሬት ላይ ወረዱ። ቁጥራቸው ሃያ አምስት ነበር፣ ክነርሱም ዘጠኙ እንግሊዛውያን መርከበኞች ሲሆኑ ቀሪዎቹ ለድስት ወንዶችና አሥር ሴቶች የታሂቲ ዜጎች ነበሩ። ከመርከቢ ክወረዱ ከጥቂት ለዓታት በኋላ መርከቢን ፈጽመው አቃጠሏት፣ ክዚያም በደሴቲቱ ላይ በቋሚነት ሠፈሩ።

ነገር ግን ይህ መክሬቸው ብዙም ሳይቆይ ትልቅ አደጋ ገጠመው። አስቸጋሪ በሆኑ አንግሊዛውያን መርከበኞች እና በታሂታውያን መካከል ክፍተኛ ግጭት ተፈጠረ፣ አለመግባባታቸውም ተካሮ ወደ መገዳደል መራቸው። አንዱ እንግሊዛዊ መርከበኛ ደግሞ ከዕዕዋት ጨምቆ የአልኮል መጠጥ ማዘጋጀት ጀምሮ "ሞቃታማ ገነት ናት" ያሏትን ደሴታቸውን የለካሮች፣ የብልሹ ምግባርና የወራዳነት ሠፈር እደረገው። ከአምስት የማይበልጡ ታሂቲዎችና አንድ እንግሊዛዊ መርከበኛ "ጆን አዳምስ" የተባለ ብቻ ተረፉ።

አንድ ቀን ጆን አዳምስ መርከቢን ሲያቃጥሏት ሳይቃጠል የተረፈና በመርከቢ ውስጥ ያገኘውን፣ ግን ለብዙ ጊዜ ረስቶት የነበረውን፣ መጽሐፍ ቅዱስ እንሶ ማንበብ ጀመረ። አግዚአብሔርም ቃሉን በመጠቀም ጆን አዳምስ ኃጢአተኛ እንደሆነ በማመን ንስሃ እንዲገባና በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምን መራው። የጆን አዳምስ ሕይወት በአስደናቂ ሁኔታ ተለወጠ፣ ክዚያም ምንም ያህል ሳይቆይ ለስደተኛ ጓደኞቹ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያካፍላቸው ጀመር። የተለወጠው የጆን አዳምስ ሕይወትና ያካፈላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት እነሱንም ለወጣቸው። በ1808 ወደዚች አነጀን አዳምስ ወደሚኖሩባት ፒትካይርን ደሴት በመምጣት ለመጀመሪያ ጊዜ የጉበኙት አሜሪካውያን መርከበኞች ነበሩ። ጉብኚዎቹ ያገኙት ማኅበረሰብ አጅግ የበለፀገና ፍጹም ተስማምቶ የሚኖር፣ ወንጀል የሌለበት፣ አስር ቤት የሌለበት፣ የአልኮል መጠጥ የሌለበትና የሥነ ምግባር ጉድለት የማይታይበት ማህበረሰብ ነበር። እግዚአብሔር የአንድን ሰው ምስክርነት ተጠቀመ፤ ግዛቱን በሙሉ ለመለወጥ የጆን አዳምስን ተፅዕኖ ተጠቀመ።

ሁሉም ክእንቅብ በታች ናቸው

የጆን አዳምስን ሕይወት ያለው ምስክርነት ተላላፊ ነበረ፣ ክዚህ በጣም በተቃረነ መልኩ አንዲት ሴት የጻፈችልኝ ደብዳቤ እንዲህ የሚል ሀሳብ ነበረው። ባለቤቷና እርስዋ ሃይማኖት የለሾችና "ወደ ቤተክርስቲያን በጭራሽ ሔደን አናውቅም፣ ምክንያቱም አብዛኞቹ ዘመዶቻችን ክርስቲያን እንደሆኑ ይነግሩናል፣ እንዲህ ነን አያሉ ግን ጋብዘውን አያውቁም ወይም የልደት ካርድ አይልኩልንም ወይም እንዲያውም ታምሜ በሆስፒታል ተኝቼ ሳለሁ እንኳን አልጎበኙኝም። ይህን ለምን አንደሚያደርጉብን አንደኛዋ ዘመዴ ክርስቲያኖች ስላልሆንን እንደሆነ ነግራኛለች። የክርስቲያኖች ተግባር ይህ ክሆነ፣ ክነርሱ ጋር ምንም ነገር ለማድረግ አልፈልግም" ይላል።

ወደ ክርስቶስ አንድትመለክት አጥብቄ አስገነዘብኳት፣ ምክንያቱም እርሱ ብቻ ፍጹም ስለሆነና እርሱ ብቻ ክቶ የማያስቀይመን ስለሆነ ነው። የሴትየዋ ደብዳቤ ግን አቀዝቅዞኛል፣ በተሰማት ጉዳይ ስለ ወሰነችው ውሳኔ ልወቅሳት አልቻልኩም። ክዚህ ሁሉ በኋላ፣ የክርስቶስ ተከታይ ነን የሚሉ ሳይወዷት እንዴት ክርስቶስ ይወደኛል ብላ ልታምን ትችላለች? እነዚያ ዘመዶቿ እውን ክርስቲያኖች መሆናቸውን አላውቅም፤ ክሆኑ ግን እግዚአብሔር ለምን በዚህ ምድር አንዳስቀመጣቸው ፈጽሞ አልተረዱም።

እንደዚህ ዓይነት ሰዎች፣ ሌሎችን ወደ ክርስቶስ በመማረክ ፈንታ ጀርባቸውን ወደ ክርስቶስ አንዲመልሱ ያደርጋሉ።

ወደ ኢየሱስ በመጣን ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከዚህ ዓለም ኃጢአትና ምስቅልቅል ነፃ አውጥቶናል። ግን ታዲያ መልሶ ወደ ዓለም ይልክናል የሚልከንም ተመልሰን ኃጢአት ልንሠራና ጨለማ የሆነው መንፈሳዊ ዓለም ሥራ ተሳታፊዎች እንድንሆን አይደለም፣ ነገር ግን ለክርስቶስ ብርሃን ምስክሮች እንድንሆን ነው። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ "አብ እኔን እንዳሰከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ" (ዮሐ 20፥21)። ደቀመዛሙርቱንም በተመለከተ ፀልዮላቸዋል፣ "ከክፉው (ሰይጣን) እንድትወገዱልቃቸው እንጂ ከዓለም ውጪ እንድትወስዳቸው አልለምንም" (ዮሐ 17፥15)። መጽሐፍ ቅዱስ እማኞችን በጨው፣ በመብራት በእርሾና በዘር ያወዳድረናል። ከነዚህ እንዳቸውም ቢሆኑ በመጋዘን ውስጥ ተቀልፎባቸው ቢቀመጡ ምንም ጥቅም የላቸውም። ተጠብቀው ሊቀመጡ ይችላሉ፣ ግን ዓላማቸው ለመቀመጥ አይደለም። ጨው ምግብን በማጣፈጥና እንዳይበላሽ በማድረግ ያገለግላል፤ መብራት ብርሃን እንዲሰጠን፣ ጨለማን በመግፈፍና መንገዳችንን በማብራት ይጠቅማል፣ እርሾም ዱቄታችን እንዲቦካና ጥሩ ዳቦ ተጋግሮ እንዲበላ ይረዳል፤ ዘር ደግሞ ይዘራና ሰብል ሆኖ ፍሬ ያፈራል።

የኛም ጉዳይ እንዲሁ ነው። እንዴት ፀጥ ብለን እንደማይመለከተን ሆነን እንቀመጣለን? ለሌሎች በማካፈል ፈንታ እንዴት ወንጌልን ከአንቅብ በታች እናኖራለን? እንዲህ ማድረግ ማለት እግዚአብሔር አኛን ያኖረበትን ዓላማ መርሳት ነው። ኢየሱስ፣ "እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ፣ በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም፣ መብራት አብርቶ እንቅብ የሚደፋበት ማንም የለም፣ ይልቅስ በቤት ውስጥ ላሉት ሁሉ አንዲያበራ በሚታይበት በክፍተኛ ቦታ ላይ ያደርገዋል" (ማቴ 5፥14-15) ብሏል። ሐዋርያው ጳውሎስ በርም የሚገኙ ክርስቲያኖችን የእምነታችሁ ዝና በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማ ከሁሉ አስቀድሜ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ስለ ሁላችሁ አምላኬን አመሰግናለሁ (ሮሜ 1፥8) በማለት አመሰገነ። በተሰሎንቄ ያሉ ክርስቲያኖች በተቃዋሚዎቻቸው ኃይለኛ ስደት ደርሶባቸው እያሉ ጳውሎስ ግን እንዲህ፣ "የእግዚአብሔር ቃል ከአናንተ ወጥቶ የተሰማው በመቄዶንያና በአካይዳ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ያላችሁ እምነት

በሁሉ ቦታ ታውቆ ነበር፤ በዚህ ምክንያት እኛ ስለዚህ ጉዳይ ምንም መናገር አያስፈልገንም" (1ኛተሰ 1፥8) በማለት ጽፎላቸዋል።

ልባቸው ወደ ተሰበረ ሕዝቦች መድረስ

እንዳለመታደል ሆኖ፣ ብዙ ክርስቲያኖች ከሳይ አንደጠቀስኳት ሴት ዘመዶች ዓይነት ናቸው፤ ስለ ሌሎች ሰዎች ግድ የሌላቸውና ስለ መንፈሳዊ ደህንነታቸውም ምንም የማይገዳቸው ናቸው። እንዳንዶች ደግሞ ግድ ልላቸው እንደሚገባ የሚያውቁ ቢሆንም ምን ማድረግ እንደሚገባቸው እያውቁም። ይህ ሁኔታ እንዴት ሊለወጥ ይችላል? በዚህች በጉስቁልና ባለች ዓለም ለክርስቶስ ተዕዕኖ ማምጣት እንዴት እንችላለን?

እንደኛ፣ እግዚአብሔር ዓለምን በሚያይበት አይን (መንገድ) ማየት እንድትችሉ እንዲረዳችሁ በጸሎት ጠይቁት። በዙሪያችሁ ያሉ ሰዎች ሁሉ ኃጢአት ባስከተለው መዘዝ በአንድም ሆነ በሌላ ስብራት ያሰባቸው፣ ኑሮአቸው የተበተነና የከፋባቸው ናቸው። ለሌሎች ደግሞ ሕይወት ቁሚና ማብቂያ የሌለው ትግል ናት። እግዚአብሔር ስለ እነሱ ግድ ይሰዋል? እኛስ?

እንድ ሰው በቅርቡ ለአጭር ጊዜ ተልዕኮ ወደ እንድ በጦርነት በድርቅና በበሽታ በእድጉ ወደ ተጎዳች ደሃ ሀገር ሔዳ ሰሰ ነበር አንዲት የኮሌጅ ተማሪ ነገረኝ። ተማሪዋ ባየችው ነገር ስሰቀፈፋት ወደ ነበረችበት ኑሮዋ ለመመለስ ችኩላ ነበር። በዚህ ሀሳብ ውስጥ አያለች ግን ከችጋር የተነሣ ሊሞት አያጣጣረ ያለ ልጅ በእጇ ላይ እቀፈችው። ይህ ሕፃን በሞት አፋፍ የነበረ ከመነጫነጭ በስተቀር ምንም ማድረግ የማይችል የደከመ ነበር፣ ይህ ሁኔታ በድንገት ልሏን ሰበራት። ይህ ሕፃን በሕይወት ዘመኑ ዳግመኛ ለአንድ ጊዜ እንኳን ፈገግ ላይል መሞቱ ልሏን ነካት። ወዲያውኑ በዙሪያዋ ያሉትን ሰዎች አያመተረች ፍጹም በተለየ ፍቅር መመልከት ጀመረች።በቀሪ የሕይወት ዘመኗም በክርስቶስ ዓይን አማካይነት መመልከት ጀመረች። እንደነዚህ ዓይነት ችግር ባለባቸው ቦታዎች ሁሉ አየተዘዋወረች የተጎዱ ሰዎችን በመርዳታ ልታገለግል ራሷን አሳልፋ ሰጠች፣ ሌሎችንም በክርስቶስ ስም ለመርዳት ወሰነች።

ሰዎችን በራሳችን አይታ ስንመለከታቸው፣ ዋጋ የምንሰጣቸው ለአኛ ምን ሊያደርጉልን ይችላሉ በሚል ሀሳብ አቅጣጫ ብቻ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያየው በተለየ

መልክ ነው። እኛም ማድረግ የሚኖርብን እንዲሁ ነው። ጳውሎስ እንዲህ ሲል ጽፏል፣ "አንድ ጊዜ ክርስቶስ ለሁሉም መሞቱንና ሁሉም የእርሱ ሞት ተካፋዮች መሆናቸውን ስለተረዳን የክርስቶስ ፍቅር ለሥራ ይገፋፋናል . . . በሕይወት ያሉ ሁሉ ለነርሱ ለሞተውና ከሞትም ለተነሣው እንዲኖሩ እንጂ ከንግዲህ ወዲህ ለራሳቸው ሲሉ እንዳይኖሩ ክርስቶስ ለሁሉም ሞተ። ስለዚህ ካሁን ጀምሮ ማንንም ቢሆን በሥጋዊ አመለካከት ከንግዲህ አናይም፤ ከዚህ በፊት ክርስቶስን ያየነው በሥጋዊ አመለካከት ቢሆንም ከንግዲህ ወዲህ የምንመለከተው በዚህ ዓይነት አይደለም" (2ኛ ቆሮ 5÷14-16)።

ጳውሎስ ሁል ጊዜ በእንዲህ ዓይነት መንገድ አያስብም፤ አንድ ጊዜ ክርስቲያኖችን ስለጠላ ለትንሽ ጥቅም ብዙ ይሮጥ ነበር። እግዚአብሔር ግን ልቡን ለወወሰስትና ክርስቶስን ያሳወቁ ሁሉ ያውቁት ዘንድ ሸክም ተቀበለ። የእግዚአብሔር ፍቅር መንፈሱን ሞላው፤ እግዚአብሔር ለሥችን በሚያይበት መንገድ አየ፤ በለሥች ላይ የእግዚአብሔር ፍቅር እንዳረፈ ተመለከተ። እርሱም አፈቀረ። ይህ በእናንተም ሕይወት እንዲሆንላችሁ እግዚአብሔርን ጠይቁት።

የሚሠሩቹን ቃል መኖር

ለክርስቶስ ተፅዕኖ ለማምጣት ሁለተኛው አስፈላጊ ነገር፣ በምንኖረው ሕይወት ወይም በምንናገርበት ሁኔታ ሁሉ የክርስቶስን ፍቅር ማሳየት ነው።

የብዙዎቹ የጥንት ክርስቲያኖች ትልቁ ችግር ከማያምኑ ጋር ጋብቻ መፈፀማቸው ነበር። ከማያምኑ ጋር እንዴት ሊገባቡ ይችላሉ? ይልቁንም ከመጨቃጨቅ፤ በሚኖሩት ኑሮ ምሳሌ በመሆን ለማግባባትና ለማሸነፍ እንዲነሳሱ ሐዋርያ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ጽፎላቸዋል፣ "እንዲሁም እናንተ ሚስቶች ሆይ፣ ለባሎቻችሁ ታዘዙ፣ በዚህ ዓይነት ገና በእግዚአብሔር ቃል የማያምኑ ባሎች ቢኖሩም በቃል ምስክርነት ብቻ ላይሆን በሚሰቶቻቸው የሕይወት ምስክርነት ሊመለሱ ይችላሉ። ይህንንም የሚያደርጉት ንፁህ የሆነውንና ለው አክባሪ ሕይወታችሁን ሲመለከቱ ነው" (1ጴጥ 3÷1-2)። ሕይወታቸው የትዳር ጓደኞቻቸውን ወደ ክርስቶስ ሊያመለክት የሚችል ምስክርነት የሌለው ስብከት ነበር። በኛም ግንኙነት ተመሳሳይ መርህ ተግባራዊ ሊሆን ይገባዋል።

ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር የርሱን ፍቅር ብዙ ግልጽ በሆኑ መንገዶች እንድናሳይ ይፈልጋል። በማንኛውም ጊዜ ኃጢአት ለጥፋት በቁጭት ሲወጣ፣ የሚለውጠውን የክርስቶስን ፍቅር ተግባራዊ ለማድረግ መለፈግ አለብን። ይህንን ዓለም ከቶ እንከንየለሽ ሥፍራ ልናደረገው አንችልም፤ ይህ ሊሆን የሚችለው ክርስቶስ በክብርና በግርማ ተመልሶ ሲመጣ ብቻ ነው። እኛ ግን የተሻለ ስፍራ ልናደርገው ተጠርተናል፣ ጥሪአችን የለምችን ሥቃይ ለመቀነስ የቻልነውን ሁሉ በማድረግና ለብአዊ በደሎችን በመዋጋት እንድንሠራ ነው። ከቁጥጥራቸው ውጭ በሆነ መንገድ የተቸገሩትን፣ የደኸዩትን፣ በበሽታ፣ በመንይምነት፣ በድርቅና በርሃብ፣ በአየር ንብረት መዛባት፣ በዘረኝነት፣ በሁከትና በጦርነት የተጐዱትን ሕዝቦች ሸክም ለመሸከም ከለምች ሁሉ ይልቅ፣ ክርስቲያኖች ኃላፊነት አለባቸው። ምናልባት እግዚአብሔር እነዚህን ችግሮች ለብቻችሁ ወይም ብዙ ሆናችሁ እንድትዋጉ ሊጠራችሁ ይችላል። ችግራቸውን ለመቀነስ እየሠሩ ያሉትን በክርስቶስ ስም ቢያንስ በጸሎታችሁና በገንዘባችሁ ልትደግፉአቸው ይገባል። ይህንን ካደረጋችሁ የክርስቶስን ርኅራኄ ለሌሎች ታሳያላችሁ፣ እንዲሁም ለወንጌል በር ታስከፍታላችሁ። ጌታ ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ በእውነት እላችኋለሁ፣ "የኔ ደቀመዝሙር በመሆኑ ከነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ አንድ ብርጭቆ ቀዝቃዛ ውኃ እንኳ የሚሰጥ እውን ዋጋውን አያጣም" (ማቴ 10÷42)።

በምትኖሩት ሕይወት ሌሎች ክርስቶስን ያዩታል? እንዲት ሴት፣ "ጓደኛዬ ክርስቲያን ነኝ ትላለች፣ ግን ከዚህ በፊት አይቼው የማላውቀው የባሰባት አስባልተኛና ሔሜተኛ ናት። ክርስቲያኖች የሚያደርጉት እንዲህ ነው?" በማለት በመጠየቅ ጽፋልኛለች። ሌላው ሰው ደግሞ "የእህቴ ልጅ ክርስቲያን ነኝ ይለኛል፣ ነገር ግን ሁልጊዜ በለሥች ላይ የሚያማርርና ስህተት የሚፈልግ ነው። ይህ ስህተት አይደለምን?" ብሎኛል። ለሥች የሠራነውን ስህተት ነቅሰው ለማውጣት ፈጣን ናቸው - በዚህም ምክንያት ክርስቶስን ለመተው ሰበብ ያደርጋሉ፣ ወደኋላም ይመለሳሉ። አንድ እውነት የሆነ ጥንታዊ አባባል አለ፣ "ከምንለው ይልቅ የሆንነው የበለጠ ይናገራል።"

የምሥራቹን ቃል መናገር

ይህ ለክርስቶስ ተፅዕኖ ሰማምጣት ወደምትችሉበት የመጨረሻ መንገድ ያመጣችኋል፣ አምነታችሁን ለሌሎች ማካፈልን ተማሩ።

ጥሩ ኑሮ መኖር ብቻውን በቂ አይደለም። ወንጌል ምን እንደሆነ ለምች ሁሉ ሊረዱ ይገባቸዋል። ሊረዱት የሚችሉት ሌላ ሰው ሊነግራቸው ብቻ ነው። ወንጌል ጣዕም አለው፣ ስለዚህ ሰምች ሊረዱት በሚችሉት የተግባቦት መንገድ ሊተላለፍላቸው ይገባዋል። ሐዋርያ ጳውሎስ፣ "ነገር ግን ላያምኑበት እንዴት ሊጠሩት ይችላሉ? ስለርሱ ላይሰሙስ እንዴት ያምናሉ? የምሥራቹን ቃል የሚያበሥርላቸው ሳይኖርስ እንዴት ሊሰሙ ይችላሉ?" ብሏል (ሮሜ 10፥14)። የወንጌል ስብከት በመደበኛ ንግግር ወይም ስብከት ብቻ የተወሰነ አይደለም። ከዚህ ሥፍራ ጳውሎስ የተጠቀመው ቃል ሊተረጐም "መልዕክቱን ማስታወቅ ወይንም ማስተላለፍ" ማለት ነው። ክርስቶስን ለሌሎች ለናካፍል ይህ ሁልጊዜ ይሆናል። ይህ በየትም ቦታ ሊሆን ይችላል። በቤተክርስቲያን ውስጥ ወይም በ-ና እየጠጣን ወይም በሆስፒታል ውስጥ ወይም በሽርሽር ቦታ ወይም በመዝናኛ ሥፍራ ወይም በአይሮፕላን ውስጥ ሊሆን ይችላል።

አንድ ሰው ማወቅ የሚገባውና የሚያስፈልገው የወንጌል መልዕክት ምንድን ነው? በአጭሩ ሊገለጽ፣ አራት ነጥቦችን ይዟል። ነጥቦቹን እንድታስላስሏቸው አበረታታችኋለሁ፣ ከዚያም ለማንም ሰው ለመናገር ትችላላችሁ (አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻዎችን ለያንዳንዱ ነጥብ ጨምሬለሰሁ፣ እንድታስላስሏቸው ግድ አላችኋለሁ።) *አንደኛ፣ እግዚአብሔር ፈጠረን፣ ይወደናል፣ ከርሱ ጋር ለዘላዓለም በሰላም አብረን አንኖር ዘንድ ይፈልጋል* (ዘፍ 2፥7፤ ዮሐ 10፥10)።

ሁለተኛ፣ ኃጢአት ሠርተናል፣ እግዚአብሔርን ትተናል፣ በመሆኑም ክርሱ ተሰይተናል፣ ከፍርዱም በታች ሆነናል። (ሮሜ 3፥23፤ ኢሳ 59፥2)።

ሦስተኛ፣ እግዚአብሔር አሁንም ይወደናል፣ ስለወደደንም አንድያ ልጁን፣ ኢየሱስ ክርስቶስን፣ ወደ ምድር ልኮታል። ተልዕኮው፣ እኛ በኃጢአታችን ምክንያት ልንቀበለው የሚገባንን ቅጣት ክርሱ ተቀብሎ እኛን ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን ነው፣ (ሮሜ 5፥8፤ 6፥23፤ 1ኛጴጥ 3፥18)።

አራተኛ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ አዳኛችን አንደሆነ በአምነት እርሱን በመተማመንና በሕይወታችን ጌታ አንዲሆን በመስጠት ልንመላለስ ይገባናል (ዮሐ 3፥16፤ 1፥12፤ ሮሜ 10፥9)።

ወንጌልን ለሰዎች ለማቅረብ ውጤታማ ከሆኑት መንገዶች አንዱ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለናንተ ያደረገላችሁን መንገር ነው። ይህንን በምታደርጉበት ጊዜ ምናልባት ሊከራከሩአችሁ ወይም አስባችሁበት የማታውቁትን ወይም መልስ የማታገኙለትን ጥያቄ ሊጠይቁአችሁ ይችላሉ፣ ይሁን አንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገላችሁን ነገር መካድ አይችሉም። ስለምትናገሩት የሕይወት ምስክርነት ጊዜ ወስዳችሁ አስቡበት፣ ከዚያም እግዚአብሔር የምትናገሩበትን ዕድል ሊሰጣችሁ በግልጽና አጠር ባለ ሁኔታ ለመንገር እንድትችሉ እንዲረዳችሁ አርሱን ለምኑት። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "ጌታ የሆነውን ክርስቶስን በልባችሁ አክብሩት፣ በእናንተ ስላለው ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዝግጁዎች ሁኑ" (1ኛ ጴጥ 3፥15)።

በተጨማሪ፣ *ክርስቶስን ለማያውቁ በአካባቢያችሁ ላሉ ሁሉ ጸልዩላቸው።* አንድ ሰው ወደ ክርስቶስ እንዲመጣ ደስማቂረጥ ልትፀልዩ አትችሉም፣ ግን ግድየለሽ አትሁኑ። እግዚአብሔር እናንተን ተጠቅሞ ሕይወታቸውን ለመንካት እንደፈለገ ካላወቃችሁ በቀር ለደነታቸው ልትፀልዩም አትችሉም። ፀሎት ሌሎችን ከመለወጡ በፊት በቅድሚያ እናንተን ይለውጣል።

ፀሎት በወንጌል አገልግሎት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ያመጸውን ሰው ልብ መለወጥ የሚችለው እርሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። የምንናገረው ቃል ምንም ያህል ተገቢና አሳማኝ ቢሆን ወይም አቀራረባችን ምንም ያህል የተዋጠለትና የተዋበ ቢሆን፣ መንፈስ ቅዱስ መንገዱን ካላዘጋጀው በስተቀር ቃላችን ምንም ፈይዳ አያመጣም። በመጽሐፍ ቅዱስ "የሰውን አሳብ ማን ሊያውቅ ይችላል? የሰው ልብ ከሁሉ ነገር ይልቅ እጅግ ተንኮለኛ ነው፣ እኔ እግዚአብሔር ግን የሰውን ልብ እመራምራለሁ፣ እያንዳንዱን ሰው በአካሄዱና በሥራው መጠን እቀጠዋለሁ" (ኤር 17፥9-10) ተብሎ ተጽፎአል።

የሰውን ልጅ ልብ ምስጢር በመላት የምናውቀው በመንግሥት ስማይ ነው፣ አንዳንድ ስዎች ስለመሆት የወንጌል ቃል

በጎ ምላሽ ሲሰጡ ሌሎች ለምን እምቢ እንዳሉ የምናውቀው እዚያ ነው። ግን አንድ ነገር ግልጽ ነው፤ ፀሎት በወንጌል አገልግሎት ውስጥ እጅግ ወሳኝ ድርሻ አለው፣ የወንጌል አገልግሎት አካልም ነው። አንዳንድ ጊዜ ለወንጌላዊነት አገልግሎት (ተልዕኮ) ዝግጅት የሚያሰፈልጉ ጠቃሚ ቅድመ ተከተሎችን እንድመዘግብላቸው ለሚጠይቁኝ ምላሼ ሁልጊዜ ተመሳሳይ ነው፤ "ጸሎት . . . ጸሎት አናም ብዙ ፀሎት ነው" አላቸዋለሁ። ሐዋርያ ጳውሎስ በቆላስይስ ለነበሩ ክርስቲያኖች፤ "እግዚአብሔር ለምሥራቹ ቃል በር እንዲከፍትልንና በእርሱ ምክንያት እኔ ታሥራ የምገኝበትን የክርስቶስን ምሰጢር ማብሰር እንድንችል ለኛም ፀልዩ" (ቆላ 4፥3) በማለት በጥብቅ አሰገንዝቦአቸዋል።

በዙሪያችሁ ያሉ ሰዎች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ያሰፈልጋቸዋል። ለቤተሰባችሁ፣ ለጐረቤቶቻችሁ፣ አብረዋችሁ ለሚሠሩ፣ አብረዋችሁ ለሚማሩ ልትፀልዩላቸው ይገባል። ትፀልያላችሁ? እውነትን ይረዱ ዘንድ እግዚአብሔር የልባቸውን በር እንዲከፍትላቸው እግዚአብሔርን ትለምኑታላችሁ? ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንድትነግሩአቸው እግዚአብሔር አናንተን እንዲጠቀማችሁ ትጠይቁታላችሁ? በተጨማሪ፣ እግዚአብሔር ከዓለም ዙሪያ ወደራሱ ለሚጠራቸው ሰዎች ልንፀልይላቸው ይገባናል። እግዚአብሔር ስተወሰኑ ሚሲዮናውያን ወይም ለአንድ አገር ወይም ጐሣ እንድትፀልዩ ሊያደርጋችሁ ይችላል። በዚህ በምድር ሕይወት እያላችሁ የምትፀልዩላቸውን በአካል ላትገናኙ ትችላላችሁ፤ ነገር ግን የናንተ ጸሎት አነርሱን ወደ ዘላለም ድነት ለማምጣት ድርሻ እንደነበረው በመንግሥተ ለማይ ትረዳላችሁ።

ለይጣን የእግዚአብሔርን ሥራ ለማደናቀፍ ከሚጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ መንገድ፤ እኛ ለክርስቶስ ተዕዕኖ እንድናመጣ እግዚአብሔር እኛን ለመጠቀም እንደማይችል በማሳመን ነው። ይህ ግን እውነት አይደለም። ማንም በዙሪያችሁ ወዳሉ ሰዎች ሁሉ በወንጌል ሊደርስላቸው አይችልም። በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 10፥2 ያለው የኢየሱስ ቃል አሁንም እውነት ነው፤ "እንዲህም አላቸው፥ እነሆ መከሩ ብዙ ነው፤ የመከሩ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው። ስለዚህ የመከሩ ጌታ ለመከሩ ሥራ ተጨማሪ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት።" በናንተ እንዲጀምር ወይቁት።

ሃያ ዘጠኝ

ሕይወት በየደረጃው



ስለሰ ሸምግዐና ደረስ ስኔ ነኝ፥ ስለሰሸበተም ደረስ ስሸከማችኋለሁ፣ ስኔ ሠርቻለሁ፣ ስኔም ስነሣለሁ፣ ስኔ ስሸከማለሁ ስኔም ስድናለሁ።

(ኢሳ 46፥4)

አንድን ውድድር እንዴት እንደምትጀምሩ ብቻ ሳይሆን፤ እንዴት እንደምትፈጽሙትም አስፈላጊነቱ እኩል ነው። የክርስትና ሕይወትም እንዲሁ ተመሳሳይ ነው።

አንድ ፕሮጀክት (ውጥን) ጀምራችሁ ላትጨርሱት ትታችሁ ታውቃላችሁ? ብዙዎቻችን አድርገን እናውቃለን። የነበራችሁ ጉጉት ከጊዜ በኋላ ቀዝቅዞ ወይም ለልችቶአችሁ ወይም ውጥኑ ከብዶአችሁ፣ በመጨረሻ ወደ ሌላ ነገር ሄዳችሁ ይሆናል።

የሕይወት ጉዞ ግን እንደዚህ አይደለም፤ ጉዞውን የምናቆምበትና ወደሌላ ሁኔታ የምንሄድበት አማራጭ የለም። የመፈፀም ወይም ያለመፈፀም ብሎ የምርጫ ነገር የለም። ጉዞው እስከኖርን ድረስ ይቀጥላል። ብቸኛው ጥያቄ ግን እንዴት አድርገን እንጨርሳለን ነው።

ቁልቁል መውረድ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙ በጣም አሳዛኝ ታሪኮች አንዱ፣ የእሥራኤል ንጉሥ የነበረው የሳኦል ታሪክ ነው። ሳኦል የተመረጠና ተሰጥኦ ያለው ሰው ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስ "ከርሱ ይልቅ መልካም ሰው እልነበረም" ይላል (1ሳሙ. 9፥2)። የንግሥና ዘውድ ከጫነ በኋላ አንድ መሪ እንዲኖረው የሚፈለገውን ብቃት ሁሉ አሳየ፤ ትህትና፣ ጀግንነት፣ ግርማ ሞገስ፣ መልካም ባሕርይ፣ የማስተዳደር ብቃት መለያዎቹ ነበሩ። የእሥራኤል ከተማ እንደ ተከበበ መልዕክት በመጣ ጊዜ፣ "በሳኦል ላይ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደ (1ሳሙ. 11፥6)፣ ሕዝቡ ሁሉ በዙሪያው ተሰበሰበ"

የሚል እናነባለን። ጠላትን መልሞ አድርጐ አሸነፈ፣ ሳኦል ስላገኘው ድል ከብሩን ለእግዚአብሔር ሰጠ።

ከጊዜ በኋላ ግን ሳኦል ተለወጠ። በእግዚአብሔር ላይ የነበረው መደገፉ ቀርቶ በትዕቢት ተሞላ፣ በራሱም መተማመን ጀመረ። ዳዊት በቅልጥፍና ግዙፉንና ኃይለኛውን ጐልያድን ጠጠር ወንጭፎ በገደለና ወራሪዎቹን ባባረረ ጊዜ - ሳኦል በማመስገን ፈንታ - በዳዊት ላይ በቅናት ጦፈ። በራሱ ሥልጣን የማይተማመንና የሚጨነቅ ሆነ፣ ዳዊትን ለመግደል ባለማቋረጥ ማሳደድ ጀመረ። በመጨረሻም ሳኦል ከእግዚአብሔር ፊቱን በመመለስ ወደ ጠንቋዮችና ሟርተኞች ዞረ፣ ምራት ከነርሱ ፈለገ፣ ፍጻሜውንም ራሱን በማጥፋት አጠናቀቀ። ሳኦል ጅማሬው መልካም ቢሆንም ፍጻሜው ግን በአሳዛኝ ሁኔታ ተደመደመ።

ሳኦልን ወደ ስህተት መንገድ የወሰደው ምንድነው? መጽሐፍ ቅዱስ መልሱን በዝርዝር አላስቀመጠልንም፣ ነገር ግን ሳኦል ከነበረበት ከፍታ ወደ ቁልቁል መውረድ የጀመረው በእንድ ጊዜ አልነበረም። ዓመታት ባለፉ ቁጥር በአዳዲስ ፈተናዎች ውስጥ እያለፈ ከውድቀት ወደ ውድቀት ገባ።

የሕይወት ደረጃዎች

እንደ ወንጌላዊነቴ አብዛኛውን የሕይወት ዘመኔን ያሳለፍኩት በጉዞ ነው፣ ከማስታውሰው በላይ በጣም ብዙና ረጃጅም ጉዞዎችን አድርጌአለሁ። ምንም እንኳ ሁለት ጉዞዎቼ ሌሎቹን የማይመስሉ ቢሆንም፣ እያንዳንዱ ጉዞዬ ግን አስከ ግቡ ድረስ ከአንዱ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ የተሸጋገረ ነበር።

የሕይወት ጉዞ ጉዳያም እንዲሁ ነው። እያንዳንዳችን በጉዞ ላይ ነን። በማያጠራጥር መልኩ ወደ ፍጻሜው እስክንደርስ ድረስ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ እየተሸጋገርን ነው። የሕፃንነት ጊዜ ወደ ልጅነት ጊዜ ያድጋል፣ ልጅነት ወደጉርምስና ወይም ኮረዳነት ያድጋል፣ ጉርምስና ወደ አካለመጠን ዕድሜ ያድጋል፣ ከአካለ መጠን ወደ ጉልማሳነት፣ ከጉልማሳነት ወደ ብስለት ዕድሜ ከዚያም ወደ ሽምግልና ይደረሳል።

ታዲያ ይህ የሕይወት ዕድገት ደረጃ እግዚአብሔር ከሰጠን ክርስቲያናዊ የሕይወት ጉዞ ጋር ምን ጉዳይ አለው? በቀላሉ እንዲህ ነው፣ እያንዳንዱ የሕይወት ደረጃ የራሱ ፮ሆነ ፈተናና አደጋ አለው፣ ሰይጣን ደግሞ በአጋጣሚዎቹና (በፈተናዎቹ) ለመጠቀም

ሁሉ ጥረት ያደርጋል። በምናረጅበት ጊዜ፣ ወጣት በነበርንበት ጊዜ በገጠመን ዓይነት ፈተና እንጋፈጥም ይሆናል - ነገር ግን በሸመገልንም ጊዜ ፈተናው ይቀጥላል። ምናልባት የሚያጋጥሙት ፈተናዎች ከዚህ በፊት ከደረሱብን የተለዩ ሊሆኑ ስለሚችሉ፣ አዲሶቹ ሥፍራችንን ሊያስለቅቁን ይችላሉ። በዚህ ምዕራፍ ቀጣይ ከፍል የመጨረሻዎቹን እንዳንድ የሕይወት ደረጃዎች መፈተሽ እፈልጋለሁ። በመንፈሳዊ ረገድ ለኛ ምን ማለት እንደሆኑ እገልጻለሁ። ባሁኑ ለዓት እንዳቸውም አላጋጠመህም ይሆናል - ነገር ግን አንድ ቀን ሊያጋጥም ይችላል፣ የመዘጋጃው ጊዜ ፈተናው ሳይደርስ አሁን ነው።

ባደሙን ጉጆ መጋፈጥ

ልጆቻችን አያደጉ ሳሉ ወደ ቤታችን ሊጐበኙን የመጡ እንግዶች ሁሉ ጉብኝታቸውን ጨርሰው ሲመለሱ በቤታችን ውስጥ ካዩት መተራመስ የተነሳ፣ ራሶቻቸውን እያወዛወዙና እያጉረመረሙ ነው የሄዱት ብዬ አስባለሁ። በአምስት እረፍት የለሽ ቅብጥብጥ ልጆች ላይ የተለያዩ ውሾችና ድመቶች ተጨምረው ቤታችንን የሞቀና ያልደበዘዘ ለማድረግ ከበቂ በላይ ነበሩ። እኔ ለአገልግሎት መጓዝ ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ፣ ሩት በየቀኑ በአሰልቺና በአድካሚ የልጆች ትግል አሳልፋለች፣ ሆኖም ሕይወት ቤቱን ከሞሉ ልጆቻችን ጋር ሁልጊዜ በተተረማመሰ ደስታ የሚቀጥል ይመስለን ነበር።

ከጊዜ በኋላ ልጆቻችን ጥለውን ሄዱ። እኛ ይህን ከማስተዋላችን በፊት ሰዎች ልጆቻችን እንዳደጉ ይነግሩን ነበር - ትክክል ነበሩ። ሩት በጻፈችው ደብዳቤዋ "አሁን ባዶ ወደሆነው ቤት መመለስ እስጠልቶኛል" ብላለች። እኛ የምንጋፈጠው ችግር በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ወላጆች በየዓመቱ የሚደርስባቸውን ነው - ባዶ ጐጆ። እግዚአብሔር በጊዜው በርኅራኄው ሕይወታችንን በአዲስ ደስታ ሞላው (የልጅ ልጆቻችንንና የልጅ ልጅ ልጆቻችንን ጨምሮ)። ሆኖም ባዶ ጉጆን እንደገና መልሶ ማስተካከሉ አሁንም ለኔና ለባለቤቴ ከባድ ፈተና ነው።

ለዚህኛው የእድሜ ደረጃ ሰዎች በተለያየ መንገድ ምላሽ ይሰጣሉ። አንዳንዶች ሰላሙንና ነጻነቱን በመናፈቅ እንደ ዕረፍት ይመለከቱታል። አንዳንዶች (በተለይ በብቸኝነት ያሉ ወላጆች) በተቀላቀለ ስሜት ይቀበሉታል፣ ስላሰፋቡት አስቸጋሪ ጊዜ ቢያመሰግኑም፣ ቀሪውን የብቸኝነት ዘመናቸውን የሚፈሩ ይሆናሉ።

ሌሎች ደግሞ ያለጠባቂና ተንከባካቢ የቀሩ፣ የማይጠቅሙ እንደሆኑ ይሰማቸዋል ወይም ለልቹ ይሆናሉ ወይም ድብርት ውስጥ ይገባሉ። እነዚህ ሁሉ ምላሾች በመንፈሳዊ ረገድ እኛን እደጋ ውስጥ ሊከቱን የሚችሉ ናቸው።

ለመሆኑ በዚህ የለውጥ ወቅት ምን ዓይነት አደጋዎች ናቸው ሊያሠጉን የሚችሉት? አንደኛው የጋብቻ አለመስማማት ነው። አንዲት ሴት በጻፈችልኝ ደብዳቤ "ለልጆቻችን ስንል አብረን ቆየን፣ አሁን ልጆቹ ሄደዋልና ከዚህ በኋላ አብረን ለመሆን የምንችልበት ምንም ምክንያት አይታየኝም" ብላለች። አንድ አባወራ ደግሞ "ልጆቻችን ከሄዱ ጀምሮ አንድ የሚያደርገን የጋራ የሆነ ነገር የለንም" በማለት ጽፎልኛል።

ችግሩን የሚያባብሰው ተጨማሪ ነገር ደግሞ የጉልማሳነት ዕድሜ፣ ልክ እንደማይፈለግ ባዶ ጉጅ ተደርጉ የሚታሰብ መሆኑ ነው። ሁሉም ለው በዚህ "በዕድሜ ጠና የማለት ጠንቅ" ተብሎ በሚጠራው ችግር ውስጥ ያልፋል ማለት አይደለም፣ ነገር ግን የሚደርሱኝ ደብዳቤዎች በዚህ ችግር ውስጥ አያሌ ሰዎች መኖራቸውን ያረጋግጡልኛል። አንዲት ልቧ በዚህ ዓይነት ችግር የተሰበረ ሴት "ባሌ ጠባዩ ተለውጦብኛል፣ አሁን ልጁ ልትሆን ወደምትችል ወጣት ሴት ዘንድ ገብቷል፣ ከኔ ጋር ሊፋታ ይፈልጋል" በማለት ጽፋልኛለች። ሌላዋ ሴት ደግሞ "ባሌ በሥራው በጣም የተወጠረ ነው። ለኔ ምንም ትኩረት አይሰጥም። እኔ አሁን ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት ጀምሬአለሁ። ምናልባት ይህንን እንደ ስህተት ልትቆጥር ትችላለህ፣ ነገር ግን እኔ ለመደሰት መብት የለኝም?" በማለት ጽፋልኛለች። እንደነዚህ ዓይነት ደብዳቤዎች ያሳስበኛል፣ ምክንያቱም እንዲህ ዓይነት *መንገዶች* ደስታን ሊያመጡ በፍፁም የማይችሉና ደህንነት የሌላቸው መሆኑን አውቃለሁ።

የኋለኛው ደብዳቤ የሚጠቁመው ብዙውን ጊዜ በዚህ የሕይወት ደረጃ ወቅት ከበስተጀርባ እያደባ የሚመጣ ሌላ አደጋ መኖሩን ነው፤ *በሌሎች ነገሮች መጠመድ ነው*። ጊዜ እያለፈ መሆኑን እንረዳለን፣ እናም የሚያስከፍለን ዋጋ ምንም ይሁን ምን የተሻለ ነው ያልነውን ነገር ለማድረግ እንወስናለን። አንዳንዶች (በሥራ እንደተዋጠው ባል) በሥራቸው የተዋጡ ይሆናሉ፣ ሌሎች ደግሞ እንደ ትንግርት ባሉ ወይም በሚያዝናኑ ፕሮግራሞች

(ልምምዶች) ራሳቸውን ያጠምዳሉ። አሁንም ሌሎች ደግሞ ሰለ ገንዘብ ዋስትና ወይም በህብረተሰቡ ውስጥ ስለሚኖራቸው ሥፍራ ይጨነቃሉ፣ ወይም ደግሞ ዕድሜን ወደ ኋላ ለመመለስ ሲሉ ቅጥ ባጣ ሁኔታ ይመገባሉ ወይም ለመዋብ ብለው ቀዶ ጥገና ያደርጋሉ። ሕይወት ሚዛኑን የጠበቀ አይሆንም። በዚህ ሂደት እግዚአብሔርን ወደ ጠርዝ ይገፉታል ይልቁንም በሕይወታችን ማዕከላዊ ሥፍራ ላይ ባለመርጋታችን፣ ክርስቶስን ቀስ በቀስ በጥላ ውስጥ እናስቀምጠዋለን። ይህ በእናንተ ላይ እንዲሆንባችሁ አትፍቀዱ።

ከትውልድ ወደትውልድ

ከባዶ ጉጅ ጋር በጥብቅ የተያያዘ እያንዳንዱ ወላጅ የሚገጥመው ሌላው ጉዳይ *ከአዋቂ ልጆቻችን* ጋር ያለን ግንኙነት ነው።

ለዚህ ጥያቄ ቀለል ያለ መልስ የለም፤ ልጆቻችን ባላቸው ፍላጐትና በማንነታቸው (ሰብዕና) የተለያዩ ናቸው (ልክ እንደ እኛ)። ወላጆች እነዚህን አዋቂ ልጆቻቸውን በተመለከተ ብዙ ጥበብና ፀሎት ያስፈልጋቸዋል። ልጆችም እንደዚሁ ከወላጆቻቸው ጋር በተዛመደ መልኩ ከወላጆቻቸው የሚማሩት ብዙ ነገር አለ።

ማንኛውም ሁኔታ ልዩ ሆኖ ሳለ፣ ካደጉ ልጆቻችን ጋር ባለን ግንኙነት መጽሐፍ ቅዱስ ከሁለቱ ጽንፎች እንድንጠነቀቅ ይነግረናል። እንደኛ፣ ልጆቻችን አዋቂ ከሆኑ በኋላ ለመቆጣጠር የምናደርገውን *መከራ* ማስወገድ እንዳለብን ይነግረናል። አንዲት በቅርቡ ያገባች፣ "ወላጆቼ በኑሮአችን ውስጥ ባለማቋረጥ ጣልቃ እየገቡብን ነው፣ ጣልቃ እንዳይገቡብን ምን ልናደርግ እንችላለን?" በማለት ጽፋልኛለች።

ልጆች ራሳቸውን ሲችሉ (ጥገኝነትን ሊያቆሙ) ትልቅ የለውጥ ሽግግር ይሆናል። ከዚያ በኋላ በእኛ ሥልጣን ሥር አይደሉም። በተለይ ይህ ጉዳይ አንዱ ካገቡ እውነትነቱ ግልጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፣ በሚስቱም ይጣበቃል" (ዘፍ 2÷24) ከዚያ በኋላ የተለየ ቤተሰብ ይሆናሉ፣ እንደ ወላጆች እነሱን ለመቆጣጠርና በኑሮአቸው ውስጥ ያለብልሃት ጣልቃ ለመግባት መሞከራችንን ማስወገድ አለብን። ሳያገቡ የተቀመጡ ወይም በፍቺ ምክንያት በጉዳት ውስጥ ያለፉ ልጆች ሁኔታ ተመሳሳይ ነው። ይህ ማለት ግን ካገቡ በኋላ

እንረዳቸውም ወይም እንመክራቸውም ማለት አይደለም - በጭራሽ። ነገር ግን እደረራጋችን በጥበብ ይሁን።

ሌላው ጽንፍ ያደጉ ልጆቻችንን ችላ ማለታችን ነው። እንደ ለው እንዲህ ብሎኛል፣ "ልጆቻችን ብዙ መከራ እላይተውናል፣ ከዚህ በኋላ እስከመቼውም ባላያቸው ማድየለኝም።" ይህ ሰው የተናገራቸው ቃላት በጣም ሸካራ ነበሩ፣ በብዙ መታገሥ ተነጋግረን ስለ ልጆቹ እንዳልሆነ አረጋግጬአለሁ - ነገር ግን እንዳንድ ወላጆች ይህን ያደርጋሉ። ሌሎች ደግሞ ዝም ብለው ከልጆቻቸው ይርቃሉ ወይም ይለያሉ። እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ፣ የቤተሰብን ቁርኝት ማላላት ብቻ ሳይሆን፣ በመንፈሳዊ ረገድ ልናበረታታቸውና ልንረዳቸው የምንችልበትን ዕድል እናጣለን።

ይህ ሁኔታ በተለይ እውነትነቱ እየተገለጠ የሚመጣው ልጆቻችን የራሳቸው ልጆች በሚኖራቸው ጊዜ ነው። አሥራ ዘጠኝ የልጅ ልጆቻችን (አሁን ደግሞ የልጅ ልጅ ልጻችን) ለኛ ለዓመታት ደስታን ሰጥተውናል፣ ይህን ላሰብ ልቤ ግንኙነታቸው በቦታ ርቀት ወይንም ደግሞ በፍቺ ምክንያት የተቋረጠባቸውን እያት ወላጆች ያሰባል። የልጅ ልጆች ዝም ብሎ ልዩ መብት (ችሮታ) እይደሉም - ኃላፊነትን የሚጠይቁ ናቸው። የልጅ ልጆቻችሁ ስለ እናንተ ምን ያስተውላሉ? አብራችሁ ያላለፋችሁትን የደስታና የፈንጠዝያ ጊዜ ብቻ ነው የሚያስታውሱት? ወይንስ ለከርስቶስ ያላችሁን ፍቅርና ደስታችሁን ያስታውሳሉ?

እግዚአብሔር የልጅ ልጆች ቢሰጣችሁ ሳታቋርጡ ፀልዩላቸው። እንዲሁም ለክርስቶስ መኖር ይችሉ ዘንድ የምትችሉትን ሁሉ በማድረግ እበረታቱአቸው። ግንኙነታችሁንም እታቋርጡ፣ ለወላጆቻቸው ስትደውሉ እነሱንም እነጋግሩአቸው። በበዓላት ቀናት ብቻ ሳይሆን በሌላ ጊዜም ካርድና ደብዳቤ ላኩላቸው (ወደ ኃላዬ መለስ ብዬ ላለበው፣ ምነው እንደዚያ ለማድረግ ታማኝ በነበርኩ ብዬ እላለሁ።) ከሁሉም በላይ ምሳሌ ሁኑአቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለመጋቢዎች የጻፈው መልዕክት እያት ወላጆችንም የሚመለከት ነው። "በነገር ሁሉ መልካምን በማድረግህ ምሳሌ የሚሆን ራስህን አሳይ" (ቲቶ 2፥7)።

በወላጆቻችን ዕድሜ ስንሆን

ዕድሜ እየገፋ ሲመጣ፣ ሌላ ነገር ደግሞ ይገጥመናል፣ እሱም በሽምግልና ያሉ የወላጆቻችን ጉዳይ ነው። በአንድ ወቅት እነሱ ለኛ ጥንቃቄ ያደርጉልን ይንከባከቡንም ነበር። አሁን ደግሞ እኛ በተራችን እነሱን ልንከባከባቸው የሚገባ ይሆናል። ከዐሥርቱ ትዕዛዛት አንዱ እንዲህ ይላል፣ "አባትህንና እናትህን አክብር" (ዘፀ 20፥12) - ይህም እስከ ዕድሜ ልክ ነው። ይህንን ትዕዛዝ ከምናከብርበት አንዱ መንገድ በእርጅናቸው ወቅት እንክብካቤና እርዳታ በማድረግ ነው። ነገሩ ቀላል ላይሆን ይችላል። ጥበብንና ትልቅ እዘኔታን የሚጠይቅ እስቸጋሪ ውሳኔ ያለበት ነው። ወንድሜና እህቶቼ እሮጊት እናታችንን ከነበረችበት እሮጌ ቤት ወደ አፓርታማ "ይመቻታል" ብለው ሲያዛውሯት እስታውሳለሁ። ከእኛ ጋር መሆንዋ ሁኔታዋን የተሻለ ያደርግለታል ብለን ነበር፣ ነገር ግን ወዲያውኑ የበለጠ ደስተኛ መሆን የምትችለው በራሷ እሮጌ ቤት ውስጥ መሆኑን ስለተረዳን ከምስጋና ጋር ወደ ቤቷ መልሰናት ልትረዳት የምትችል ሞግዚት እደረግንላት።

እግዚአብሔር በእርጅና ውስጥ ላሉ ወላጆቻችሁ ኃላፊነት ከለጣችሁ፣ ለእነሱ ምርጥ የሆነው ምን እንደሆነ እሹ እንጂ ለእናንተ የበለጠ ምቹ የሆነውን እይደለም። ግንኙነታችሁን እታቋርጡ! ብዙውን ጊዜ ደረጃ ለምችን የመኖሪያ ማዕከል በምጐበኝበት ወቅት ተንከባካቢዎቻቸው እንዳንድ በልጆቻቸው የተረሱትን ወላጆች ለላምታ እንዳቀርብላቸው ይጠይቁኛል። "እንዲያው እንደምን ናችሁ ቢሉአቸው እንኳን በቂ ነበር፣ ቤተሰቦቻቸው በፍጹም እይጐበኙአቸውም" ይሉኛል። ይህ ያላዝናል! ወርቃማውን ትዕዛዝ (መመሪያ) ተግባራዊ ማድረግና መታዘዝ ካለብን ያረጁ ወላጆቻችንን መንከባከብን ይጨምራል።

ጡረታ - አዲስ ጅማሬ

እግዚአብሔር እንድንሠራ ይፈልጋል (በቤታችንም ሆነ በሥራ ቦታ ማለት ነው)፣ ነገር ግን ጡረታ መውጣት ማለት ስህተት ነው ማለት እይደለም። ሌዋውያን (እሥራኤልን በአምልኮ የመሩ) በእምሣ ዓመታቸው ጡረታ እንዲወጡ ታዘዋል (ዘኁ 8÷24-26)፣ መሴም ባረጀ ጊዜ በገላጣ መሬት ላይ ቆሞ "እኔ ዛሬ መቶ ሃያ ዓመት ሆኖኛል፣ ከዚህ በኋላ እወጣና እገባ ዘንድ አልችልም" በማለት አሳውቋል (ዘዳ 3፥12)።

ብዙዎቻችን በተወለነ ደረጃ ላይ ጡረታ እንወጣለን፣ ነገር ግን ጡረታ ለብዙዎች ያልተጠበቀ አሠቃቂ ገጠመኝ ይሆንባቸዋል። አንድ ለው፣ "ጡረታ የምወጣበትን ቀን ለዓመታት በጉጉት ስጠባበቅ ኖሬአለሁ፣ አሁን ጡረታ መውጣቴ እርግጠኛ ሲሆን ግን የሚለማኝ ለሜት ምንም እንደማልጠቅም ዋጋ እንደሌለው ለው ነው" በማለት ጽፎልኛል። ሌላ ሰው ደግሞ አዕምሮዬን እየላትኩና ስልቹ እየሆንኩ ነው ብሏል። ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ጡረታ ከወጡ ከጥቂት ዓመታት በኋላ እንደሚሞቱ አንድ ሐኪም ገልጸልኛል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት ከጡረታ በኋላ የሚኖራቸው ሕይወት የማይጠቅም እንደሆነ ስለሚያምኑ ነው በማለት ሐኪሙ አስረድቶኛ ል።

ብዙ ሰዎች ስመጥሪያቸው ገንዘብ እንደሚያጠራቅሙ አውቃለሁ፣ ነገር ግን በመንፈላቸውና በስሜታቸው እይዘጋጁበትም። ሥራን የምንሠራው ለኑሮአችን የሚሆን ገንዘብን ለማግኘት ብቻ እይደለም፣ ሥራ የዓላማን ትርጉምና ጥቅም ያሳየናል፣ እንዲሁም ባልንጀራን የምናፈራበት ዕድል ነው። በጡረታ ይህ ሁሉ ይሰወጣል፣ ብዙ ሰዎች ደግሞ ሰዚህ አልተዘጋጁበትም። ጡረታ ሲወጡ ምን እንደሚያደርጉ፣ በፍፁም እስበውበት አያውቁም ወይም እንዴት አድርገው አዲስ መንገድ መፈለግና ማግኘት እንደሚኖርባቸው አያስቡም።

ግን አድምጡኝ፣ ጡረታ ብትወጡም እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ያለውን ሥራ አልጨረሰም! ክርስቶስን ስናውቅ ክርሱ አገልግሎት በፍፁም ጡረታ እንወጣም። ጡረታ ላይ ከሆናችሁ ወይም ከጥቂት ዓመታት በኋላ ጡረታ የምትወጡ ከሆነ፣ እርሱን የምታገለግሉበትን አዲስ መንገድ እንዲያሳያችሁ እግዚአብሔርን በፀሎት ጠይቁት። ምናልባት በአካባቢያችሁ በቤተሰብ ሀብረት ወይም በቤተክርስቲያን ኃላፊነት በትርፍ ጊዜ ሥራ ወይም በፈቃደኝነት የምትሠሩት ሥራ ሊሆን ይችላል። ጡረታን ምንም ዓይነት ሥራ የማይሠራበት ዕድል እድርጋችሁ እትመልከቱ። ይልቁንም፣ ከእግዚአብሔር የተሰጣችሁ የሥራ ለውጥ እንደሆነ እስቡት። እዲሱን ነፃነታችሁን በጉዞ በመዝናናት ወይም የምትፈልጉትን ብቻ በማድረግ ደስታ የምታገኙበት እድርጋችሁ እትቁጠሩት። ነገር ግን ሌሎችን በክርስቶስ ስም እንድትረዱ ከእግዚአብሔር የተሰጣችሁ ትኩስ (አዲስ) ዕድል እንደሆነ እድርጋችሁ እዩት።

አየሽመገልን ስንመጣ

በቅርቡ አንድ ወዳጄ "ሽማግሌ መሆን ያስጠላኛል፣ ግን ሽማግሌ ላስመሆን ምንም አማራጭ የለኝም፣ አማራጭ ይኖረኛል?" በማለት ገልጸልኛል። እኔም እስማማለሁ። እስከ ሰማንያዎቹ ዕድሜ መጨረሻ እኖራለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም። ከዚህ በፊት አደርገው የነበረውን ነገር እሁን መልሼ ሰማድረግ አይሆንልኝም ሰማለትም አልችልም ወይም ደግሞ በነጋ በጠባ ቁጥር አዲስ ህመም ወይም ሥቃይ ወይም የከፋ ነገር ያገኘኛል አልልም። ሩትና እኔ መለያየትን የማንወደው ቢሆንም ከወቅታዊ ሁኔታችን እየተለማን ያለው እውነታ ግን አቅመቢስ እንደምንሆን ወይም እንደምንሞት ነው።

ይሁን እንጂ የእርጅና ዕድሜ ዋጋ ያለው ነው። ከምንጊዜም በላይ፣ እያንዳንዱ ቀን የእግዚአብሔር ሰጦታ ሆኖ አግኝቻለሁ። እንዲሁ ያለ ዓላማ የተሰጠ ሰጦታ እድርጌ አልቆጥርም። ይህ ጊዜ እግዚአብሔር በዘመናችን ያደረገውን ምህረት መልሰን በማንጸባረቅ ለማሳየትና እግዚአብሔር ለለጠው ተስፋ በትክክል የታመነ መሆኑን ለሌሎች ለማረጋገጥ የተሰጠን ዕድል ነው። ከሁሉም በላይ፣ የእርጅና ጊዜ ተስፋችን በሆነው በመንግሥተ ሰማይ የምንደሰትበት ጊዜ ነው።

በተጨማሪም፣ እንደተረዳሁት፣ የእርጅና ጊዜ በእነሰተኛ (በጥቃቅን) መዝናኛዎች የመደሰቻ ጊዜ ነው። ጥቃቅኖቹ ነገሮች እሰቀድመን የናቅናቸው ሊሆኑ ይችላሉ። አሁን እኔ ጤንነቴን የሚከታተል ሐኪሜ በሰጠኝ መመሪያ ሚዛኔን ጠብቄ መራመድ እንዲያስችለኝ ምርኩዝ እጠቀማለሁ። በምራመድበት ጊዜ ያስማቂረጥ በአግሮቼ አካባቢ ያለውን መሬት እመለከታለሁ። በመሬት ላይ በድንገት የማያቸው ጥቃቂን ነገሮች ሁሉ ከዚህ በፊት ትኩረት በመስጠት ልብ ብዬ ያልተመለከትኳቸው ይሆናሉ። በጣም ትንንሽ ነፍሳት፣ በተለያየ ቀለም የተሰበጡ አብረቅራቂ ድንጋዮችና ጥቃቅን ዕጽዋት ሁሉ የእግዚአብሔርን የረቀቀ ውበታዊ ፈጠራን እንዳስተውል አድርጐኛል። መጽሐፍ ቅዱስ ለነፎችን "እንተ ታካች ወደ ገብረጉንዳን ሂድ፣ መንገድዋንም ተመልከተህ ጠቢህ ሁን" ይላል (ምሳሌ 6፥6)። የማስታወስ ችሎታችን በእግዚአብሔር ከተሰጡን ታላላቅ ስጦታዎች እንዱ ነው። በሽምግልና ዘመናችን ከዚህ በፊት ያሳለፍናቸውን ሁኔታዎች መለስ ብለን በአዕምሮአችንና በስሜቶቻችን መረዳት እንድንችል የተሰጠን ታላቅ ስጦታ ነው።

የእርጅና ዕድሜ፣ ለይጣን ከሕይወት ጉዞ ለመነጠል የመጨረሻ ዕድሉን የሚጠቀምበት ጊዜ ነው። እንደሚሞክርም እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ። ስለ ጤንነታችን ሁኔታ፣ ስለ ገንዘብ ችግር፣ ስለ ብቸኝነት፣ ወይም ስለ ሌሎች ስለተለያዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮቻችን አንጨነቅም ማለት አንችልም። ራሳችንን መቻል ውልቅ ብሎ ሲወጣ ወይም እቅመቢስነታችን ሲባባስ ተስፋ መቁረጣችን የግድ ነው። ሌላው ቀርቶ እግዚአብሔር ራሱ ትቶናል ብለን እንገረማለን።

ነገር ግን እግዚአብሔር አልተወንም። የኢየሱስ የተሰፋ ቃል ልክ በሌሎች የዕድሜ ደረጃዎች እውነት እንደነበረ ሁሉ በእርጅና ዘመናችንም እውነት ነው፣ "እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴ 28÷20) ብሎናል። መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ በእግዚብሔር ዓይን፣ "ረኽቦም ዕድሜ የቅኖች ሽልማት ነው፣ ሽበትም የክብር ዘውድ ነው" (ምሳሌ 16÷31) ይላል። ባሁኑ ጊዜ እግዚአብሔር ከምንጊዜም በበለጠ ከእኔ ጋር እንደሆነ እንደሚለማኝ በታማኝነት ልነግራችሁ እወዳለሁ። ይህ ለእናንተም እውነት ሊሆን ይችላል። ከዚህ በፊት መሥራት የምትችሉትን ነገር አሁን መሥራት አትችሉም - ነገር ግን አንድ ነገር መሥራት ትችላላችሁ። እግዚአብሔር አሁንም ሌሎችን ለመባረክ እናንተን ይጠቀማል። ይልቁንም፣ ብስጩ ወይም ቁጡ ከመሆን፣ በእርጅና ዘመናችሁ ክርስቶስን በሕይወታችሁ ማንፀባረቅ እንድትችሉ እንዲረዳችሁ ለምኑት።

የፀሎት ጊዜ መድቡ። አንድ ክርስቲያን ጓደኛዬ ከመሞቱ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ድምፁን እያወጣ መፀለይ እንዳቃተው ሲረዳ፣ በውስጡ በመቃተት መጸለዩን ቀጠለ፣ ይህም ሲያቅተው ከንፈሮቹን በማንቀሳቀስ ቀጠለ፣ ከንፈሮቹ ሲደክመውበት በፀጥታ ሆኖ በአዕምሮ መፀለዩን አላቆመም ነበር። ሌላው ጓደኛዬ ደግሞ የብዙ የወንጌል መልዕክተኞች ስም ዝርዝር ነበረው ለብዙ ዓመታትም ለነዚህ መልዕክተኞች ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ስማቸውን እየጠራ ይፀልይላቸው ነበር። በጣም አርጅቶ ሳለም ከነዚህ የወንጌል መልዕክተኞች አገልግሎት ጉን እንደሆነ ያውቅ ነበር።

በጉዞ አቅጣጫው መዝሰቅ

ራሳችንን ለእግዚአብሔር ሰጥተን ከሆነ፣ የዕድሜአችን የመጨረሻ ዓመታት በጣም ስኬታማ የምንሆንባቸው ሲሆኑ ይችላሉ። ግን እንዴት ነው በአቅጣጫው መቀጠል የምንችለው?

የመጀመሪያው ደረጃ፣ ሊገጥመን ለሚችል አደጋ ንቁ መሆን ነው። ምናልባት "አስቀድሞ የተጠነቀቀ አስቀድሞ የታጠቀ ነው" የሚል ብሂል ሰምታችሁ ይሆናል። እናም እውነት ነው። መንፈሳዊ አደጋን መቋቋም የሚገባው ከመሆኑ (ከመድረሱ) በፊት ነው። ንጉስ ዳዊት በመካከለኛ የዕድሜ ዘመኑ ካጋጠመው ፈተና ራሱን ቢጠብቅ ኖሮ ሕይወቱ ምንኛ አስደላችና ልዩ በሆነ ነበር። ይልቁንም፣ ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ፣ በአመንዝራነት፣ በነፍስ ገዳይነት ምክንያት ሕይወቱ ቁልቁል ወረደበት፤ የልብ ስብራትም ደረሰበት (2ሳሙ. 11-12)። ነገር ግን የሠራውን ኃጢአት ተናዘ ንስሃ ሲገባ እግዚአብሔር ምሕረት እደረገለት፤ ይሁን እንጂ ጥፋት ስለተፈፀመ ተሰሚነቱ ወይም ምላሌነቱ እንደ ቀድሞው አልሆነለትም። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፣ የሕይወት መውጫ ከርሱ ነውና" ይላል (ምሳሌ 4÷23)።

ሁለተኛ፣ ለክርስቶስ የገባችሁትን ቃል አጠንክሩ። የእርጅና ዘመን ማዕበል ከሕይወት ጉዞ አቅጣጫ ሲያስወጣችሁ እስኪያስፈራራችሁ ድረስ አትጠብቁት። እምነታችሁን የምታጠነክሩበት ጊዜው አሁን ነው። ከክርስቶስ ጋር ያለን ግንኙነት ከጠነከረ፣ የለይጣንን ፈተና መከላከያችንም ጠንካራ ይሆናል። ለይጣን ሁልጊዜ፣ አሁንም ቢሆን፣ ሊማርከን ይሞክራል፤ ነገር ግን ክርስቶስ እንድንቋቋመው ይረዳናል። "ያለ ነውር የሚሄድ ተማምኖ እንደሚሄድ" መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል (ምሳሌ 10÷9)።

በተጨማሪ፣ ማንኛውንም ሁኔታ ለእግዚአብሔር አሳልፎ መስጠትን ተማሩ፣ ስለውጤቱም በርሱ እመኑ። በምንም ዓይነት ችግር ውስጥ ብትሆኑ ወይም ኑሮአችሁ የተረጋጋ ባይሆን እግዚአብሔር ለናንተ ያለው ፍቅር አይሰወጥም። በርሱ ዘንድ ድንገተኛ (የማይታወቅ) ነገር የለም፣ እርሱ መልካሙን ሁሉ እንደሚያደርግ ሊታመን ይገባዋል። ይልቁንም፣ ፍራቻና ጭንቀት ሸባ እንዳያደርጉአችሁ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር አሳልፋችሁ መስጠትን ተማሩ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "ጌታ

እግዚአብሔር የዘላለም አምላ ነውና ስለላለም በእግዚአብሔር ታመኑ" (ኢሳ 26÷4)።

በመጨረሻም፣ እግዚአብሔር በናንተና በሌሎች መካከል የመሠረተውን ግንኙነት አጠንክሩ። ከትዳር አጋሮቻችሁ፣ ከልጆቻችሁ፣ ከጓደኞቻችሁና ከአማኞች ጋር ግንኙነታችሁን አጠንክሩ። ከሰው ስንገለል ወይም ማንም አያስፈልገንም ብለን የምናስብ ከሆነ በሚያጋጥመን ፈተና የምንጐዳና የምናመቻምች እንሆናለን። ስይጣን በኢየሱስ ላይ የክረረ የጥቃት መከራ ያደረገው ብቻውን በሆነ ጊዜ ነበር (በምድረ በዳና በጌቴሴማኒ የአትክልት ሥፍራ)። እንደ እግዚብሔር ህላብ የሆነ ግንኙነት ስሌሎች ኃላፊነት እንዲሰማንና ሕይወታችን በደስታ እንዲሞላ ያደርጋል። አውነተኛ ደስተኛ የሆነ ክርስቲያንን ሰይጣን ሲያሸንፍ አላየሁም።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሰሞት በተቃረበ ጊዜ፣ ምንም ነገር አልነበረውም። በእምነቱ ምክንያት በሮም እስር ቤት ውስጥ ተጥሎ ሳለ በስውነቱ ላይ የሚደርበው ካባ እንኳን አልነበረውም። መጪውን ክረምት የሚቋቋምበት ምንም ልብስ አልነበረውም። ወዳጆቹ ሁሉ ትተውት ወይንም ደግሞ ወደ ሌላ ሥፍራ ሔደው ነበር። ሉቃስ ብቻ አብሮት ነበር። በዓሰም መስኪያ (ሚዛን) ሕይወቱ በውድቀት የተደመደመ ነበር።

በእግዚአብሔር መስኪያ ሲመዘን ግን በውድቀት አልተደመደመም። ክርስቶስ ጳውሎስን ደቀመዝሙር እንዲሆን ጠራው። ጳውሎስም ሰጥሪው ታማኝ ነበረ። ክርስቲያን ከሆነ በኋላ በመከራና በፈተና ያሰፈበትን ወደ ኋላ መለስ ብሎ ከተመለከተ በኋላ በአርግጠኛነት፣ "መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፣ ሩጫዬን ጨርሻለሁ፣ ኃይማኖቴን ጠብቄአለሁ" (2ኛ ጢሞ 4÷7) ለማለት በቅቷል።

ጳውሎስ ፍፃሜውን አላመረ። እናንተስ?

ሰላሳ

ያሸበረቀ ተስፋችን

ለንባን ሁሉ ለለያናቸው ላይ ደመርጋል። ሞተ ወይም ሀዘን ወይም ሰቅሶ ወይም ሥቃይ ከለንግዲህ ወዲህ ለይኖርም፤ ምክንያቱም የቀድሞዎቹ ነገሮች ሥርዓተ ለሰጩለሰ።

(ራዕይ 21÷4)

ሕይወት እስቸጋሪ ናት፣ እግዚአብሔር ግን መልካም ነው፣ መንግሥተ ሰማይም አውን ነው።

ማንም ሰው ቢሆን ስለመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ጥርጣሬ አይኖረውም። እውነት ነው ሕይወት እስቸጋሪ ናት። ይህን ምዕራፍ ስጽፍ አዕምሮዬ አብዛኛውን ጊዜ በአሜሪካ ደቡባዊ ክፍል የተነሳው ዐውሎ ንፋስ ባስከተለው የሞት አደጋና ጥፋት ተይዞ ነበር። ከጥቂት ወራት በፊት ልክ ደቡባዊ አስያን እንዳወደመው አንደ "ስናሚ" ነውጥ፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከቤታቸው ተፈናቅለዋል፣ የት አንደሚደርስ እንኳን ሳይወጥኑ በለበሷት ልብስ ብቻ ተሰደዋል። አንድ በሺህዎች ጊዜ ሊባዛ የሚችል የአንድ ቤተሰብ ታሪክ እሰ። ይህ ቤተሰብ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን በረግረጋማና ፍርስራሽ በሞላበት ወንዝ እየወደቀና እየተነሳ ከብዙ ጉዳትና ጉስቁልና በኋላ መጥቶ በአቅራቢያችን ያለች ቤተክርስቲያን የተቀበሰችው ቤተሰብ ነበር። ታሪኩ እሳዛኝ ነበር። የኋላ ኋላ አደጋው የደረሰበት አካባቢ ተመልሶ የሚገነባ፣ "ካትሪና" የተባለው ዐውሎ ንፋስም ከትዝታችን የሚደበዝዝ ቢሆንም፣ ሕይወት ስለአደጋው ስሰባዎች ግን አሁንም እስቸጋሪ ናት፣ በጣም አስቸጋሪ ናት።

ምናልባት አብዛኛዎቻችን እንደዚህ ዓይነት ከባድ አደጋ በፍጹም ደርሶብን አያውቅም - ነገር ግን እኛም ሕይወት እስቸጋሪ መሆኗን እናውቃለን። አንዳንድ ጊዜ ሻከራነቷ ላናስበው በድንገትና ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ ይመጣብናል፣ አንዳንድ ጊዜም የደረሰብን ችግር በአብዛኛው የሕይወት ዘመናችን እብሮን ይቆያል። በዚህ መጽሐፍ አንዳንድ የልብ ስብራትና የትግል ሁኔታዎች

ተመልክተናል። ነገር ግን የትኛውም መጽሐፍ እነዚህን ችግሮች ሊቋቋም አይችልም። ሕይወት ደስታና ሳቅም ያጋጥማታል። ነገር ግን የሕይወት ጉዳና አብዛኛውን ጊዜ በጣም ኮረኮንች እንደሆነ ደግሞ እናውቃለን። ፈተናዎች በኃይል ያጠቁናል፣ ለዎች ተስፋ ያስቆርጡናል፣ በሽታና እርጅና ያዳክሙናል፣ ሀዘንና ትካዜ ያደፍጡብናል፣ ክፋትና ፍትሕ አልባነት ያጠቁናል።

ሕይወት አስቸጋሪና ከባድ ናት፣ እግዚአብሔር ግን መልካም ነው፣ መንግሥተ ሰማይም እውን ነው።

የመጨረሻው ግባችን

ከመጽሐፍ ቅዱስ ታላላቅ እውነታዎች አንዱ *እኛ የተፈጠርነው በዚህ ዓለም ብቻ ተወስነን ልንቀር አለመሆኑ* ነው። ሞት የሕይወታችን መደምደሚያ አይደለም፣ ነገር ግን ሞት ወደ ዘላዓለማዊነት ብቸኛው መግቢያ መንገድ ነው። የተፈጠርነው ለዘላለም እንድንኖር ነው፣ ሞት ደግሞ ከዚህ ምድር ሕይወት ወደሚቀጥለው ሕይወት ብቸኛ የሽግግር መንገድ ነው። ጥያቄው ሞት በኋላ ሕይወት ይኖራል ወይስ አይኖርም አይደለም። ብቸኛው ጥያቄ ዘለዓለማዊነቱን የምናሳልፈው የት ነው? የሚል ነው - መጽሐፍ ቅዱስ መንግስተ ሰማይ (ገነት) ብሎ በሚጠራው ስፍራ ከእግዚአብሔር ጋር ማለቂያ በሌለው ደስታ ወይም ከእግዚአብሔር ተለይተን በዘላለም ሥቃይና ማለቂያ በሌለው ተስፋ መቁረጥ መጽሐፍ ቅዱስ ሲኦል (ገሃነም) ብሎ በሚጠራው ሥፍራ)፣ ከሁለቱ ባንዱ መሆናችን አይቀሬ ነው።

ሞት መደምደሚያ እንደሆነ ተደርጉ እንደሚታሰበው የማይሆነው ለምንድነው? ኢዮብ፣ "ሥጋ ለባሽ ሁሉ ዕድሜው እጭር ነው፣ ያም ቢሆን በመከራ የተሞላ ነው። እንደ አበባ ታይቶ ወዲያው ይረግፋል። እንደ ጥላም ብዙ ላይቆይ ያልፋል . . . ለው ግን ሞቶ እንዳልነበረ ሆኖ ይቀራል፣ ታዲያ ነፍሱ ከሥጋው ከተለየች በኋላ የት ይገኛል?" (ኢዮ 14፥1-2፣ 10) በማለት በሀዘን አንጐራጉሯል። ሆኖም ኢዮብ ጠቅላላ የለው ታሪክ ይህ እንዳልሆነ ያውቃል። አንድ ቀን የዚህ ምድር የሕይወት ምዕራፍ ይፈፀማል፣ ለክርስቲያኖች ግን ሞት የሚያመለክተው ጅማሬን ነው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም አብሮ ለመኖር የኢዲስ ሕይወት ጅማሬ ነው። ሐዋርያ ጳውሎስ፣ የለው ዓይን ያላያችው፣ ጆሮም ያልሰማው በለውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው" ካለ በኋላ "... ለኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በክል

ገለጠው" ብሏል (1ቆሮ 2፥9-10)። ተስፋ እስቆራጭ በሆነና ሥቃይ በበዛበት ሕይወት መሃል ብናልፍም፣ መንግሥተ ሰማይ ያሸበረቀ ታላቅ ተስፋችን ነው።

እንዴት እናውቃለን?

ይሁን እንጂ ለብዙዎች የመንግሥተ ሰማይ ወይም የዘላለም ሕይወት ጉዳይ ህሳባዊ ምኞት ይመስላቸዋል። አንድ ለው፣ "እኔ መንግሥተ ሰማይን የምመለከተው ልክ እንደ አፈታሪክ ነው" ብሎኛ ል። "ለዘላለም እናራለሁ ብሎ ማሰቡ ጥሩ ቢሆንም አንዴ ክሞትን ግን ሁሉም ነገር ያከትማል" በማለት አክሎልኛል።

ይህ ለው ትክክል ነውን? መንግሥተ ሰማይ እውን መሆኑን እንዴት እናውቃለን?

አንደኛው የማወቂያ ምክንያት፣ በውስጣችን ባለው ናፍቆት ነው። ምንም ያህል ባልተለያየ ሁኔታ ሉሎች ሃይማኖቶችም ከሕይወት በኋላ አንድ ነገር እንዳለ ያምናሉ፣ እንዲሁም ሁላችንም በውስጣችን ክዚህ ምድራዊ ሕይወት ባሻገር አንድ ነገር እንደሚኖር ይለማናል። ይህ የምድሩ ሕይወት ያልተሟላ (ደላለቀ) ነው። የተሟላ እንዲሆን ደግሞ እንናፍቃለን። ይህ ዓለም አቀፋዊ ናፍቆት የመጣው ክየት ነው? እግዚአብሔር በውስጣችን እንደተከለው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፣ "እግዚአብሔርም ከጥንት ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ድረስ የሠራውን ሥራ ለው መርምሮ እንዳያገኝ ዘላለምነትን በልቡ ለጠው" (መክ 3፥11)። የተሠራነው ለእግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ክርሱ ጋር ለዘላለም አብሮ ለመኖር እንናፍቃለን። ይህን ናፍቆት ልንጨቁን ወይም እውነት አይደለም ብለን ራሳችንን ልናሳምን እንችላለን፣ ነገር ግን አሁንም አንድ ቀን ፍትሕ አልባነትና ክፋት ይሻራሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

መንግሥተ ሰማይ እውን እንደሆነ የምናውቅበት ሌላው ምክንያት እግዚአብሔር የገባው ቃል ኪዳን በመኖሩ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ካንዱ ጫፍ እስክ ሌላኛው ጫፍ፣ እግዚአብሔር የሠራን ከእርሱ ጋር ለዘላለም እንድንኖር መሆኑን ያረጋግጥልናል። መዝሙረኛው፣ "ምሕረትህና ቸርነትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፣ አምላኬ ሆይ በቤትህ ለዘላለም እኖራለሁ" (መዝ 23፥6) ብሏል። ኢዮብም፣ "እኔን ግን የሚቤገርኝ ሕያው እንደሆነ፣ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም፣ ይህ ቁርበቴም ክጠፋ

በኋላ፣ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ" (ኢዮ 19፥25-26) በማለት አረጋግጧል። ኢየሱስም፣ "ትንሳኤና ሕይወት እኔ ነኝ፣ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል" በማለት ቃል ገብቷል (ዮሐ 11፥25)። ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ፣ "ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን (ሥጋችን) ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንፃ እንዳለን እናውቃለንና" በማለት አስተምሮአል (2ቆሮ 5፥1)።

መንግሥተ ሰማይ እውን መሆኑን የምናውቅበት ሦስተኛው ምክንያት፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተነሣ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን የመንግሥተ ሰማይን ክብር ትቶ በኃጢአት ወደተወረረ ዓለም መጣ? አ[illegible]ያት የኛን የዘላለም ድነት ለመፈፀም ነው። እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ሲፈጥራቸው የነበረው ዕቅድ፣ ከርሱ ጋር እንከን አልባ በሆነ መሰማማት ለዘላለም እንዲኖሩ ነበር። ነገር ግን ሰይጣን ይህን እቅድ ለመለወጥ ቆርጦ ተነሣ፣ በውሸትና በማባበል ማረካቸው፣ ከእግዚአብሔርም ለያቸው። እንዲህ ሲሆን፣ ሞት በለው ዘር ሳይ መጣ፣ ሁሳችንም የሞት ሰለባዎች ሆንን። ሞት የሰይጣን ትልቁ ድል መሆኑን ከቶ አትርሱ።

ነገር ግን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ በሞቱና በትንሣኤው፣ ይህን ታሪክ ሽሮአል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ ክርስቶስ የመጣው "በሕይወታቸውም ሁሉ ሰለሞት ፍርሃት በባርነት ይታሠሩ የነበሩትን ሁሉ ነፃ እንዲያወጣ ነው" (ዕብ 2፥15)። እስቲ አስቡት፣ የሰይጣን ትልቁ ድል ተቀሰበሰ፣ ሽንፈትን ተከናነበ፣ ሞት በሞት ተቀጣ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ፣ "ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ ድል መንሣትህ የት አለ? . . . ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሳትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይሁን" ቢል አያስገርምም (1ቆሮ 15፥55፣57)።

የክርስቶስ ወደ ምደር ለመምጣቱ አንቀሳቃሽ ምክንያት ሰኛ ያለው ጽኑ ፍቅር ነበር፣ ዓላማና ግቡ ደግሞ ሞትን አጥፍቶ፣ እኛ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ለዘላለም እንድንሆን ሊወሰደን ነው። የኢየሱስ ትንሣኤ ያለምንም ጥርጥር የሚያረጋግጥልን ሞት መደምደሚያ ሳይሆን ከወደፊታችን መንግሥተ ሰማይ መኖሩን ነው። ኢየሱስ፣ "በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፣ እንዲህስ ባይሆን

ባልኋችሁ ነበር፤ ሥፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና" በማለት ቃል ገብቶልናል (ዮሐ 14፥2)። ይህ እርግጠኛ ተስፋችን ነው።

መንግሥተ ሰማይ ምን ይመስላል?

መንግሥተ ሰማይ እውን ከሆነ፣ ምን ይመሰላል? የዚህን ጥያቄ መልስ ሰማይ የማይፈልግ ክርስቲያን እስካሁን ከቶ አሳጋጠመኝም። ይህ እኔንም ይጨምራል። የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት እንኳን ተገርመው ነበር፣ ኢየሱስ ስለመንግሥተ ሰማይ ካስተማራቸው በኋላ፣ "ጌታ ሆይ ወዴት እንደምትሄድ አናውቅም" በማለት ቶማስ ተከራክሯል (ዮሐ 14፥5)።

መንግሥተ ሰማይ ምን እንደሚመስል ላስን ጥያቄዎች ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ መልስ አያሰጠንም፣ ምክንያቱም መንግሥተ ሰማይ እኛ ከምናስበው ከማንኛውም ነገር በላይ እጅግ የከበረና ያሸበረቀ በመሆኑ ነው። *መንግሥተ ሰማይ* ልንረዳ ከምንችለው በላይ እጅግ ፍጹምና ውብ ቦታ ነው። *መንግሥተ ሰማይ* ምን እንደሚመስል ማወቅ የምንችለው በመንግሥተ ሰማይ ሰንሆን ብቻ ነው። የዮሐንስ ራዕይ ፀሐፊ በጨረፍታ ያየውን (ውልብ ያሳለትን) የመንግሥተ ሰማይ ውበትን የሚገልጽ ቃላት ሲፈልግ፣ "የእግዚአብሔር ክብር ያሰባትን ቅድስቲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰትወርድ አሳየኝ፣ ብርሃንዋም እጅግ እንደከበረ ድንጋይ እንደ ኢያሰጲድ ድንጋይ ሆኖ እንደ ብርሌ የጠራ ነበረ . . . አሥራ ሁለቱም ደጆች አሥራ ሁለት ዕንቁች ነበሩ፤ እያንዳንዱ ደጅ ከአንድ ዕንቁ የተሠራ ነበረ። የከተማይቱም አደባባይ ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረ" ብሏል (ራዕ 21፥11፣21)። ሐዋርያ ጳውሎስም፣ "ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከዕውቀት ከፍዬ አውቃለሁ፤ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ አውቃለሁ" በማለት ጽፏል (1ቆሮ 13፥12)።

ይሁን እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንግሥተ ሰማይ ምንም ሳያሳውቀን በጨለማ ውሰጥ አይተወንም - በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ማንኛውም ነገር እዚያ ሰመሄድ እንድንፈልግ የሚያደርገን መሆን አለበት። ከዚህ አኳያ መጽሐፍ ቅዱስ ስለመንግሥተ ሰማይና በዚያ እኛ ምን እንደምንሆን የሚያስተምረውን አራት እውነታዎችን እንመለከታለን።

ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር እንሆናለን

እንደኛ፣ በመንግሥተ ሰማይ ከእግዚአብሔር ጋር እንደምንሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። መንግሥተ ሰማይ ብዙ ነገር ነው - ከሁሉም በላይ ዋናው ነገር የእግዚአብሔር መኖሪያ ሥፍራ መሆኑ ነው። እግዚአብሔር የሚኖርበት ሥፍራ ነው! እግዚአብሔር በሁሉም ሥፍራ የሚገኝ መሆኑ እውነት ነው፤ ነገር ግን መንግሥተ ሰማይ ከሁሉም በታ የበለጠ ነው። ፍፁም ልዩ የሆነ ሥፍረታዊ መኖሪያ ሲሆን እግዚአብሔር በመሃሉ፣ ክርስቶስ በቀኙ በኩል ሆኖ አለ። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ለዘላለም ከጌታ ጋር እንሆናለን" ይላል (1ተሰ 4፥17)።

ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም አብረን እንሆናለን! የሚለውን እስቲ እስቡት። ከርሱ ጋር ለለምንሆን ከክፉ ሁሉ ፍጹም የተጠበቅን እንሆናለን። ትካዜና ሥቃይ በፍፁም እያገኙንም - በፍፁም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ ምንባቦች ውስጥ በጣም ለሚት የሚነካ ክፍል በዮሐንስ ራዕይ ከመጨረሻው ምዕራፍ በፊት የሚገኝ ነው፣ "ታላቅም ድምጽ ከሰማይ፣ እነሆ፣ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው፤ ከእነርሱም ጋር ይድራል፣ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ፣ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤ እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ደብሳል፣ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፣ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፣ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ" (ራዕ 21፥3-4)።

በመጨረሻም ወደ ቤታችን እንገባለን

ይህ ስለ መንግሥተ ሰማይ ወደ ሁለተኛው ታላቅ እውነት ይመራናል፣ በቤታችን እንሆናለን። "ቤት" የሚለው ቃል ትርጉሙ ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ነገር ነው። አንድ ወጣት፣ በልጅነት ዘመኑ የደረሰበትን ሁከትና ጉስቁልና እያስታወሰ "በጭራሽ ወደ ቤቴ አልመለስም" ብሎኛል። አያይዞም፣ "ነገር ግን ሰልጆቼ የተለየ እንዲሆንላቸው እፈልጋለሁ፤ እውነተኛ ቤት እንዲኖራቸው እፈልጋለሁ" ብሎኛል። ምንም እንኳን ዕድሉን ባያገኝም፣ ቤት የሰላምና የደስታ ቦታ መሆኑን ያውቅ ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ ይህ ዓለም የእኛ የመጨረሻ ቤታችን እንዳልሆነ ይናገራል። ነገር ግን አንድ መኖሪያ አለን፣ እርሱም

መንግሥተ ሰማይ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ "በምድር ላይ እንግዶችና መጻተኞች" እንደሆንን ተጽፏል (ዕብ 11፥13)። እንዲሁም "አገራችን በሰማይ ነው" ተብሰናል (ፊልጵ 3፥20)። የልባችን ጩኸት ልክ ሐዋርያ ጳውሎስ እንደተናገረው ነው፣ "ከዚህ እንደ መኖሪያችን ከሆነው ሥጋችን ተለይተን ከጌታ ጋር መሆን እንመኛለን" (2ቆሮ 5፥8)።

በአካባቢዬ የሚታተም አንድ ጋዜጣ "በዜና ዕረፍት" ዐምዱ ላይ ከጊዜ ወደ ጊዜ "ሟች እገሌ/ እገሌት ወደ ሰማያዊ ቤቱ/ቷ ሄደ/ች" እያለ ይጽፋል። ይህን ዐምድ ሳይ ሁል ጊዜ "ሟች ክርስቲያን መሆን አለበት/አለባት" እላለሁ።

ቤት የደስታና የሰላም ቦታ ነው - መንግሥተ ሰማይም እንዲሁ ነው። ቤት የዕረፍትና የሚያስደስት ቦታ ነው - መንግሥተ ሰማይም እንዲሁ ነው። ቤት የፍቅርና የደህንነት ቦታ ነው - መንግሥተ ሰማይም እንዲሁ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ "ወደ ሰላም ይገባል፤ በቅንነት የሄደ በአልጋው ላይ ያርፋል" ይላል (ኢሳ 57፥2)። በክርስቶስ ሆነን ስንሞት፣ ከርሱ ጋር በመንግሥተ ሰማይ ለዘለዓለም እንኖራለን።

እንዳንድ ሰዎች፣ "ደህና፣ መንግሥተ ሰማይ ለመሄድ የምፈልግ ለመሆኔ እርግጠኛ እይደለሁም። በጣም አሰልቺ ይመስለኛል" ይሉኛል። ነገር ግን በመንግሥተ ሰማይ መሰልቸት የሚባል ነገር የለም፣ የእግዚአብሔርን የከብሩን ባለጠግነት ለማወቅ ዘላለምነትን እናገኛለን። መጽሐፍ ቅዱስም፣ እግዚአብሔር የምንሠራውን ሥራ እንደሚሰጠን፣ እርሱን እንደምናገለግለው፣ ከርሱም ጋር እንደምንነግሥና ያለ ድካም እንደምናመልከው ይናገራል (ራዕ 22፥3፣5)።

ለዘለዓለም እንሰወጣለን

በተጨማሪ፣ በመንግሥተ ሰማይ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደምንሆን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንመስል እግዚአብሔር ያቀደው ዕቅድ እንድ ቀን ይጠናቀቃል፣ "የኃለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበት ዓይን እንለወጣለን" (1ቆሮ 15፥51-52)።

ይህ ማለት ምን ማለት ነው? አንደኛ፣ አዲስ አካል አንለብሳለን፤ አዲሱ አካል የኢየሱስ የትንሣኤ እካል ዓይነት ነው። በመንግሥተ ሰማይ ምን እንደምንመስል እውቃለሁ? ሰማወቅ እልችልም - ነገር ግን እዲሱ እካላችን ከበሽታና ከመበስበስ ፍጹም የነፃ እንደሆነ አውቃለሁ። አዲሱ እካላችን በምድር ላይ እናውቃቸው በነበሩ ዘንድ የሚታወቅ እንደሆነ አውቃለሁ የእሁኑ አካላችን በኃጢአት የተበከለ ነው፣ እንዲሁም "... ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውሰጣችን እንቃትታለን" (ሮሜ 8፥23)። ነገር ግን መጠባበቃችን አንድ ቀን ያበቃል። ክርስቶስን እንመስላለን ስንል ጠቅላላ ባሕርያችንም ይለወጣል ማለት ነው። እንድ ቀን እንደ ክርስቶስ እንሆናለን! እሁን ባልተሟላ ሁኔታ እንወዳለን - በዚያን ጊዜ ግን በተሟላ ሁኔታ ይሆናል። አሁን ደስታችንና ሰላማችን በትካዜና በግርግር ይሰናከላል - በዚያን ጊዜ ግን እንዲህ አይሆንም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ "ወዳጆች ሆይ፣ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ፣ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና፣ እርሱን እንድንመስል እናውቃለን" (1ዮሐ 3፥2)። ምንኛ የከበረ ተስፋ ነው!

ሁሉም ነገር አዲስ ይሆናል

በመጨረሻም፣ በመንግሥተ ሰማይ የአዲስ ፍጥረት አካል እንሆናለን። ኃጢአት የበከለው አካላችንን (እኛን) ብቻ ሳይሆን፣ ሁሉንም ፍጥረት ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ሙሉ በሙሉ ስትመሠረት እኛ እንደምንለወጥ ሁሉ ፍጥረት ሁሉ ይለወጣል፣ የአዳም ዐመፅ ያስከተለውን ውጤት ሁሉ ይቀለብሰዋልና። በዚያን ቀን "ፍጥረት ራሱ ከጥፋት ባርነት ነፃ ወጥቶ ከእግዚአብሔር ልጆች ጋር የነጻነትና የክብር ተካፋይ እንደሚሆን ነው" (ሮሜ 8፥21)። ምናልባት ይህ ነቢዩ ኢሳያስ እንዳመለከተው፣ ተኩላ ከበግ ጠቦት ጋር ይቀመጣል፣ ነብርም ከፍየል ጠቦት ጋር ይተኛል፣ ጥጃና የእንበሳ ግልገል በአንድነት ያርፋሉ፣ ትንሽ ህፃንም እየመራ ይጠብቃቸዋል (ኢሳ 11፥6) ይሆናል።

ይህ መቼ ይፈፀማል? መጽሐፍ ቅዱስ፣ ይህ የሚሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጥረት ሁሉ ላይ ሥልጣኑን ሲያሰፍን ዳግመኛ ሲመጣ እንደሆነ ይናገራል። "የጌታ ቀን እንደ ሌባ ይመጣል፣ በዚያ ቀን ሰማያት በታላቅ ድምጽ ያልፋሉ፣ ፍጥረት ሁሉ ይቃጠላል፣

... ነገር ግን እኛ ዕድቅ የሚኖርበትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በተስፋ ቃሉ መሠረት እንጠባበቃለን" (1ጴጥ 3፥10፣13)።

ጆን ኤፍ ኬኔዲ፣ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ሆኖ ከተመረጠ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ የጎልፍ (ሩር እየመቱ ጉድጓድ ውስጥ መክተት) ጨዋታ ፍሎሪዳ ውስጥ እብሬው እንጫወት ጠየቀኝ። ግብዣውን ተቀብዬ በመኪና ስንጓዝ መኪናውን አቆመና ኢየሱስ እንድ ቀን ወደ ምድር ተመልሶ የመምጣቱ ነገር እውነት መሆኑን ጠየቀኝ። ከጥያቄውም በላይ መኪናውን አቁሞ መጠየቁ አስገርሞኝ ነበር። እውነት መሆኑን እረጋግጥኩለት፣ እንዲሁም ቤተክርስቲያናት ሁሉ (የርሱም ጭምር) በእምነታቸው ያረጋገጡት ይህንኑ እውነት እንደሆነ አስገነዘብኩት። ከሦስት ዓመታት በኋላ በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ፣ ጳጳሱ ያነበቡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፥16 የሚገኝ ስለክርስቶስ ዳግመኛ መምጣት ነበር፤ "ጌታ ራሱ በትዕዛዝ፣ በመላዕክትም እስቃ ድምፅ፣ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፣ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ።"

እንዳንድ ጊዜ የክርስቶስን የመመለስ ተስፋ ሳናስተውለው እንቀራለን፣ ዳሩ ግን ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች በማይመችና አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲሆኑ ወደዚህ ታላቅ እውነት ሲመለሱ ይስተዋላል። ልጅ ሳለሁ፣ አስቃቂው የ1ኛ ዓለም ጦርነትና የሚያስጨንቀውና ተስፋ የሚያስቆርጠው ያ ክፉ ቀን ብዙ ክርስቲያኖችን (እናቴንም ጨምሮ) ወደ መጽሐፍ ቅዱሳችን ዞር አንዲሉ አድርጉ ነበር። ይህም ስትንቢቱ ቃል ትኩረት እንዲሰጡና የክርስቶስን መመለስ ተስፋ እንዲያስበብት አነሳስቷቸዋል። በስደትና በመከራ ወቅት ሁልጊዜ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ዳግመኛ የመመለስ ተስፋ ተፅናንተዋል፣ ክፉውንም አሸንፈዋል። የወንጌል እገልግሎት በሰጠኋቸው ጉባኤዎች ሁሉ የክርስቶስን የመመለስ ተስፋ ጨምሬ ሳልናገር ያገለገልኩበት ጊዜ የለም።

የክርስቶስ ዳግሞ ምፅዓት የመጨረሻው ተስፋችን እዚህ ዓለም እንዳልሆነና ምፅዓቱ የዓለምን ችግር ሰማቃለል እንዳልሆነ ያስተውሰናል፣ ነገር ግን የክርስቶስ የተስፋ ቃል ፍጹማዊ አገዛዙን በምድር ላይ ሰማስፈን እንደሆነ ያረጋግጥልናል። ኢየሱስ የምድር አገልግሎቱን ፈጽሞ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ፣ መላዕክት ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ የሚል ተስፋ ሰጡ፣ "ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ

ይመጣል አሉአቸው" (የሐዋ ሥራ 1፥11)። ኢየሱስም፣ "ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፣ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና" (ማቴ 24፥44) በማለት አስጠንቅቋል።

የክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ከሌላው ተገቢ ከሆነው እውነታ ተለይቶ ሲታይ የሚችል አይደለም፣ ያም የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚኖር የተናገረው ቃል ነው። ኢየሱስ እንዲህ አለ "የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላዕክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል። አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፣ አረኛም በጕቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል" (ማቴ 25፥31-32)። የእግዚአብሔርን የድነት ነፃ ስጦታ የታቃወሙ ወደ "ዘላለም ቅጣት ይሄዳሉ" (ማቴ 25፥46) በማለት አስጠንቅቋል። ጳውሎስ በአቴንስ ለነበሩ አረማውያን ፊላስፎች፣ እግዚአብሔር "ቀን ቀጥሮአልና፣ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው፤ ስለዚህም እርሱን ከሙታን በማስነሣቱ ሁሉን አረጋግጦአል" በማለት አሳውቆአቸዋል (የሐዋ ሥራ. 17፥31) የእግዚአብሔር ፍርድ በተገለጸላቸው ጊዜ የሰጡት ምላሽ አሁን ባለንበትም ዘመን ብዙዎች ከሚሰጡት ምላሽ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ "የሙታንንም ትንሣኤ በሰሙ ጊዜ አኩሌቶች አፌዙበት፣ አኩሌቶቹ ግን ስለዚህ ነገር ሁለተኛ እንሰማሃለን አሉት" (የሐዋ ሥራ 17፥32)።

ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፍርድ ብንንቅ በአደጋ ውስጥ መሆናችንን ያመለክታል። አንድ ቀን ግን እግዚአብሔር በዚህ ምድር ላይ ስለተፈፀመው ግፍና ክፋት ተጠያቂ በሆኑት ላይ ይፈርድባቸዋል። እግዚአብሔርን የናቁና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ያዘጋጀውን ድነት ያንቋሸሹ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርድ በእነሱ ላይ ይሆናል። ልክ የእግዚአብሔር የመጨረሻው ፍርድ እውን እንደሆነ፣ የቅጣት ቦታውም መጽሐፍ ቅዱስ ገሃነም (ሲኦል) ብሎ የሚጠራው እውን ነው። በኢየሱስ ያመኑ ሁሉ የዘላለም መኖሪያቸው መንግሥተ ሰማይ (ገነት) እንደሆነ ሁሉ፣ በክርስቶስ በኩል የሚገኘውን የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ የናቁ ሁሉ የመጨረሻ መድረሻቸው ሲኦል ነው። ይህ ከበድ ያለና ተገቢ የሆነ እውነት ነው። የእንድ ሌሚናሪዬም ፕሮፌሰር አንድ ጊዜ ለተማሪዎቹ፣ "ስለ ሲኦል ስትሰብኩ ካለ አንባ ባትሰብኩ ይሻላችኋል" ብሏቸዋል። አልፎ አልፎ አንዳንድ ሰዎች በሚጽፉልኝ ደብዳቤ

ሲኦልን በጉጉት እንደሚጠባበቁ ይነግሩኛል፣ ምክንያታቸው፣ "ሁሉም ጓደኞቻቸውና ዘመዶቻቸው እዚያ ስለሚገኙና ስለሚሆኑ ነው" ይላሉ። ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ሥዕል ፍፁም የተለየ ነው። ሲኦል ፍጹም የብቸኝነትና የተስፋ መቁረጥ ሥፍራ እንደሆነ ይነግረናል፣ "የጨለማ፣ የልቅሶና ጥርስ የማፋጨት ሥፍራ" እንደሆነ ይገልጽልናል (ማቴ 25፥30)። ከሁሉም በላይ፣ ሲኦል ከእግዚአብሔር መለየት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሲኦል ከተዓፋ ቃላት ወደ ሲያል እንድንሄድ የሚያበረታታ አንድም ቃል የለም።

የምሥራቹ ቃል ወደ ሲኦል መሄድ እንደሌለብን የሚያሳስብ ነው! ክርስቶስ የማምለጫ መንገድ ሰጥቶናል - እናም ምክንያቱ እንዳየነው እርሱ በእኛ ፈንታ የሲኦልን (የገሃነምን) ሥቃይና ብቸኝነት ስለተቋቋመ ነው። የእግዚአብሔር ተስፋ እውነት ነው፤ "እንግዲህ፣ በክርስቶስ፣ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም" (ሮሜ 8፥1)። በዘለዓለማዊ ዕጣ ፈንታችሁ አትቆምሩበት። ነገር ግን ራሳችሁን ለክርስቶስ መስጠታችሁን ዛሬውኑ አረጋግጡ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምፅዐት ጊዜ ስለሚፈጸሙ እንዳንድ ዝርዝር ሁኔታዎች እይስማሙም - ዳሩ ግን፣ አንድ ነገር እርግጠኛ ነው፤ በዘመኑ ፍጻሜ፣ ክርስቶስ መንግሥቱን ሊመሠርት ዳግመኛ ይመጣል። አንድ ቀን እግዚአብሔር የገባው ተስፋ ቃል በርግጥ ይፈፀማል፤ "እነሆ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ!" (ራዕ 21፥5)። ኢየሱስ ተመልሶ እንደሚመጣ በተደጋጋሚ ቃል ገብቷል። የሚመጣው የማይታወቅ ሆኖ አይደለም፣ የቤተልሔሙ ተራ ሰው ሆኖም አይደለም፣ በጨለማም አይደለም፤ የሚመጣው በክብርና በኃይል በዓለም ሁሉ ላይ በግልጽ ነው። ይህን መጽሐፍ ቅዱስ፣ "የተባረከው ተስፋችን - እርሱም የታላቁ አምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ" ብሎ ቢጠራ አያስገርምም (ቲቶ 2፥13)። እናቴ ባረጀች ጊዜ፣ ሁልጊዜ ጠዋት ከእንቅልፏ ስትነቃ፣ "ይህ ቀን ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣበት ቀን ቢሆን ያስደንቀኛል?" ብላ ራስዋን ሳትጠይቅ ከቶ ከመኝታዋ እትነሳም ነበር። የሁላችንም የዘውትር ቋሚ ፀሎት በራዕይ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ያለው መሆን አለበት፤ "አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና" (ራዕ 22፥20)።

እስከዚያ ድረስ

መንግሥተ ሰማይ እውን ነው - ነገር ግን ይኼ በእሁኑ ሰዓት በክርስቲያኖች ላይ ምን ልዩነት ያመጣል? ክርስቲያኖች ስለ መንግሥተ ሰማይ ብቻ የሚያልሙ (የሚያስቡ) እንጂ በምድር ላይ የሚያስፈልገው መልካምነት የማያገናቸው ናቸው የሚባለው የጥንት ዘመን ቀልድ እውነት ነው? በርግጥ አይደለም - እውነቱ በተቃራኒው ነው።

እንደኛ፣ መንግሥተ ሰማይ እውን ሰዘሆነ፣ ተስፋ ያሰን ነን፣ ለወደፊቱ ተስፋ አለን፤ እሁን ላለንበት ኑሮአችንም ተስፋ አለን። በእሁኑ የምድር ኑሮአችን ምንም ይሁን ምን ቢገጥመን፣ ስዘለዓለም አብሮን እንደማይቀጥል እናውቃለን፣ ከፊት ለፊታችን የመንግሥተ ሰማይ ሰላምና ደስታ አለ። በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ፣ "ሕይወት አስቸጋሪ ናት፣ እግዚአብሔር ግን መልካም ነው፤ መንግሥተ ሰማያም እውን ነው" ብዬአለሁ። ይሀን ያልኩት አንድ ባልንጀራዬ የሆነ ሐኪም ወደርሱ ለሚመጡ ክርስቲያን ተካሚዎች የሚነግራቸውን ጠቅሼ ነው። ምክንያቱም በወቅታዊ ችግሮቻችን እንዴት በቀላሉ ልንጠመድ እንደምንችልና የእግዚአብሔርን የመንግሥተ ሰማይ ተስፋ እንደምንረሳ ስሚያውቅ ነው። ሐዋርያ ጳውሎስ፣ "በክርስቶስ ተስፋ የምናደርገው ስዚህ ዓለም ሕይወት ብቻ ከሆነ፣ ከለዎች ሁሉ ይበልጥ የሚታዘንልን መሆናችን ነዋ!" ብሏል (1ቆሮ 15÷19)። ነገር ግን የኛ ተስፋ በዚህ ምድር ሕይወት ብቻ አያበቃም! በሕይወት ማዕበል መሃል ብንሆን፣ እግዚአብሔር መንግሥተ ሰማይ ሊያወርስን የገባልን ተስፋችን "እንደ ነፍስ መልሕቅ ነው፣ እርሱም እርግጥና ጽኑ ነው" (ዕብ 6÷19)።

በተጨማሪ፣ መንግሥተ ሰማይ እውን ሰሰሆነ፣ የእሁኑ የምድር ኑሮአችን ትርጉምና ዓላማ አለው። የመጋልየ መጋልይ ጸሐፊ፣ ወደ እግዚአብሔር ከመመለሱ በፊት፣ "ሁሉም ነገር ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ ነው" በማለት ደምድሞ ነበር (መጋ 1÷2)። ብዙዎች ዛሬም በተመሣሣይ መልኩ እንደዚሁ ዓይነት መደምደሚያ ላይ ይደርሳሉ። ነገር ግን ክርስቶስን ስናውቅ፣ ሕይወት ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ እንዳልሆነች እናውቃለን፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በዚህ ምድር ሲያስቀምጠን (ሲያኖረን) የራሱ ምክንያት አለው። እያንዳንዱ የሚጨመርልን ቀን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፣ እንድንወደውና እንድናገለግለው የተሰጠን ተጨማሪ ዕድል ነው።

ይህን ሕይወት መንግሥተ ሰማይ አያቀለውም፤ ግን የበለጠ አስፈላጊ ያደርገዋል።

ይህ መንግሥተ ሰማይ ወደሚያመጣው የመጨረሻ ልዩነት ይመራናል፣ መንግሥተ ሰማይ እውን ሰሰሆነ እያንዳንዱን ጊዜ ለሊየሱስ ክርስቶስ መኖር አለብን። የምድር ኑሮአችን በጣም እጭር ነው፣ ማናችንም ብንሆን ሰምን ያህል ጊዜ እንደምንኖር አናውቅም። እያንዳንዱን ቀን በምድር ላይ እንደ የመጨረሻው ቀናችን እንደሆነ በማሰብ እንኑር - አንድ ቀን የመጨረሻ መሆኑ አይቀርም። ሐዋርያ ጴጥሮስ፣ "እንግዲህ ሁሉ ነገር በዚህ ሁኔታ የሚጠፋ ከሆነ፣ ታዲያ እናንተ በቅድስናና በመንፈሳዊ ኑሮ መኖር እንዴት አይገባችሁም? እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት የምትጠባበቁና በቶሎም እንዲመጣ የምትሠሩ ሁኑ። በዚያ ቀን ሰማይ በእሳት ተቃጥሎ ይጠፋል፣ ፍጥረትም በእሳት ግለት ይቀልጣል" (2ጴጥ 3÷11-12)። ለክርስቶስ መኖር ከፊለጋችሁ፣ ጊዜው አሁን ነው።

ግባችሁ መንግሥተ ሰማይ ነው? ወደዚያ ለመሄድ በናፍቆት እየተጠባበቃችሁ ነው? እኔ እየናፈቅሁ ነኝ፣ ለእናንተም እፀልያለሁ። እግዚአብሔር ለኛ ያዘጋጀው የወደፊት ሕይወት ምንኛ እስደናቂና የከበረ ነው!

የዚህ ዓለም ሽክምና መከራው ከዚህ ሕይወት እንዳያደናቅፋችሁ ወይም ተስፋ እንዳያስቆርጣችሁ ተጠንቀቁ። ነገር ግን ዓይናችሁ እግዚአብሔር በጉዞ መጨረሻ ላይ ሊሰጥ በገባው ተስፋ (እርሱም መንግሥተ ሰማይ ነው) ላይ የፀና ይሁን።

> "ስለዚህም አንታክትም፣ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የወስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል። የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፣ የማይታየው ግን የዘላለም ነው" (2ቆሮ 4÷16-18)።

በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስላለን ተስፋ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይሁን!

የቪሲግፌሃም

የመጨረሻ መልዕክት



አንድ ቀን የሕይወት ጉዞአችሁ ያበቃል፣ ወደ ዘለዓለማዊነትም ትሸጋገራላችሁ። ነገር ግን የሕይወት ጉዞአችሁ ፍፃሜ ምን ዓይነት ይሆን? በሕይወታችሁ ፍፃሜ፣ የተጓዛችሁት በስህተት መንገድ ላይ እንደሆነና ዕድሉ እንዳመለጠ በመገንዘብ በሀዘንና በፀፀት መሰስ ብላችሁ ትመለከቱ ይሆን? ወይስ ምናልባት የተጓዛችሁት መንገድ ትክክለኛ መንገድ ሆኖ፣ ነገር ግን ባጋጠማችሁ በዚህ ዓለም ፈተናና ችግር ተተብትባችሁ ወደኋላ እንዲያስቀራችሁና ወደ ሙሉ ብቃት እንዳትደርሱ ሆናችሁ ይሆን? ይልቁንም፣ ፀሎቴ በሕይወታችሁ በትክክለኛው መንገድ ላይ እንድትሆኑ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን፣ የጉዞአችሁ ፍፃሜ በደስታ የሚጠናቀቅ እንዲሆን አፀልያለሁ። የእግዚብሔርን ሀልውና በሁሉም አቅጣጫ እንድታውቁና በኑሮአችሁ መሃል የሚያጋጥማችሁ ጥልቅ በሆነ ችግር ውስጥ ስታልፉ በርሱ እንድትበረቱ ፀሎቴ ነው።

አንተ እና እኔ አሁን አብረን ስመቀመጥና ስመነጋገር ብንችል ኖሮ፣ እስካሁን ስላደረከው ጉዞ በሰማሁ ነበር። ጉዞህ በየትኛው መንገድ ነው? እግዚአብሔር ባዘጋጀልህ በትክክለኛው መንገድ ነው? ወይስ አሁንም ኢየሱስ "ሰፊው መንገድ" ብሎ በገለፀው - የሚያባብልና ቀላል የሆነ ግን በመጨረሻ ባዶነትን፣ ሀዘንና ሞትን የሚያተርፍ መንገድ - ላይ ነህ?

የትኛውን መንገድ እንደምትከተሉ ስመወሰን ስዓቱ አሁን ነው። እስካሁን ከቶ ያልወሰናችሁ ከሆነ፣ ዛሬ ወደ ክርስቶስ እንድትመለሱና በአምነት ወደ ሕይወታችሁ እንዲመጣ እንድትፈቅዱለት አጥብቄ አሳስባችኋለሁ። ማንም ብትሆኑ፣ ምንም አድርጋችሁ ቢሆን፣ እግዚአብሔር አሁንም ይወዳችኋል፣ ወደ አዲስ የሕይወት መንገድ መምጣት እንድትችሉ፣ ክርስቶስ ለለ ኃጢአታችን ሞቷል፣ ተነሥቷልም። የርሱ መንገድ ይኼ ነው። የእግዚአብሔር ተስፋ ስናንተም ነው፣ "በርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ አግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" (ዮሐ 3+16)። ዛሬውኑ ራሳችሁን ለክርስቶስ ስጡ።

ከዚያም፣ ግባችሁ በየዕለቱ አርሱን መከተል ይሁን። በዚህ መጽሐፍ እንደተመለከትነው አግዚአብሔር በሕይወታችን በሚደርሱ ችግሮችና መከራዎች አማካይነት ራሳችንን እንድንፈትሽና ጉዞአችንን በድል እንድንፈጽም ሁሉን ነገር ሰጥቶናል። ሕይወታችሁን አታበላሹት፣ ከአግዚአብሔር ዕቅድ በወረደ ነገር ራሳችሁን አታጠላልፉ።

አንድ ቀን የምድር ሕይወት ያበቃል። ያንን ቀን እኔ አናፍቃለሁ፣ ምክንያቱም ከዚህ ሕይወት በኋላ ያለው መንግሥተ ሰማይ እንደሆነ አውቃለሁ። አናንተም እንድትናፍቁ አፀልያለሁ። ነገር ግን አስክዚያ ቀን፣ እግዚአብሔር ወደርሱ አስከሚጠራችሁ ደረስ፣ ግባችሁን ለክርስቶስ ስመኖር አድርጉ።

“ይህን መጽሐፍ በምታነቡበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዲባርካችሁ፣ እንዲያስተምራችሁና በዚህ አስተማማኝ ባልሆነ ዓለም በእምነት እንድትኖሩ እንዲያደርጋችሁ እሻለሁ።”



ቢሊ ግራሃም

ቢሊ ግራሃም፣ ታዋቂ ፀሐፊ፣ ሰባኪና በታሪክ ከተዘገቡት ከማናቸውም የበለጠ ለብዙ ሰዎች ፊት ለፊት ወንጌልን የሰበኩ ወንጌላዊ ናቸው፣ በዚህ አገልግሎታቸው በዓለም ላይ ወደ ሁለም አህጉራት ሄደው አገልግለዋል። አነሳሳሽና ቀስቃሽ የሆኑ ሥራዎቻቸው (ለምሳሌ መላዕክት፣ የደስታ ምስጢር፣ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም፣ መንፈስ ቅዱስ፣ ተስፋ ለተጨነቀ ልብ፣ ዳግመኛ መወለድ) በሚሊዮኖች ተነበዋል።

ይህን ጉዞ የምትጓዙት ለአንዴ ብቻ ነው። ጉዞአችሁ ምን ዓይነት ይሆን?

ቢሊ ግራሃም

በዚህ በሚጠናቀቅ የሕይወት ጉዞ፣ እግዚአብሔር ለናንተ ያለው አቅድ ምን እንደሆነ እንድትፈልጉ ቢሊ ግራሃም ይጋብዟችኋል። በሕይወት ጉዞአችሁ በየትኛውም ደረጃ ላይ - በጅማሬ፣ በጉልማሳነት ወይም በማጠናቀቂያው ጫፍ - ብትሆኑ ሕይወት የተለያየ የመጓጓ መንገድ እንደምታቀርብላችሁ ተምራችኋል። በጉዞአችሁ ውሳኔ የሚጠይቁ መንታና መስቀለኛ መንገዶች ያጋጥሙአችኋል፣ በሕይወታችሁ መሠረታዊ ለውጥ የሚያስከትል ውሳኔ የሚሹ ይሆናሉ። ትክክለኛውን ጎዳና የምትመርጡት እንዴት ነው? በጉዞአችሁ ከሚያጋጥሙአችሁ አይቀሬ ከሆኑ እንቅፋቶችና ስርንጥች የምታፈገፍጉትስ እንዴት ነው?

ቢሊ ግራሃም፣ ብቻችንን አይደለንምና የምሥራች ይሉናል። እግዚአብሔር ለኛ ጎዳናውን ማጠፍ ብቻ ሳይሆን በመንገዳችን በሚያጋጥሙን ተግዳሮቶች ሊረዳንና ወደ ግቡ (ወደ ቤታችን) እንድንደርስ ሊመራን አብሮን ለመሆን ይፈልጋል።

ታዋቂው ፀሐፊና ወንጌላዊ፣ በዚህ መጽሐፋቸው በርኅራኄና በፍፁም ግልጽነት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ከተጓዙ ሰዎች ብቻ የሚገኝ ግንዛቤ እየሰጡን ደረጃ በደረጃ ይመሩናል። እግዚአብሔር ለኛ ያለውን ዓላማና ኢየሱስ የሠራልንን እንማራለን። ፈተናዎችን አፍራሽ ልማዶችንና የሕይወት ቅይማቶችን (መከፋቶችን) እንዴት እንደምናስተናግዳቸው እንገነዘባለን። እንዲሁም ትክክለኛ ውሳኔ በማድረግ፣ ጋብቻችንን ለማጠናከር፣ እና በጉዞአችን ለሚገጥመን ህመም፣ ሥቃይና ሀዘን፣ በፀሎት የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅበትን ተሞክሯዊ ምክር ይሰጠናል።

ይህ የቢሊ ግራሃም ሥራ፣ በብዙ በግል ሕይወታቸው ልምዶች የተሞላ መጽሐፍ ሲሆን፣ የሚልቀውን ለሚፈልግ ለማንም፣ ጥበብ፣ ማበረታቻ፣ ተስፋና መነሳሳት ይሰጣል . . .

የማይደገም ጉዞ።

Printed by Africa Printing P.L.C

ዋጋ ብር 35.00